# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር 10ኛ ዓመት ቁጥር 2 ግንቦት/ሰኔ 1994 ዓ.ም



## ጨጐዴ ሐና ደብር ቤተ ጉባ

(ምዕራብ ጐጃም)

## እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## በራሳችን እንጠቀም

በዕለተ ሰንበት በቅዳሴ ላይ ነን:: በቅዳሴው መካከል አንድ ወጣት መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ:: ነጠላ አልለበሰም:: በአንገቱ ላይ ጥቁር ቦርሳ አንጠልጥሏል:: በዚሁ ጊዜ የተወሰኑ እናቶችና አባቶች በየበሮቻቸው ገቡ:: ልጆቻቸውን ክርስትና ሊያሥነሱ ነው:: ዲያቆኑ «ተንሥኡ» ቢል አጠገቤ በጃኬት ያለው ወጣት ቁጭ:: «ስግዱ»፣ ቁጭ:: ባያውቅ ነው አልኩ:: ወደ ምህላ ጸሎት /እግዚኦታ/ ተቃረብን:: በካህኑ መሪነት ሕዝቡ ይከተላል:: ወጣቱ ተነሥ እንኳ ቢባል ቁጭ እንዳለ ቀረ:: ድርገት ሆነ:: ምእመኑ መሬት ላይ ተደፋ፣ ሰገደ:: ወጣቱ ግን ቁጭ:: ካህናቱ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ማቀበል ሲጀምሩ ከአጠገቤ እመር ብሎ ሄደ:: ወጣቱ ለካ ፎቶ አንሺ ነው:: ሥራውን ጨረሰና ተመልሶ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ:: አባቶች ሊባርኩን መጡ:: ወጣቱ ምን ጨንቆኝ ብሎ ቁጭ:: ዲያቆኑ «እትው በሰላም» ብሎ አሰናበተን:: በኋላ ስሰማ የ ወጣት በሃይማኖት የማ ይመስሉን የሌሎች ወገን ነው:: እንደዚህ ዓይነት ዝግጅት ሲኖረን የራሳችንን ኦርቶዶክሳውያን ባለሞያዎችን መጠቀም የለብንም ትላላችሁ?

ዋሲሁን
ከነቀምቴ

## ድንቅ ትብብር

እኔ በምኖርበት በይርጋለም ከተማ ውስጥ የሚገኙ የቅዱስ አማኑኤል፣ የቅድስት ማርያምና የቅዱስ ሚካኤል ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት አባላት በመተባበርና አንድነትን በመፍጠር ከዚህ በፊት በጥምቀትና በመስቀል ጊዜ አምልኮተ እግዚአብሔርን የምንፈጽምበትን ከበዓላቱ ረድኤትና በረከት የምናገኝበትን የመስቀል ደመራና የባሕረ ጥምቀት ቦታ ምእመናንን በማስተባበር በግንብ አጥር እንዲከበር ንብረትነቱም የቤተ ክርስቲያን እንዲሆን አድርገዋል:: እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይክፈልልን:: በሌሎች አካባቢዎች ያሉ ሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያትም ከእነዚህ አባቶች መተባበርንና አርቆ አስተዋይነትን እንዲማሩ ቢሆን መልካም ነው እላለሁ::

ዲ.ካሣሁንና ሃይማኖት
ከይርጋለም

## እባቡን ሸሽቶ ወደ ዘንዶው

ከኃ/ገብርኤል ዘሐና

ሌሊቱ አልቆ ሰማዩ የአህያ ሆድ በመሰለበት ሰዓት የመንገደኛው ቤት በር ተቆረቆረ:: ሁለት ሦስቴ ተቆረቆረ:: መንገደኛው ቢሰማም ከሰው ጋር ከመነጋገሩ በፊት ፈጣሪውን «አቡነ ዘበሰማያት» እያለው ነው:: ክፉውንም ደጉንም ከመስማት በፊት ፈጣሪን ተመስገን... ማለት ምንኛ ድንቅ ነው::

በሩ አሁንም ይቆረቆራል:: ማን ነው? ባለጉዳይ መልስ ሰጠ:: መንገደኛው ገባው:: መንገደኛው ነው፣ መንገደኛውን ለረጅም መንገድ የሚቀሰቅሰው:: ከመ ቅጽበት ሁሉን አከናውኖ በሩን ከፍቶ ወጣ-መንገደኛው:: ቀኑን ሙሉ ሲጓዝ ውሎ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ከአንዲት ከሚያውቃት ከተማ ገባ:: በዚህን ሰዓት የት ይኬዳል? መንገደኛው አንድ ሁለት ምዕራፍ በእግር እንደ ተጓዘ ከአንድ ሆቴል ደረሰ:: የሆቴሉን ባለቤት ያውቃቸዋል:: አሉ የተባሉ ክርስቲያን ናቸው:: እንዲያውም በቅርቡ በሰበካ ጉባኤና በሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አሠሪነት መመረጣቸውን ሰምቷል፤ መንገደኛው:: የሆቴሉ የመጀመሪያው ክፍል በሰውና በሙዚቃ ሁካታ ተደበላልቋል:: መብራቱ ቦግ ጭልም ይላል:: መንገደኛው ጆሮውን አፍኖ አንገቱን አቀርቅሮ ወደ ውስጥ ዘለቀ:: ባይመችም ለጎኑ ማሳረፊያ የሚሆን መኝታ ለተጋመሰው ሌሊት ተከራየ::

ሒሳብ ሊከፍል አልጋ ክፍሏን እያነጋገረ ሳለ አንድ በግምት 14 ዓመት የሚሆነው ጎረምሳ ልጅቷን በጥፊ አጮላት:: ሳቀች:: እጇን ጠመዘዛት:: ጮኸች:: ሸሸች:: ተከተላት:: ቢጤዎቹ በአንድነት «አይለቃትም» ተባባሉ:: ሌላም፣ ሌላም አሉ:: ልታመልጠው አልቻለችም:: ያዛት:: ይዟት.......::

መንገደኛው ተናደደ:: ግን አንዳች አልተነፈሰም:: በልቡ ግን ብዙ አወራ:: ለመሆኑ ይህ ሰው ነው ወይስ እንስሳ? ለመሆኑስ የእናቱን ጡት መጥባት ትቷል? እንጀራ በቅጡ በልቶ ጠግቧል? በዚህን ሰዓት ውጪ ምን ይሠራል? ወላጆች አሉት ወይስ......? ጥያቄውን አቁሞ የልጅነት ጊዜውን በትዝታ ሠረገላ ገሥግሦ ቃኘው:: በጨዋታ እንኳን «እገሊት ሚስትህ ናት» ሲባል ይሰማው የነበረው እፍረት፣ ሁለት ሰዎች ሲያወሩ ገለል ማለቱ፣ በጊዜ ወደ ቤት መሰብሰቡ፣ ጨዋታ እንኳን ይዘው ከሆነ ታላላቆች ሲመጡ ጨዋታውን አቁሞ ማሳለፉ ..... በመንገደኛው ኅሊና ውስጥ ተግተለተሉ::

መንገደኛው ዘመኑንም አሰበ:: በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የተነሣ ጧሪ ቀባሪ ያጡ አረጋውያን፣ በለጋ ዕድሜያቸው የተቀጩ ወጣቶች፣ በበሽታው ተይዘው በየሆስፒታሉ፣ በየቤታቸው በአልጋ ላይ የዋሉ ወላጅ ወዳጅ ያገለላቸው ሕሙማን፣ ወላጆቻቸውን በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክንያት ያጡ የነገ ተስፋቸው ከጭራ የቀጠነባቸው ሕፃናት.....:: መንገደኛው «አይ ኢትዮጵያ!» አለ::

ልጅቷ እየሳቀች መጣች:: «ጎረምሳው» ድል በማድረግ መንፈስ ይንጀባረራል:: በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ልቅ መሆኑን ማን በነገረው :: እሱም እሷም አንዳች የኀፍረት ስሜት የለባቸውም:: ብቻ መጥታ ለመንገደኛው መኝታ ክፍሉን አሳየችው:: መንገደኛው ዝምታው አላስደሰተውም:: ሲፈራ ሲቸር «ዕድሜሽ ስንት ነው?» ብሎ ጠየቃት:: «አሥራ ስድስት» አለች:: ትምህርት ጨርሰሻል? ከስምንተኛ ክፍል ነው ያቋረጥኩት:: ለምን? እንገቷን ሰበረች:: ነገር አለ ማለት ነው አለ፣ መንገደኛው:: «የዛሬ ሁለት ዓመት አባቴ ወደ ሽሬ ዘመተ:: «ድንበሬን» እንዳለ በዚያው ቀረ:: ለእናቴ የመጀመሪያ ልጇ ነኝ:: ሌሎቹ ሕፃናት ናቸው:: ሁላችንንም ለማሳደግና ለማስተማር ዐቅም የላትም:: ይህን ያወቀች ዘመዴ /የሆቴሉ ባለቤት/ ላግድጋት ብላ ወሰደችኝ:: እንደ መጣሁ ለአንድ ዓመት በወጥ ቤትነት እንድሠራ አደረገችኝ:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በአስተናጋጅነትና በአልጋ ክፍል ትሠራ የነበረችው ልጅ ስለ ሄደች በእርሷ ቦታ መደበችኝ::»

- ሥራው ተስማምቶሻል? «ባይስማማም ስላስገደደችኝ እሠራለሁ::»
- ስለ ዘመኑ በሽታ አታውቂም? «ዐውቃለሁ ግን ምን ላድርግ? ምርጫ የለኝም::»
- እናትሽ ምን እየሠራሽ እንደሆነ ያውቃሉ? «በፍጹም አታውቅም:: ብታውቅ ከፍተኛ ጥል ነው የሚጣሉት::»
- በዚህ ሁኔታሽ እስከ መቼ ትቆያለሽ? «እግዚአብሔር ያውቃል::» መንገደኛው የወትሮው ራስ ምታቱ ተነሣበት:: ከዚህን በላይ ሊያናግራት አልቻለም:: ምን ያድርግ? አቅም የለውም:: ሴትዮዋን /የሆቴሉን ባለቤት/ ሊያነጋግራቸው አሰበ:: ሰዓቱ ከሌሊቱ 6:00 ሆኗል:: «ቢሆንም...» አለ:: «የሆቴሉ ባለቤት አሉ?» «የሉም፥ አዲስ አበባ ሄደዋል» አለችው:: የመኝታውን ሒሳብ ስጥቷት መንገደኛው ወደ ክፍሉ ገባ:: ከራሱ ጋር ያወራ ጀመረ::

ወ/ሮ እገሊት ታላቅ ክርስቲያን አይደሉም ወይ? የተቸገረን መርዳት ሲገባቸው ልርዳ ብለው ከድጡ ወደ ማጡ የሚከቷት? ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ ሕንፃ ሥላሴን መታደግ ምነው ተሳናቸው? መንገደኛው ሄደ ነጎደ:: በየቡና ቤቱ፣ በየሆቴሉ ካሉ አስተናጋጆች ከእናት አባታቸው ቤት በሀብታም ዘመዳቸው «እናሳድጋቸው፣ እናስተምራቸው» ተብለው ተወስደው ለዝሙት አዳሪነት የተዳረጉት ምን ያህል ይሆኑ? ሥላሴ ይወቁት:: የአንዱ የንግድ ሥራ ሊካሄድ የሌላው ሕይወት ለኃጢአት ሊሠዋ? መንገደኛው አነባ::

በአሥራ አምስት ዓመቷ ለቡና ቤት የኃጢአት ሥራ የተዳረገች ልጅ ፍጻሜዋ ምን ይሆን? ኤድስ፣ ውርጃ፣ የተለየዩ የአባለዘር በሽታዎች፣ አባት የሌላቸው ልጆች፣ ጎዳና ተዳዳሪነት....... ከሚዳ ወድቆ መቅረት፣ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለ.........መዳረግ:: ምን ይበጃል? ዘመድ ዘመዱን ለኃጢአት ሊሠዋ ካቀረበ በክርስትና ተኖራታ? መንገደኛው የሥነ ምግባርን መጉደል፣ የሰውን መጨካከን፣ የሀገራችንን ምስቅልቅል ችግሮች..... ቢያውጠነጥንም ማጣፊያው ቸገረው:: ምን እናድርግ? ከማለቱ እንቅልፍ ይዞት ጥርግ:: ለእርሱም ለሁላችንም መልካም የትንሣኤ በዓል ይሁንልን::


### የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 11.40 | 22.80 | 20.40 | 40.80 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 21.00 | 42.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለባለው ታደለ እና/ወይም መስፍን ጥላሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 68608 አዲስ አበባ ከፍለው
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ
በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን

የጌታችን ዕርገቱ በነቢያት አስቀድሞ የተነገረ ነው:: እግዚአብሔር የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጉልቶ ስለገለጠላቸው:: ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት–«እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ /በይባቤ መላእክት፣ በቅዳሴ፣ በብርሃን፣ በሥልጣን/ ዐረገ» ብሏል መዝ.46፥5:: ዳግመኛም «ወደ ላይ ዐርገህ ምርኮን ማረክህ፣ /ነፍሳትን ይዘህ ማርከህ ከሲኦል ወደ ገነት ወጣህ ዐረግህ/» ብሏል:: መዝ.67፥18:: ሦስተኛም «በምሥራቅ በኩል ወደ ሰማየ ሰማያት /ወደ ጽርሐ አርያም/ ለወጣ /ላረገ/ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤» በማለት የዕርገቱን ነገር አስቀድሞ ተናግሯል:: መዝ.67፥33:: ከዚህም ጋር «እግዚአብሔር ዐረገ፤» በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት መስክሯል::

/ትምህርተ ሃይማኖት/

መለያያችን ከመድረሱ በፊት በፈለገችው ጊዜ ልታገኘኝ የምትችልበትን አድራሻ ሰጠኋት:: ዞር ስልላት የምትጥለው ትመስላለች:: ማለት የምፈልገውን ገና አላልኩም:: መመስከር ነበረብኝ፣ ግን እኔ ሳልሆን የሚያስ ተምር እሱ እግዚአብሔር ነውና በፈቀደ ጊዜ ያስተምራታል:: አልኩና በዚህ ተጽናናሁ እሷም የአውቶቡስ ተራን ታክሲ ይዛ ነጐደች::

/ኪነ ጥበብ/

በአጤ ድልነአድ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ በ900 ዓ.ም ገደማ በዚህ ባሕር አጠገብ ቀራ ገደል እየተባለ በሚጠራው ዋሻ ጥግ ታቦተ ራጉኤል ተተክሎበት ነበር:: ይህ ቦታ በጠፍነት ከቆየ በኋላ በአጤ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት በ1265 ዓ.ም ገደማ ወደ ቆላማው ክፍል ተዛወሮ አሁን ጦር መስቀያ እየተባለ በሚጠራው ገደል አጠገብ ለሁለተኛ ጊዜ ታቦተ ራጉኤል ተተክሎ ከቆየ በኋላ በአጤ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በ1304 ዓ.ም የወንድ ገዳም ሆኖ ነበር::

/እናስተዋውቃችሁ/

በዝዋይ ገዳም የሚገኙት ተማሪዎች ከደረሰባቸው መራር ኀዘንና ከባድ ጉዳት እንዲጽናኑ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስና ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ እስከ አርባ ቀን መታሰቢያ ድረስ በገዳሙ ተቀምጠው ሲመክሩአቸውና ሲያበረታቱአቸው ሰንብተዋል::

/ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ/

ዋና አዘጋጅ - ዲ.መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ- አሉላ ጥላሁን
አዘጋጅ - ዲ. ያሬድ ገ/ መድኅን
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወ/ት ወይንሸት ወጉ

ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail-EOC-M-KIDUSAN-@ telecom.net.et.

«ማኅበረ ቅዱሳን»
እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል::

ሐመር
10ኛ ዓመት ቁጥር 2
ግንቦት/ ሰኔ 1994 ዓ. ም

# ይዘት

የማኅበሩ መልእክት
●ሃይማኖትን ታሪክንና ቅርስን መጠበቅ የሁሉም ድርሻ ነው.........................................2
ደብዳቤዎች ................................................ 4
በረከተ ወንጌል
• ትንሣኤው ትንሣኤያችን ........................6
ትምህርተ ሃይማኖት
• ጸሎተ ሃይማኖት ................................ 8
• አዋልድ መጻሕፍት ..............................11
የጥያቄዎቻችሁ መልሶች
• ቁጤማ ለምን እናስራለን?
ምሰራፍ
ኪነ ጥበብ
• ይዲድያ ማራና ይዲድያ ......................15
እናስተዋውቃችሁ
• ከዋሸራ እስከ ገረገራ............................ .20
• አቡነ ሐራ ድንግል..................................21
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
• ክርስትናና ዘመናዊነት ..........................25
ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
• ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ........................ 28

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

# ሃይማኖትን ታሪክንና ቅርስን መጠበቅ የሁሉም ድርሻ ነው

አንድ ሀገር ሃይማኖት፣ ታሪክና ቅርስ ከሌለው ማንነቱ ሊታወቅ አይችልም። በመሆኑም ብዙ ሀገሮች የአጭር ጊዜም ትሁን የረጅም ዘመን ታሪካቸውንና ቅርሳቸውን ይከባከባሉ። ዜጐቻቸውም በሥራው እንዲሳተፉ አጥብቀው ይቀሰቅሳሉ፤ ያስተምራሉ።

የብዙ ሕዝቦች መኖሪያ የሆነችው ሀገራችን በዓለም መድረክ ከፍ ያለ ታሪክና ቅርስ ያላት ናት። ይሁን እንጂ ያለመታደል ሆኖ ከቅርብ ዘመናት ወዲህ ምናልባትም ከዘመነ መሳፍንት ጀምሮ /1769–1855 እ.አ.አ./ ከጥቂት ግለሰቦችና ነገሥታት በስተቀር ስለሀገራችን የሦስት ሺህ ዘመናት በላይ ሃይማኖት፣ ታሪክና ቅርስ የሚያውቅና የሚቆረቆር ሰው ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል። አንድን ታሪክ ወይም ቅርስ ለመጠበቅና ለመከባከብ ታሪኩንና ቅርሱን አስቀድሞ ማወቅ ያስፈልጋል። ወደ ዘመናችን ስንመጣ ሃይማኖታችንን ታሪካችንንና ቅርሶቻችንን ከእኛ ይልቅ ከባዕዳን ሀገር የመጡ ጐብኚዎችና ተመራማሪዎች ይበልጥ ያውቁታል። ሃይማኖታችንን፣ ታሪካችንንና ቅርሶቻችንን በአጠቃላይ ማንነታችንን ያለማወቅ ችግር እንዳንጠብቃቸው፣ እንዳንከባከባቸውና እንዳንቆረቆርላቸውም አድርገውናል።

ይህንን ያለማወቅ ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ከሚያዝያ 4–13 ቀን 1994 ዓ.ም በማኅበረ ቅዱሳን አዘጋጅነት ታላቅ ዐውደ ርእይ /ኤግዚቢሽን/ ተካሂዶ ነበር።። ይህ ዐውደ ርእይ በ14 ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በእያንዳንዱ ክፍል ከተመልካቹ ምን እንደሚጠበቅ ለመጠቆም ተሞክሯል።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጥሪ በመክፈቻው ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስና የወጣቶች ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ እንደገለጡት ታሪክንና ቅርስን በመጠበቅ ረገድ የመንግሥት ድርሻም ከፍተኛ ነው። አያይዘውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ አገልግሎትና ትርጉም ያላቸውን ቅዱሳት መካናትን ንዋያተ ቅድሳትን፣ ቅዱሳት ሥዕላትን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ጸዋትወ ዜማን ብቻ ሳይሆን የነገሥታቱን የመኳንንቱንና የመሳፍንቱን የሥርዓተ መንግሥት ማድረሻ ንዋያት፣ አልባሳትና የወግ ዕቃዎች፣ የፍትሕና የአስተዳደር ሰነዶች፣ የሕዝቦችን ባሕልና ታሪክ በቤተ መቅደስዋ ምሕዋርና በዕቃ ቤትዋ ሸክፋ የያዘች፣ የግራኝ አሕመድን ካባ ሳይቀር ጠብቃ ለዘመናችን ያደረሰች ነዋሪ ባለርስት ናት። ከእነዚህ ዓለም አቀፋዊና ብሔራዊ ቅርሶች ታሪካዊና ሕጋዊ ባለቤትነትም አኳያ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትና ዜጎች የበኩላቸውን ጥበቃ ክብካቤ የማድረግ ታላቅ ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በበኩላቸው «ታሪክንና ቅርስን መጠበቅ የዓለም ሕዝብ ወይንም የሰው ዘር በሙሉ ድርሻ አለው፣ ምክንያቱም ቅርሶች የሰው ልጅን ታላቅ ፍጡርነት የሚገልጡ ናቸውና፤ ሀብቱም የዓለም ሁሉ ሀብት ነው» ብለዋል።

ይህንን ዐውደ ርእይ ነጭም፣ ጥቁርም በእምነት የተለያየውም እምነት የሌለውም የተመለከተው ሲሆን ቁጥሩም ከ60,000 በላይ ይሆናል። ከተሰጠው በርካታ የቃልና የጽሑፍ አስተያየት ለመረዳት የተቻለው ሕዝቡ ከዚህ በፊት ያላወቀውን ታሪኩንና ቅርሱን እንደተረዳ ለመጠበቅም የራሱን ድርሻ የሚወጣ መሆኑን ነው። እንዲያውም ይህን በመሰለ ሁኔታ ብዙ ነገር ማስተማር እየተቻለ እንደ ዋዛ ባለፉት ጊዜያት የተቆጨ አዛውንትን አስተያየት በሰማንበት ጆሮአችን «ስናድግ ሙዚየም እናሠራለን፤ በዚህና በዚያ ሞያችን ለቤተ ክርስቲያናችን እንዲህና እንዲያ እናደርጋለን» በማለት የሚናገሩና የሚያለቅሱ ሕፃናትና አዳጊ ወጣቶችን ለማስተዋል ተችሏል። በዐውደ ርእዩ መዝጊያ ላይ ቅዱስ ፓትርያርኩ አበክረው ያስታወቁት ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቋሚ ዐውደ ርእይ የምታዘጋጅ መሆንዋን ሲሆን በዚህ ሥራ የሁሉም ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ ተሠምሮበታል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ማኅበሩ በዐውደ ርእዩ የታዩት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪኮችና ቅርሶች በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የበለጠ ለማሳወቅ ከዐውደ ርዕዩ ጋር በተያያዘ መልኩ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኰሚሽን የአፍሪካ አዳ ራሽ ሚያዚያ 9 እና 10 ቀን 1994 ዓ.ም አሥራ ሁለት ጥናታዊ ጹሑፎች የቀረቡበትንና 200 ያህል ሰዎች የተሳተፉበት ዐውደ ጥናት አዘጋጅቶ ነበር። በዚህ ዐውደ ጥናትም የሁላችንም የሆኑትን ብዙ የሃይማኖት፣ የታሪክና የትውፊት ሀብቶቻችን መጠበቅና መከባከብ የሚገባን መሆኑ ተገልጧል። በዐውደ ጥናቱ የቀረቡት ሁሉም ጉዳዮች የመንግሥትን የቤተ ክርስቲያንን እንዲሁም የእያንዳንዱን ዜጋ ተሳትፎ የሚፈልጉ መሆናቸው ተመልክቷል።

«የደብረ ሥልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የባለቤትነትና የይዞታ መብት ከዓለም አቀፍ ሕ ግ አንጻር» በሚል ርእስ የቀረበውን ጥናት ብናስታውስ በኢየሩሳሌም የደብረ ሥልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሦስት ሺ ዘመናት ርስትዋ የነበረ ሲሆን ከ1766–1838 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ሌሎች ይዞታዎቿ ሁሉ በግሪኮችና በአርመኖች ሲነጠቁ ይህ ገዳምም በግብጻውያን ተወስዶብን ነበር። ይሁንና በቦታው ላይ ይገኙ በነበሩት ጥቂት ኢትዮጵያውያን መነኮሳትና መነኮሳዪያት ጽናት፣ በሀገራችን ነገሥታት ያልተቆጠበ ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ፣ እነ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስን በመሳሰሉ አባቶቻችን አርቆ አስተዋይነት እንዲሁም እውነታውን ተረድተው ሞያዊ አስተዋጽዖ ባደረጉት የዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራን ብርቱ ጥረት ቀደም ሲል በዮርዳኖስ መንግሥት አስተዳደር በኋላም በእስራኤል መንግሥት በተቋቋሙት የፍትሕ መድረኮች ባለቤትነታችንን በውል አረጋግጠናል። ከዚህም በላይ የእስራኤል መንግሥት የገዳሙን መግቢያ ቁልፍ ለእኛ በመስጠቱ ግብጻውያን መልሰው ለመንጠቅ ጉዳዩን ብሔራዊ እና ዐረባዊ አጀንዳ በ ማድረግ ሕዝቡም በእምነቱ ሳይለያይ ከመንግሥት ጋር አንድ ላይ በመሆን እየተረባረቡ ይገኛሉ።

በእኛም በኩል ይህ የታሪክና የቅርስ ጉዳይ ስለሆነ መንግሥትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻቸውን ሳይሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ በቅንጅት ሊያስብበትና ይዞታውን ሊያስጠብቅ ይገባል። የዓለም ከተማ ትሆናለች ተብላ በምትጠበቀው በኢየሩሳሌም ኢትዮጵያ ይዞታዋ እንዲከበርላት ድርሻችን ምንድን ነው ብለን ልንጨነቅ ያስፈልጋል።

ሌላው በሥነ ጹሑፍና በቅዱሳት መጻሕፍት ሀብትዋ የምትታወቀው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራ ሷን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በማዘጋጀት ላይ ነች። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በግእዝ ቋንቋ ተጽፎ እስከ ዘመናችን የደረሰ ነው። ዛሬ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በእጃችን የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላ ሲተረጐም፣ እንደገና ሲጻፍ ሲተረጐም የመጣ በመሆኑ ከመጀመሪያው መሥመር የለቀቁ ሐሳቦችና ሐረጐች ያሉበት መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህም በጥንቃቄ የራሳችንን ከራሳችን ቋንቋ ለመተርጐምና ለማሳተም የሚደረገው ጥረት ሃይማኖትን፣ ታሪክንና ቅርስን ከመጠበቅ አኳያ ስለሆነ ጉዳዩ የሁላችንም ነው።

በመሆኑም ምእመኑ እንዲሁም ለታሪኩና ለቅርሱ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በአጠቃላይ ለንትመቱ ሥራ የገንዘብ አቅሙን ሊያስተባብር ይገባል። ይህንን ሥራ በባለቤትነት የያዘችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለሁሉም ድርሻ ድርሻውን አከፋፍላ ብትሰጥ ወደ ኋላ የሚል ዜጋ ይኖራል የሚል እምነት የለንም። ምክንያቱም ሃይማኖትን፣ ታሪክንና ቅርስን መጠበቅ የሁሉም ግዴታ ነውና። ከዚህ ባሻገር በዐውደ ጥናቱ እንደተጠቆመው ቤተ ክርስቲያናችን የራሷን የጥናትና ምርምር ማዕከል ብታቋቁ ም፣ ዐውደ ጥናቱ በየዓመቱ ቢካሄድ ለዚህም ስኬታማነት በልዩ ልዩ ዘርፍ ያሉ ባለሞያዎች እንዲሳተፉና እንዲተባበሩ ቢደረግ የሚሉትን የመፍትሔ ሐሳቦች ተገቢነት በእጅጉ የምናምንበት ብቻ ሳይሆን አጥብቀን የምንሠራበትም ይሆናል። ስለሆነም የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያናችን የአስተዳደር አካላትና መንግሥት ሁኔታውን ቢያመቻቹ፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ምሁራንና እያንዳንዱ ምእመን ደግሞ ተግባራዊ መተባበር ቢያደርጉ ጥረቱን ሁለንተናዊ መልክና ትርጉም እንዲኖረው ያስችላል እንላለን።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም በርቱ ጠ... ክሩ፣ በሃይማኖት ጐልምሱ።

*ዮርዳኖስ የጓላሸ...*
*አዲስ አበ...*

## አይገባም!

ውድ አርቶዶክሳውያን፤ ሰላምና ጤና እንደዚሁም ፍቅር ዘወትር ከእናንተ ጋር ይሆኑ ዘንድ እመኛለሁ። በዚህ ባለንበት ዘመን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በርካታ ስሕተቶችን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ስንፈጽም እንታያለን። ከእነዚህም ውስጥ በእኔ በደካማው ኅሊና ያስተዋልኩትን አንዱን ልግለጽ። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ መቅደስ ወለል ላይ የሚነጠፉ የወለል ምንጣፎች ስመ እግዚአብሔርንና ቅዱሳት ሥዕላትን የያዙ መሆን ጀምረዋል። እነዚህ ምንጣፎች አገልግሎታቸውን የሚያበረክቱት በመረገጥ በመሆኑ ካህናትና ምእመናን ይረግጡአቸዋል። ከእነሱ ጋር የያዙት ስመ አምላክና ቅዱሳት ሥዕላትም በዚህ ጊዜ ይረገጣሉ። ይህ ከክህደት የከፋ ክህደት ስማቸው በሚከብርበት ምስጋናቸው በሚቀርብበት በቤተ መቅደስ መፈጸሙ በእጅጉ የሚያሰቅቅ ነውና ምእመናን እንድናስተውልና የሚመለከታቸውም አካላት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ አደራ እላለሁ።

*ከንፈ ሀብቴ*
*ደ/ም/ቅ/ሚካኤል ሰንበት ት/ቤት*
*አዲስ አበባ*

## በማዕከል ይሆሪ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቤተ ክርስቲያናችን ስም የሚወጡ አንዳንድ መዝሙራት ከቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ እምነት ጋር ሲጋጩ ይታያሉ። የሐሳብ እና የቃላት ሕጸጾች ጐልተው ይታዩባቸዋል። እንዲሁም ሮጥ ሮጥ ያሉ በመሆናቸው ምእመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን የማቅረብ ኃይላቸው አናሣ ነው። አሁን አሁን ደግሞ በካሴቶቹ ሽፋን ጀርባ ላይ የዘማሪውን ወይም የዘማሪዋን ፎቶ ግራፍ ማውጣት እየተስተዋለ መጥቷል። ይህ ድርጊት ከእግዚአብሔር ክብር የራስን ክብር ማስቀደም ነው። ስለዚህ ይህ ሁሉ ግድፈት ቀርቶ በመዝሙራቱ ምእመናን ትክክለኛውን አገልግሎት እንዲያገኙ የሚወጡት ካሴቶች በመሉ ማዕከላዊ በሆነ ሁኔታ የሚገመገሙበት መንገድ ቢፈጠር መልካም ነው እላለሁ። ለዚህም የመዘምራኑ ፈቃደኝነት፣ የምእመናን ግፊትና የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስገዳጅነት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ማስተዋሉን ይስጠን።

*ገብረ አረጋዊ*
*ከፍኖተ ብርሃን ሐዋርያ*
*ጎላ ቅ/ሚካኤል ሰንበት ት/ቤት*

## በመጽሐፍ መልክ ቢዘጋጅ

ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ከእኛ ጋር ባይኖሩም በመንፈስ ከእኛ ጋ... በመሆን የሚያስተምሩንና የሚመክሩ... ን የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስን ታሪክ... በተለያየ መልኩ በመጽሔቷ እየቀረበ... በመሆኑ በእጅጉ እያስደሰተኝ ነው። ነገር ግን ብፁዕ አባታችን በሕይወት ዘመናቸው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲጠበቅ ትምህርቷም እንዲስፋፋ ያደረጉት ተጋድሎ እጅግ ሰፊና መጽሐፍ የሚወጣው በመሆኑ በእሳቸው ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን አንድ መጽሐፍ ማሳተም ብትችሉ መልካም ነው፤ የብፁዕ አባታችን ታሪክ ቅርሳችንና ታሪካችን በመሆኑ።

*በሪሁን ገብሩ*
*አዲስ አበባ*
*ትርሲተ ማርያም*
*ጉባ...*

<u>ከአዘጋጁ</u>፦ የተወደዳችሁ አንባብያን ለአስተያየታችሁ እያመሰገንን ጉዳዩ ወደፊት ሊሠራ የታሰበ መሆኑን እንገልጻለን።

## ያጽናሽ

ሐመራችን፤እንኳን ለ10ኛ ዓመት የልደት በዓልሽ አደረሰሽ። በ10ዓመት የሕፃንነት ዕድሜሽ በጽሑፍ ልገልጠው የማልችለው መጠነ ሰፊ ዕውቀት አስጨ ብጠሽኛል። በዚህ ዘመን አንቺን ያስነሣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። አንቺንም እስከ መጨረሻው ያጽናሽ።

*ወልደ መድኅን*
*አዲስ አበባ*

## ጊዜ አንስጥ

እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ። ባለፈው የ10ኛ ዓመት ቁጥር 1 እትም የዓምደ ወራዙት ዓምድ ላይ የጅማ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከቀለም ትምህርታቸው ጐን የአብነት ትምህርት እየተማሩ መሆናቸውን ገልጻችሁልናል። በእውነቱ በእጅጉ የሚያስደስትና ተስፋን የሚያለመልም ነው። የተማሪዎቹን አርአያነት በመከተል ሁላችንም ይህንን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለማግኘት የማንችለውን ትምህርት ልንማር ይገባል። ነገ «ሊቀ ሊቃውንት ዶክተር» ለመባል ያለማችሁት የጅማ

## አሁን ደግሞ...

በእናንተ የተስተካከለ ዓላማ በእግዚአብሔር አከናዋኝነት ትውልዱ ያለውን እንዲያውቅ በተለያዩ ቦታዎች ዐውደ ርእይ እያዘጋጃችሁ በመሆኑ ትመሰገናላችሁ። ለቅርሳችን፣ ለሃይማኖታችንና ለታሪካችን ዘብ እንድንቆም ስለ እኛነታችን በሚገባ ማወቅ አለብንና። ይህን የማስተዋወቅ ኃላፊነት በሚገባ እንደተወጣችሁ /ሁሉም አውቋል ባይ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ባልም/ እኔ ቀዳሚ ምስክር ነኝ:: አሁን ደግሞ ያሉትን እንዴት እንጠብቃቸው፤ ከእጃችን የወጡትን እንዴት እናስመልሳቸው ወደሚሉት ወቅታዊና አንገብጋቢ ርእሰ ጉዳዮች ፊታችሁን አዙራችሁ በመጽሔታችሁና በጋዜጣችሁ እንዲሁም ዐውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት እንድትተጉ ቢሆን መልካም ነው እላለሁ::

*ጸጋሁን ሞንአ*
*ድሬዳዋ*

## የተዋሕዶ አርበኞች

እግር ጥሎኝ መልካም ነገር ዐየሁ:: ከአዲስ አበባ 752 ኪ.ሜ ከሱዳን 90 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው ጀባ ከተማ ነው:: በከተማዋ የሚገኘው የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤና ሰንበት ት/ቤት አባላት በቅንጅት የበረሃው ዋዕይ ሳይበግራቸው ረጅሙ ዳገትና ቁልቁለት ሳያደክማቸው ካህናትን አስቀድመው ከበሮ ተሸክመው አሕዛብ እንዲጠመቁ እያደረጉ ነው:: በወርቅ ቁፋሮ ከቤተ ክርስቲያን ርቀው የሚገኙ ምእመናንንም አሉበት ድረስ በመሄድ አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው:: እነዚህ አገልጋዮች በእውነቱ በዘመኑ የተነሡ የተዋሕዶ አርበኞች ቢባሉ አያንሳቸውም:: ከሀገረ ስብከታቸው ጀምሮ ሁሉም ባለው አቅም ሊረዳቸው ይገባል እላለሁ::

*መ/ር እሸቱ ተክሌ*
*ጀባ*

## ስተግባራዊነቱም

ሐመር በመግቢያዋ ላይ ትኩረት ሰጥታ በምታሰፍረው «የማኅበሩ መልእክት» ላይ የማገኛቸው ርእሶች ወቅታዊና እጅግ ደስ የሚያሰኙ ልቤን በሐሴት የሚሞሉ ናቸው:: ከብዙ በጥቂቱ «ትኩረት የሚሹ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች፣ በዕርዳታ ስም ወንጀሎችን መሥራት መቆም ይገባዋል፣ ይህ ሁሉ አድማና ግርግር...» የሚሉት ይገኙበታል:: ተለይ በ9ኛ ዓመት ቁጥር 6 ላይ «ልመናም ሕግና ሥረዓት ይኑረው» ብላ ያሰፈረችው መልእክት ደግሞ ለንግሥ በሄድኩ ቁጥር ዘወትር ከሚያሳስቡኝና ከሚያስጨንቁኝ ጉዳዮች አንዱ ነው:: ይህ በአሁኑ ወቅት አየተስተዋለ ያለ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ የበለጠ አሳሳቢ የሚሆነው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ቅዱሳት ሥዕላትን በመያዝ ጥላ ዘርግተው ምንጣፍ አንጥፈው የሚለምኑ ሰዎች ሲታዩ ነው:: በሌላም በኩል ሰንበት ተማሪዎች የደንብ ልብስ ለብሰው ከበሮ ጸናጽል ይዘው እየዘመሩ ሲለምኑ መመልከት እጅግ አስደንጋጭ ነው:: ይህን አደጋ ሐመር 9ኛ ዓመት ቁጥር 6 በሚገባ አስታውሳ መፍትሔውንም ጠቋቁማለች:: ታዲያ መፍትሔውን እንደጠቆማችሁ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድም እንድትፈልጉ አደራ እላለሁ:: እግዚአብሔር ይጠብቀን::

*ለይኩን ብርሃኑ*
*ኮቶቤ ደ/ጽ/ቅ/ሚ/ብርሃን*
*ሕይወት ሰንበት /ት/ቤት*

## የልብ ዐውቃ

የሐናው ኃ/ገብርኤል ሆይ መጽሐፍ «ሠናይ እገሪሆሙ ለእለ ይዜንው ሠናየ ዜና፤ መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው» እንዳለ በሄደበት ሁሉ ትምህርትን ለመቅሰም ለሚተጋው አንተነትህ ሰላም ይሁን እላለሁ:: በመጽሔቷ የፊት ሽፋን የውስጥ ገጽ ሁልጊዜ እየሰነቅህ የምትልክልኝን ትዝብታዊ ጹሑፎች በተመስጦ አነባቸዋለሁ:: የጽሑፎቹ ይዘት ሁልጊዜ እኔንም የሚያሳስቡኝ አንተን እንደሚከነክኑህ እኔንም የሚከነክኑኝ ናቸው :: የልብ ዐውቃዬ ነህና በርታ::

*ሱራፌል አካሉ*
*ሻሸመኔ*

## አዎን÷አሁን ነው!

በሐመር 10ኛ ዓመት ቁጥር 1 የወጣው የማኅበሩ መልእክት እጅግ ወቅታዊ ነው:: ትናንት ከእጃችን የወጡትን ንዋያተ ቅድሳት የምናስመልስበት ጊዜው አሁን ነው:: አዎ! አሁን ነው:: እንደውም ዘግይቷል:: ሁላችንም ኢትዮጵያውያን በያለንበት ድምፃችንን እናሰማ::

*ሰላማዊት ለወየሁ*
*ባሕር ዳር*

## ዛሬም ያስፈልጉናል

ባለፈው ያወጣችሁት
ፁዕ አቡነ ጐርጐርዮስን ስብከ
ጹም መደነቅ አነበብኩት::
ቴን ነው የምላችሁ ብፁዕነ
በአንደበታቸው በሚያስፈራ
ሞገሳቸው ከፊቴ ቆመው እ
ማሩኝ ነው የቆጠርኩት::
ቸው ይደርብን:: ዛሬም እ
እኛ ቀርቶ መላ ቤተሰባችን
ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እ
ግስ የሚመክር፣ መለያየት
ሆን አንድነትን ፍቅርንና
ሰብን የሚሰብኩ አባቶች እ
ን እንፈልጋለን:: እግዚአ
የአባቶቻችን ልጆች ያድርገን

*ወ/ሮ ሙላቷ*

## ታሪክ ይዘክራቸዋል

በሐመር 10ኛ ዓመት
1 እትም «ለካ የወታደሩ
በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ ተፈ
ሯል» በሚል ርዕስ የአቡነ
መንፈስ ቅዱስ የቃል ኪዳ
ት ለረጅም ዓመታት ተቀ
ከነበረበት ሣጥን አግኝተው
ጵያ እንዲመለስ ጥረት ያደ
የጆን ሉቃስን ቃለ ምልልስ
ኩት:: በእውነት እንዲህ
ስለ ኢትዮጵያውያን ታሪካ
ማኖታዊ ቅርሶች የሚቆረቆ
የውጭ ሀገር ዜጎች መ
አስገርሞኛል:: የሠሩት ሥራ
ነውና ታሪክና የኢትዮጵያ
እስከ ወዲያኛው ሲዘክራቸው
ል:: ወደፊትም በጀመሩት
ም ሥራ እንዲገፉበት
ምኞቴ ነው::

*አፈወርቅ*
*አ*

## ንጉቻስሁ

ዲያቆን ያሬድና አሉላ ጥ
ርዐ ቡሩክ እስከ ጨጎዴ ሐና
የጉዞ ማስታወሻቸው በምዕራ
ሀገረ ስብከት ይልማና ዴን
ስለምትገኘው የደብረ መዊዕ
ገዳም እንዲሁም የዬኔታ
የጨጎዴ ሐና ደብር ቤተ ጉባ
ራረት ታሪክና አጠቃላይ ገጽ
አገላለጽ አስነብበውናል :: ቀ
ል በጉጉት የምጠብቀው ሆኖ
ው ዓመት ቁጥር 1 የቀረበ
በተገቢው መንገድ ባለመቋጨ
አዝኛለሁ:: ይህንንም በቀጣ
ችሁ እንደምትክሱ ተስፋ አደ

*ስሉም*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ትንሣኤው ትንሣኤያችን



*እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሰዎ*

*Happy Easter*

የክርስቶስ ትንሣኤ በትንቢት የተነገረ በምሳሌ የተገለጠ ነው፤ እግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም ከመምጣቱና ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ አንድ ሺህ ዓመት ገደማ የነበረው ነቢዩ ዳዊት «እግዚአብሔር÷ አሁን እነሣለሁ መድኃኒትን አደርጋለሁ በላዩም እገለጣለሁ ይላል፡፡ እግዚአብሔር ይነሣል ጠላቶቹም ይበተናሉ እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ ጠላቶቹንም በኋላው መታ፡፡» መዝ. 67÷1 በማለት ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ እንደሚነሣና ጠላቶቹ አይሁድም በትንሣኤው እንደሚያፍሩ ገልጦ ነበር፡፡

የዮናስ ሦስት ሌሊት በከርሠ አንበሪ አድሮ መውጣት ክርስቶስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ለመነሣቱ ምሳሌ ነው፡፡ ይህንንም ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር እየተመላለሰ ያስተምር በነበረበት ጊዜ «ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሌሊት እንደነበረ እንዲሁ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል፡፡» ማቴ. 12÷40 በማለት የትንሣኤውን ምሳሌ ለደቀ መዛሙርቱ አስረድቷቸዋል፤ የክርስቶስ ሞት የዓለም ሕይወት የክር ስቶስ ሕማም የዓለም ሰላም መሆኑ የተረጋገጠው ከትንሣኤው በኋላ ነው፡፡ ክርስቶስ በሞተና በተቀበረ ጊዜ ተከታዮቹ ሁሉ በጥርጥር በፍርሃትና በድን ጋጤ ወድቀው ነበር፡፡ ትንሣኤውን ባዩ ጊዜ ግን ጥርጥር፤ ፍርሃትና ድን ጋጤ ተወገደላቸው፡፡

ሰው ከሞት በኋላ ሕይወት ያለው ዘላለማዊና ሕያው ሁኖ እንደሚኖር፤ በትንሣኤ ሙታን በሐዲስ ትንሣኤ እንደሚነሣ የተረ ጋገጠው በክርስቶስ ትንሣኤ ነው፡፡ ክርስቶስ የእኛን ባሕርይ ተዋሕዶ በተዋሐደው ሥጋ ከሙታን ተለ ይቶ ተነሣ፡፡ ሙስና መቃብርን አጠፋ፡፡ ታሞ ሞቶ ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖአልና የሞተ በፈቃዱ የተ ነሣም በሥልጣኑ እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ «እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ማንም ከእኔ አይወስዳትም ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላስነሣት ሥልጣን አለኝ፡፡» ዮሐ. 10÷18፡፡ በማለት በፈቃዱ ሞቶ በሥልጣኑ እንደ ሚነሣ ነግሮአቸዋል፡፡

ይህንና የመሳሰለውን ትምህርት እያወጡና እያወረዱ ክርስቶስ እንደ ሞተ ይቀር ይሆን ወይስ እንደተናገረ ይነሣ ይሆን? እያሉ በመጠራጠርና ከአይሁድ ዛቻ የተነሣ በፍርሃት ተውጠው ቤት ዘግተው ሳሉ በዝግ ቤት ገብቶ በመካከላቸው ቆመና ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፤ የተቸነከሩ እጆቹን የተወጋ ጐኑን አሳያቸው፡፡ ደቀ መዛሙርቱም አይተው ትንሣኤውን አመኑ፤ ጥርጥርና ፍርሃት ጠፋላቸው፤ እነርሱ ያዩትንና የሰሙትን ለሌሎች በድፍረት መሰከሩ፡፡ ሉቃ÷24-36፣ 43፣ ዮሐ ÷20-19፡፡

የክርስቶስ ትንሣኤ ለእኛ





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ትንሣኤ በኩር መሆኑንና ክርስቶስ እንደ ተነሣ ሰዎችም ሁሉ እንደሚነሡ ለሌሎች አስተማሩ ።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረ፤ በሦስተኛውም ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም ታየ፤ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ ከዚያም በኋላም ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ... ስለዚህ ክርስቶስ ሳንቀላፉት ሁሉ በኩር ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል። ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና ሁሉ በአዳም እንደ ሞቱ እንዲሁ ደግሞ ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ» በማለት ትንሣኤውንና ትንሣኤ ሙታንን አስተምሮ አል።

የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ሳዊሮስ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከንጽሕት ድንግል የመወለዱ፤ የመሞቱና የትንሣኤው ሥርዓት እኛን ለማዳንና እኛን ወደ እርሱ ለመመለስ ተደረገ።» ሃይማኖተ አበው ክፍል ስድስት። ነፍሱን በሲኦል አልተወም። ሥጋውም እንዲፈርስ እንዲበሰብስ አላደረገም፤ ነፍሱ ከሥጋው በተለየች ጊዜ እግዚአብሔር ቃል በፈቃዱ ይህንን ሠራ። ከተለያዩ ከሁለቱ ከነፍስና ከሥጋ አልተለየም፤ አንድ አካል አንድ ባሕርይ በመሆን ከነፍስና ከሥጋ ጋር ተዋሕዶ ይኖራል። እርሱ እግዚአብሔር በሁሉ የመላ ነው፤ ከቦታም በአንድ ቦታ የሚወሰን አይደለምና። ከሥጋ ጋር ተዋሕዶ መፍረስ መበስበስን አጠፋ። በመቃብር ያሉ ሥጋዎችንም ፈርሰው በስብሰው ከመቅረት አዳነ። ከሞቱ ከጻድቃን በድኖችም ብዙዎቹን አስነሣ።» 1ቆሮ 15፥1–8 ሃይማኖተ አበው ክፍል 3.29–30።

የእግዚአብሔር ወልድ ወደ ያድነን ዘንድ በሥጋ ሞተ ወዳጆቹ ጻድቃንን ትንሣኤ ለክብር ያስነሣቸውና ያጸድቃቸው ዘንድ ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ። «ስለ በደላችን ተሰቀለ፤ ያጸድ ቀንም ዘንድ ተነሣ። እንዲሁ ክርስቶስ በአባቱ ጌትነት እንደ ተነሣ እኛም ተነሥተን በአዲስ ሕይወት ከእርሱ ጋር እንኖራለን» ተብሎ ተጽፎአልና።

❖❖❖

## ከዳግም ትንሣኤ እስከ በዓለ ሃምሳ ያሉ እሑዶች ምንባባትና ቅዳሴያት

1ኛ እሑድ ፡– ትንሣኤ

2ኛ እሑድ

**<u>የዕለቱ መዝሙር</u>** **<u>መነሻ</u>** ፡– ይትፌሣሕ ሰማይ

**<u>ምንባብ</u>** ፡– ግብ.ሐዋ.2፥25–31

**<u>ምስባክ</u>** ፡– ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፌሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ፥አ እግዚአ አድኅንሶ

**<u>ትርጉሙ</u>** ፡– ይህች ዕለት እግዚአብሔር ሥራውን የሠራባት ናት፤ በእርሷ ፈጽሞ ደስ ይበለን፤ አቤቱ አድነን። መዝ.117፥24

**<u>ወንጌል</u>** ፡– ዮሐ.2፥19–31

**<u>ቅዳሴ</u>**፡– ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ

3ኛ እሑድ

ጌታ ለሐዋርያት በባሕረ ጥብርያዶስ የተገለጠበት

**<u>የዕለቱ መዝሙር ርዕስ/ መነሻ</u>** ፡– ወበእሑድ ሰንበት

**<u>ምንባብ</u>** ፡– ሐዋ.5፥30–33።

**<u>ምስባክ</u>** ፡– ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚአብሔር እሬሲ መድኃኒተ ወአግህድ ቦቱ ቃለ እግዚአብሔር ቃል ንጹሕ

**<u>ትርጉም</u>** ፡– እግዚአብሔር አሁን እነሣለሁ አለ፤ ድኅነቴን አደርጋለሁ እገልጽበታለሁ፤ የእግዚአብሔር ቃል ንጹሕ ነው። መዝ.11፥5–6።

**<u>ወንጌል</u>** ፡– ዮሐ.1፥11–18

**<u>ቅዳሴ</u>** ፡– ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ

4ኛ እሑድ

**<u>የዕለቱ መዝሙር መነሻ</u>** ፡– ተንሥአ ወአንሥአ ኵሎ ሙታነ

**<u>ምንባብ</u>** ፡– ሐዋ.4፥10–12

**<u>ምስባክ</u>** ፡– አንሰ ሰከብኩ ኖምኩ ወተንሣእኩ እስመ እግዚአብሔር አንሥአኒ ኢይፈርህ እምአዕላፍ አሕዛብ

**<u>ትርጉም</u>** ፡– እኔስ ተኛሁ አንቀላፋሁም፤ እግዚአብሔር ደግፎኛልና ተነሣሁ። ከአእላፍ ሕዝብ አልፈራም። መዝ.3፥5።

**<u>ወንጌል</u>** ፡– ሉቃ.24፥33–40

**<u>ቅዳሴ</u>** ፡– ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ

5ኛ እሑድ

የዕለቱ መዝሙር ርዕስ/መነሻ ፡– ፋሲካ

**<u>ምንባብ</u>** ፡– ሐዋ.13፥27–36

**<u>ምስባክ</u>** ፡– ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረው ፀሩ ወይጉየዩ ጸላዕቱ እምቅድመ ገጹ ከመ የኃልቅ ጢስ ከማሁ የኃልቁ

**<u>ትርጉም</u>** ፡– እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ፤ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሽሹ፤ ጢስ እንደሚበተን እንዲሁ ይብነኑ /መዝ.67፥1/

**<u>ወንጌል</u>** ፡– ሉቃ.24፥40–47

**<u>ቅዳሴ</u>** ፡– ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ

6ኛ እሑድ

**<u>የዕለቱ መዝሙር ርዕስ መነሻ</u>** ፡– አርአየ ሥልጣኖ ላዕለ ሞት

**<u>ምንባብ</u>** ፡– ሐዋ.13፥32–34

**<u>ምስባክ</u>**፡– ንግሩ ለእግዚአብሔር ምሕረቶ ወመንክሮሂ ለእጓለ እመሕያው እስመ ሰበረ ኖኃተ ብርት

**<u>ትርጉም</u>**፡– የእግዚአብሔርን ቸርነት ንገሩ አስተምሩ፤ ተአምራቱንም ለሰው ልጆች የነሐሱን መስኮት ሰብሯልና። መዝ.107፥8–9

**<u>ወንጌል</u>** ፡– ማር.16፥ 9–16

**<u>ቅዳሴ</u>** ፡– ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ

7ኛ እሑድ

**<u>የዕለቱ መዝሙር መነሻ</u>** ፡– በሰንበት ዐረገ ሐመረ

**<u>ምንባብ</u>** ፡– ሐዋ.1፥9–12

**<u>ምስባክ</u>** ፡– ዘምሩ ለእግዚአብሔር ዘዐርገ ውስተ ሰማየ ሰማይ ዘመንገለ ጽባሕ ናሁ ይሁብ ቃሎ ቃለ ኃይል

**<u>ትርጉም</u>** ፡– ወደ ሰማይ ያረገ እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ በስተምሥራቅ ባለው ሰማይ ዐረገ፤ እነሆ የኃይል ቃል ቃሉን ይሰጣል። /መዝ.67፥32–33/

**<u>ወንጌል</u>** ፡– ሉቃ. 24፥45–53/

**<u>ቅዳሴ</u>** ፡– ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ

8ኛ እሑድ የጰራቅሊጦስ በዓል የሚውልበት ነው

**<u>የዕለቱ መዝሙር ርዕስ/መነሻ</u>** ፡– ይትፌሣሕ ሰማይ

**<u>ምንባብ</u>** ፡– ምስባክና ወንጌል የቅዳሴውም ሥርዓት ሁሉ በትንሣኤ የመጀመሪያ እሑድ ላይ እንዳለው ነው።

ምንጭ፡– መጽሐፈ ግጻዌ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ጸሎተ ሃይማኖት

*በዚህ እትም ካለፈው በመቀጠል በያዝ ነው ዐቢይ ርዕስ ሥር አንዳንድ ነጥቦችን እናነሳለን:: ባለፈው እትም «ሞተ÷ ወተቀብረ፤ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት የሚለውን አንቀጽ መተንተናችን ይታወሳል::*

«በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት፣ ወነበረ በየማነ አቡሁ፣ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ:: በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ:: በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ በምስጋና ይመጣል፤»

## ዕርገት

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሞትን ድል ነሥቶ በተነሣ በአርባኛው ቀን ደቀ መዛሙርቱን እስከ ቢታኒያ አወጣቸው:: ቢታኒያ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ አምስት ኪ.ሜ ርቆ ከደብረ ዘይት ወዲያ የሚገኝ መንደር ነው:: ከዮርዳኖስም በስተ ምሥራቅ ነው:: ከገላትያ ደግሞ በስተ ሰሜን ነው:: የማርያም የማርታና የአልዓዛር የለምጻሙ የስምዖንም መኖርያ በዚያ ነበር:: ማቴ.26÷6፣ ዮሐ.11÷1::

ጌታችን ወደ ቢታንያ ያወጣቸውን ደቀ መዛሙርቱን እጆቹን አንሥቶ ባረካቸው:: በዚህም እስከ ፓትርያርክነት ድረስ ያለውን ማዕርግ ሾማቸው:: ከዚህ በኋላ የርቀት /የመርቀቅ/ ያይደለ የርኅቀት /የመራቅ/ ተሠውሯቸው ወደ ሰማይ ዐረገ:: እነርሱም ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፣ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ /እያገለገሉ/ በመቅደስ ኖሩ:: ሉቃ.24÷50–53:: ቅዱስ ሉቃስ የዕርገቱን ነገር በግብረ ሐዋርያት መጽሐፉም ላይ ጠቅሶታል:: «ወእንዘ ጉቡአን እሙንቱ ተስእልዎ ወይቤልዎ እግዚኦ:: በዝኑ መዋዕል ታገብእ መንግሥተ ለደቂቀ እስራኤልን እነርሱ በተሰበሰቡ ጊዜ ጌታ ሆይ÷በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለ ው ጠየቁት:: ይኸውም «አቤቱ በዘሩባቤል የሄደችውን መንግሥት ለእስራኤል ልጆች የምትመልሰው መቼ ነው? አንድም በአዳም ስሕተት የሄደችውን ልጅነት የምትመልሰው መቼ ነው?» ሲሉት ነው:: እርሱም »አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ /ሰማያዊ ሀብትን ሰማያዊ ዕውቀትን ገንዘብ ታደርጋላችሁ/፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ /በአራቱ መዓዘን/ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ::» አላቸው:: ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሠውራ ተቀበለችው:: ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፣ እነሆ÷ ነጫጭ /ብሩህ/ ልብስ የለበሱ ሁለት ቅዱሳን መላእክት በሰው አምሳል ተገልጠው በአጠገባቸው ቆሙ:: ብሩህ ልብስ መልበሳቸውም «ድኅነተ ዓለም በመፈጸሙ ከእንግዲህ ወዲያ ዘመኑ የደስታ ዘመን ነው፤» ሲሉ ነው:: ደግሞም «የገሊላ ሰዎች ሆይ÷ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ክርስቶስ በብርሃን በሥልጣን በቅዳሴ ሲያርግ እንዳያ ችሁት ዳግመኛ በብርሃን በሥልጣን በቅዳሴ ሲመጣ ታዩታላችሁ:: አንድም በጥበበ ትስብእት /የለበሰውን ሥጋ እንደ ተዋሐደ/ ሲያርግ እንዳያችሁት ዳግመኛ በክበበ ትስብእት ይመጣል::» አሏአቸው::

የጌታችን ዕርገቱ በነቢያት አስቀድሞ የተነገረ ነው:: እግዚአብሔር የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጉልቶ ስለ ገለጠላቸው:: ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት–«እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ /በይባቤ መላእክት፣ በቅዳሴ፣ በብርሃን፣ በሥልጣን/ ዐረገ::» ብሏል:: መዝ.46÷5:: ዳግመኛም «ወደ ላይ ዐርገህ ምርኮን ማረክህ፣ /ነፍሳትን ይዘህ ማርከህ ከሲኦል ወደ ገነት ወጣህ ዐረግህ/፤» ብሏል:: መዝ.67÷18:: ሦስተኛም «በምሥራቅ በኩል ወደ ሰማየ ሰማያት /ወደ ጽርሐ አርያም/ ለወጣ /ላረገ/ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤» በማለት የዕርገቱን ነገር አስቀድሞ ተናግሯል:: መዝ. 67÷33:: ከዚህም ጋር «እግዚአብሔር ዐረገ፤» በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት መስክሯል::

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአምላካዊ ኃይሉና ሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጐ እንደተነሣ ሥጋን እንደ ተዋሐደ ወደ ሰማይ የወጣው በኃይሉና በሥልጣኑ ነው:: የአዳም ሰባተኛ ትውልድ ሄኖክ ያረገው በራሱ ኃይል ሳይሆን እግዚአብሔር ወስዶት ነው:: ዘፍ.5÷24:: ነቢዩ ኤልያስም በእሳት ሠረገላ ያረገው በራሱ ኃይል ሳይሆን እግዚአብሔር ወስዶት ነው:: 2ኛነገ.2÷11:: እኛንም በትንሣኤ ዘጉባኤ ነፍሳችንን ከሥጋችን አዋሕዶ፣ ትንሣኤ ዘለክብር አሥንስቶ፣ ወደ ሰማይ እንደሚያሳርገን እናምናለን:: ይኸንንም ራሱ ባለቤቱ «እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ በማለት እውነተኛ ተስፋ ሰጥቶናል:: ዮሐ.14÷3:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፣» ያለው ለዚህ ነው:: ፊል.3÷2:: ዳግመኛም በተሰሎንቄ መልእክቱ «በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁል ጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን:: ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ::» ብሏል:: 1ኛ.ተሰ.4÷16::

## በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ፤

ከሦስቱ አካላት አንዱ የሆነው ወልድ ከሰማይ ወረደ ተወለደ ስንል በተለየ አካሉ ነው:: በመለኰት ግን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አልተለየም:: ይኸንንም ኢትዮጵያዊው የሥነ ጹሑ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ፍና የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱ «በዚህም ዓለም ኪሩቤልና ሱራፌል በሰማያት ካለው ምስጋናቸው ወይም ከቀድሞ ምስጋናቸው ወገን ባልሆነ በሌላ ምስጋና አመሰገኑሽ፤ ፍጥረትን ሁሉ ሰብስቦ የያዘና ፍጥረቱን ሁሉ የሚመግብ ጌታቸው በእቅፍሽ ተቀምጦ ጡትሽን እንደ ሕፃን ሲጠባ ባዩ ጊዜ በአርያም ፈለጉና በዚያ ዓለም እንደቀድሞው ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አገኙት፤ የጌታ ትኅትናውን ባዩ ጊዜም ዓይኖቻቸውን ወደ ላይ ወደ አርያም ከፍ ከፍ አደረጉ፤ ክንፋቸውንም ዘርግተው ለሁሉ ጌታ ለአንተ በሰማይ ምስጋና ይገባሃል እያሉ ጌታቸውን አመሰገኑ:: ዳግመኛም በዋሻ በጐል ውስጥ አንቺን ከሕፃንሽ ጋር አይተው በምድር ላይ ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነት ሆነ አሉ:: ካንቺ የነሣውን የኛን ሥጋ ለብሶ /ሰው ሆኖ/ ባዩት ጊዜም ሰውን ምንኛ ወደደው ብለው ሰገዱለት::» በማለት «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጐ ፈቃድ» የሚለውን የመላእክት መዝሙር ተርጉሞታል:: ሉቃ.2÷14 :: በወንጌልም ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኰት በህልውና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አለመለየቱን ሲናገር «እኔና አብ አንድ ነን፤... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤» ብሏል:: ዮሐ.10÷30፣ 14÷ 11::

እንግዲህ በተዋሕዶ ሰው የሆነው አምላካችን ወደ ሰማይ ወጣ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ የምንለው በተለየ አካሉ ስለ ተዋሐደው ሥጋ ነው:: በተዋሕዶ አምላክ ሰው እንደሆነ ሁሉ ሰውም አምላክ በመሆኑ ያ አምላክ የሆነ ሥጋ በዕርገት ወደ ሰማይ ወጥቶ በአብ ቀኝ የሚቀመጥ ሆነ:: ይህም ትስብእት በተዋሕዶ ያገኘውን ክብር፣ አንድም መለኰት በተዋሕዶ የሥጋን ገንዘብ – ገንዘብ አድርጐ እንደ ተራበ እንደ ተጠማ ሁሉ ሥጋም በተዋሕዶ የመለኰትን ገንዘብ – ገንዘብ አድርጐ ከሰማያት ዙፋን መቀመጡን የሚያመለክተው ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት በጠቅላላ የሚመሰክሩት ይኼንኑ ነው::

«ነገር ግን እላችኋለሁ፣ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ /ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ/ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ ታያላችሁ» ማቴ.26÷64

«ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእነርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ::» ማር. 16÷19::

«እነሆ፣ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም /ወልድ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ/ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ::» የሐዋ.7÷56::

«ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ::» ዕብ.1÷3::

«እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦ አልና::» ዕብ.12÷2::

«ጌታ /አብ/ ጌታዬን /ወልድን/ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው::» ማቴ.22÷44፣ መዝ. 109÷1:: ይላል::

ለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ በመተባበር «ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ ተቀመጠ፤» ሲሉ ምን ማለ ታቸው ነው? ምክንያቱም ቅዱስ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ድርሰቱ «በመለኮት ላይና ታች፣ ፊትና ኋላ ግራና ቀኝ የለውም በሁሉ የመላ ነው እንጂ፤» ብሏልና::

በመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር ቀኝ እጅ ብዙ ነገሮችን ያመለክታል:: ለምሳሌ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች:: የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች::» ብሏል:: መዝ. 117÷15–17:: ነቢዩ ፣ የእግዚአብሔር ቀኝ ያለው የእግዚአብሔርን ሥልጣን ነው:: በዚህ መሠረት «ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ ተቀመጠ፤» ማለት «በሥልጣን አንድ ናቸው፤» ማለት ነው:: ዳግመኛም «በቀኝህ አድን፣ አድምጠኝም::» ብሏል:: መዝ. 59÷5:: ይህም «በሥልጣንህ አድነኝ፤» ማለት ነው:: በኦሪት ዘጸአት ደግሞ «አቤቱ ቀኝህ በኃይል ከበረ፤ አቤቱ ቀኝህ ጠላቱን አደቀቀ::» የሚል አለ:: ዘጸ.15÷6:: ይህም ኃይልን የሚያመለክት ነው:: ይኸውም «በቀኝ ተቀመጠ» የተባለ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃያል አምላክ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

## ዳግም ምጽአት

በይባቤ፣ በቅዳሴ፣ በኃይል፣ በሥልጣን ወደ ሰማይ ያረገ በአባቱም ቀኝ የተቀመጠ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ /ለጻድቃን ሊፈርድላቸው ኃጥአን ሊፈርድባቸው/ ዳግመኛ ይመጣል:: የሚመቀጣውም በክበበ ትስብእት ነው:: አመጣጡም እንደ ቀድሞ በትኅትና ሳይሆን በኃይልና በሥልጣን ነው:: ይኸንንም ነቢዩ ዳዊት «የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር ተናገ ረ፣ ከፀሐይም መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ ጠራት ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል:: አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም፤ እሳት በፊቱ ይቃጠላል፣ በዙሪያውም ብዙ ዐውሎ አለ:: በላይ ያለውን ሰማይን ምድርንም በሕዝቡ ለመፍረድ ይጠራል፤ ከእርሱ ጋር ለመሥዋዕት ኪዳን የቆሙትን ቅዱሳኑን ሰብስቡለት:: ሰማያት ጽድቁን ይናገራሉ፣ እግዚአብሔር ፈራጅ ነውና::» በማለት ገልጦታል:: መዝ.49÷1–6:: በወንጌልም «የሰው ልጅንም /ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን/ በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፣ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ :: ... የሰው ልጅ /ወልድ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ/ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፣ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል::» ተብሏል:: ማቴ. 24÷30፣ 25÷31:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በኩሉ «ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና::» ብሏል:: 1ኛ.ተሰ.4÷16:: በአጠቃላይ ነገረ ምጽአትን በተመለከተ በነቢያትም በሐዋርያትም በመላእክትም ብዙ ተነግሯል::

«እነሆ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል፣.....እግዚአብሔርም ይወጣል፣... በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ፤... እግዚአብሔርም ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል:: ዘካ.14÷8::

«የሰው ልጅ /ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ/ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤» ማቴ.16÷27::

«በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፣ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍ ርበታል:: እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ ከሚቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መን ግሥት እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀ ምሱ አንዳንድ አሉ::» ማቴ..16÷27::

«ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ሰማይ ሲሄድ እንዳ ያችሁት እንዲሁ ይመጣል::» የሐዋ.1÷11

«እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ::» ራእ.22÷12::





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## የዳግም ምጽአት ምልክቶችና ኩነቶች

ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ደቀ መዛሙርቱ በጠየቁት ጊዜ የዳግም ምጽአትን ምልክቶች ተናግሯል:: «እኔ ክርስቶስ ነኝ፤ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ:: ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ... ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፣ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል:: ...በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፣ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ:: በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ:: እርስ በርሳ ቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ከዓመፃ ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች» ብሏል:: በተጨማሪም ከመከራው በኋላ ስለሚሆነው ነገር፣ ስለ ሚታየው ምልክት ሲናገር «ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፣ ጨረቃም ብርሃንዋን አት ሰጥም፣ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፣ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ:: በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ:: ... ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ ዕወቁ::» ብሏል:: ማቴ.24:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እን ዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል:: የጌታ ቀን እንደ ሌባ ሆኖ /በድንገት/ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፣ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፣ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል::» በማለት ተናግሯል:: 2ኛ. ጴጥ.3÷9–10:: ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ «አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር /መንግሥተ ሰማያትን/ አየሁ፣ ፊተኛው ሰማይና ምድር አልፈዋልና፣ ባሕርም ወደፊት የለም:: ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ::» ብሏል:: ራእ. 21÷1–2:: በነቢያትም ነቢዩ ዳዊት «አቤቱ፣ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ÷ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው:: እነርሱ ይጠፋሉ፣ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ÷ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፣ ይለወጡማል፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመ ቶችህም ከቶ አያልቁም::» ብሏል:: መዝ. 101÷25–27 በትንቢተ ኢሳይያስም «እነሆ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁና፤ የቀደሙትም አይታሰቡም፣ ወደ ልብም አይገቡም:: ነገር ግን በፈጠርሁት ደስ ይበላችሁ ለዘላለምም ሐሤት አድርጉ፤» የሚል ተጽፏል:: ኢሳ. 65÷17–18::

በአጠቃላይ በዳግም ምጽአት ሙታን ይነሣሉ፤ ኢሳ.26÷19:: ትነሣኤው የጻድቃን ለክብር የኃጥአን ግን ለሐሳር ነው:: ዳን.12÷2:: አቋቋማቸውም የጻድቃን በቀኝ ሲሆን የኃጥአን ግን በግራ ነው:: በመጻሕፍት እንደ ተጻፈ ዋጋቸው ተከፍሎአቸው ጻድቃን ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ፣ ኃጥአን ግን ወደ ገሃነመ እሳት ይወርዳሉ:: ማቴ.25÷32–46፣ ራእ.20÷11–15፣ 21÷8::

## የዳግም ምጽአት ማስጠንቀቂያዎች

«በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ /በሃይማኖት ያሉ ረድኤተ እግዚአብሔርን ጥግ ያድርጉ/ በሠገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ለመውሰድ አይውረድ፣/በጽድቅ ያለ ወደ ኃጢአትም አይመለስ/፣ በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ:: /የመነነም ወደ ዓለም አይመለስ/:: በዚያችም ወራት ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው:: /ኃጢአትን በህሳብ ፀንሰው በቃል ወልደው በግብር ለሚያሳድጉ ወዮታ አለባቸው:: አንድም ደቀ መዛሙርትን በትምህርት ፀንሰው በትምህርት ወልደው በትምህርት ለሚያሳድጉ ወዮላቸው ምክንያቱም መከራ ይጸናባቸዋልና/:: ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ:: /ክረምት ቅጠል እንጂ ፍሬ የለውም:: እናንተም ሃይማኖት ይዛችሁ ፍሬ ምግባር ሳታፈሩ እንዳትወሰዱ ተጠንቀቁ:: ሰንበትም የዕረፍት ቀን ነው:: እናንተም እንደ ሰንበት በመንግሥተ ሰማያት ማረፍ ሲገባችሁ ገሃነም እንዳትወርዱ ተጠንቀቁ::

በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ:– ክርስቶስ ከዚህ አለ፤ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ:: እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ:: እንግዲህ እነሆ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፣ አትውጡ፤ እነሆ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ አትመኑ፤ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደ ሚታይ፣ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤ /ክርስቶስ ሲመጣ ለሁሉ ይታያል/፤ በድን ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ:: /እኔ ክርስቶስ ባለሁበት እናንተ በዚያ ትሰበሰባላችሁ/... ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ::.... ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ:: የሰው ልጅ /ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ/ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና:: ...ያ ክፉ ባሪያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፣ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፣ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግ በታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል::»

*ይቀጥላል*

## ዳክርስ

*ሉቃ.23÷39–43*

ፀሐይ ብርሃኗ ነጥፎ
የበርኖስ ክንብንብ ስታጠልቅ
ጨረቃ በኀዘን ድባብ ተውጣ
በደም አበላ ስትጠመቅ
ዐጽም፣ ቅርበታቸው ጸንቶ
ሙታን ከመቃብር ሲነሡ
ዓለታት በፍርሃት ተንጠው
በድን እከላቸውን ሲኳምሱ
ተፈጥሮ ሥረዓቷ ተዛብቶ
ቀኑ በጽልመት ሲቀየር
ሕይወት በቀኝህ ተሰቅሎ
አጽርሃ መስቀሉን እየሰማህ
ወዳጅህ ልቡ ተነክቶ
አንተን ለድኅነት ሲጠራህ
ታአምርን በዐይኖችህ እያየህ .
ቃሉን በጆሮ እየሰማህ
በመጨረሻዋ ደቂቃ ተጠቅመህ
ሕይወትህን መዋጀት ሲገባህ
ልብህ እንደ አልማዝ ደንጊያ ደድሮ
አንደበትን ለስድብ ማሾል
ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው ይኼ?!
በበደል ላይ በደል ማከል
ዋ! ምነዋ?! ዳክርስ
የእምነት ቋጥህ ሚጠጠ
ልብህ ባለማመን ረግረግ
በክህደት አረንቋ ተዋጠ::

*ስንታየሁ ዓለማየሁ*
*አማኑኤል ካቴድራል*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አዋልድ መጻሕፍት

ዲ.ዳንኤል ክብረት

*/የመጨረሻ ክፍል/*

*ባለፈው እትማችን አዋልድ መጻሕፍት ከቅዱሳት መጻሕፍትነት ሊቆጠሩ የሚችሉባቸውን ሁለት መመዘ ኛዎች ተመልክተን ነበር:: የአዋልድ መጻሕፍት ጸሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ ቃኘነት፣ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመግለጥ የጻፉ በመሆናቸው መጻሕፎቻቸው ከሌሎች ተለይተው ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚባሉ፤ በሌላም በኩል አሥራው መጻሕፍት ቅዱሳት ተብለው የተመረጡት በቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍት ቀኖና መሠረት እንደሆነው ሁሉ አዋልድ መጻሕፍትም ቤተ ክርስቲያን በቀኖናዋ እስከ ተቀበለቻቸው ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍት ተብለው እንደሚጠሩ ተመልክተናል::*

በዚህ እትም ደግሞ ሁለቱን ቀሪ ነጥቦች እንመለከታለን::

## ሐ. <u>በዐውዳቸው</u> /Contextual Authenticity/

ቤተ ክርስቲያን አሥራው መጻሕፍትን፤

1. የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት መሠረት አድርጋ ማለትም ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ያገኘችውን ትምህርትና የእነርሱንም ማረጋገጫ በመቀበል፣

2. ከመሠረታዊው የቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት ጋር ያላቸውን አንድነት በመመልከት በቀኖናዋ ተቀብላቸዋለች:: ከዚህ በኋላ ደግሞ አዋልድ መጻሕፍትን በይዘታቸው፣ በዓላማቸውና በአቀራረባቸው ከአሥራው መጻሕፍት ጋር ያላቸውን ኅብረትና አንድነት በመመርመር ትቀበላቸዋለች:: ቤተ ክርስቲያን በተቀበለቻቸው አዋልድ መጻሕፍትና በአሥራው መጻሕፍት መካከል ያለውን የይዘት አንድነት ከሚያሳዩ ማስረጃዎች ጥቂቱን ቀጥለን እንጠቅሳለን::

1. ***የእግዚአብሔርን ሥራ መግለጥ:-*** የቅዱሳት መጻሕፍት ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን ሥራ መግለጥ ነው:: እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያደረገውን ተአምር፣ መግቦቱን፣ ቸርነቱን፣ በሰዎች ላይ አድሮ የሚሠራውን ሊረዳ በሚችል መልኩ ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊው ያብራራሉ:: በዚህም የተነሣ ስለራሳቸውም ሆነ ተአምሩ ስለተፈጸመለት/በት ሰውም ሆነ ቦታ እምብዛም ትኩረት አይሰጡም:: ይህን ትኩረት የሚሰጡት የቦታው ወይም የሰውየው መታወቅ ዓላማቸውን አጉልቶ የሚያስረዳ ከሆነ ብቻ ነው::

ለምሳሌ:- በማቴ.26÷18 ጌታችን «ወደ ከተማ ከእገሌ ዘንድ ሂዳችሁ-መምህር ጊዜዬ ቀርቧል ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ከአንተ ዘንድ ፋሲካን አደርጋለሁ ይላል በሉት» ሲል ደቀ መዛሙርቱን ልኳቸዋል:: ማእምረ ኅቡዓት ኢየሱስ ክርስቶስ «እገሌ» ብሎ መጥራቱ በቤቱ የሚስተናገደውን ሰውስም ባለማወቁ አይደለም፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ልማድ መሠረት የጌታችን በሰውየው ቤት መገኘት ሰውየው ጌታን በእን ግድነት ተቀበለ ከሚለው የበለጠ በመሆኑ ለጌታችን ትኅትና ጸሐፊው ትኩረት በመስጠቱ ነው እንጂ:: በዚህም ምክንያት የተጸ ውዖ ስማቸውን የማናውቃቸው የአያሌ ሰዎች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል:: ለምሳሌ:-

–1ነገሥት 13÷1–እነሆም አንድ <u>የእግዚአብሔር ሰው</u> በእግዚአብሔር ቃል ከይሁዳ ወደ ቤቴል መጣ::

–ማቴ. 8÷2–እነሆም <u>ለምጻም ቀረበ</u> ጌታ ሆይ÷ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ ሰገደለት

– ሉቃ.11÷45 – <u>ከሕግ ዐዋቂዎች አንዱ</u>

– የሐዋ.16÷17 – <u>አንዲት ገረድ</u> አገኘችን

በአዋልድ መጻሕፍትም ተመሳሳይ የሆነ ነገር እንመለከታለን:: በተአምረ ማርያም፣ በገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስና በገድለ ተክለ ሃይማኖት «እገሌ፣ እገሊት፣ አንዲት ሴት፣ አንድ ሰው፣ አንድ ሀገር» እየተባሉ የተጠሩ ሰዎችና ቦታዎች ሁሉ የየራሳቸው የተጸውዖ ስም ነበራቸው:: ነገር ግን የጸሐፊው ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ መግለጥ በመሆኑ አላነሣቸውም::

2. **ለሰው ኅሊና የሚከብዱ ነገር ግን በእምነት የሚረዱ ድር ጊቶችን መግለጥ:-** በአሥራው መጻሕፍትና በአዋልድ መጻሕፍት መካከል ከምናገኛቸው የይዘት ተመሳሳ ይነቶች አንዱ ይኸ ነው:: የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እስከሆነ ድረስ የሰው ኅሊና ቢቀበለውም ባይቀበለውም አስደናቂ እውነታዎችን ይገ[illegible]ጣሉ:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እ[illegible]ነት ተስፋ ስለ ምናደርገው ነገር የ[illegible] ያስረግጥ፣ የማናየውን ነገር የሚያስረ[illegible] ነው» እን ዳለው /ዕብ.11÷1/ ቅዱሳ[illegible] መጻሕፍት የሚመረመሩት በእምነ[illegible] ነው:: የታሪክ፣ የአርኬዎሎጂና ሌሎ[illegible] ምርምሮች ዋና ሳይሆኑ የእምነት መ[illegible] ገፊያዎች ናቸው::

ለምሳሌ:- መስፍኑ ኢያሱ እ[illegible] ራኤልን እየመራ አምስቱን የገባዖን [illegible] ሥታት በወጋ ጊዜ መሸ:: ኢያሱ[illegible] ፀሐይን ገዝቶ አቆማት /ኢያ[illegible] 10÷12–14/:: ይህ ነገር በዘመናዊ[illegible] የጠፈር ሳይንስ ዓይን ሲታይ ለኅለ[illegible]





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ይከብዳል:: ለሚያምን ግን ሁሉ ይቻላል /ማር. 9÷23/:: በተመሳሳይም ከገድላቸው እንደምናነበው አቡነ ዜና ማርቆስና አቡነ አሮን ዘመቄት ፀሐይን እየገዙ አቁመዋታል::

2ነገሥት 13÷20 የኤልሳዕ ዐጽም ሙት አስነሥቷል:: በአዋልድ መጻሕፍትም በልዩ ልዩ ሥፍራ ዐጽመ ቅዱሳንን ነክተው የተፈወሱ ከሙታንም የተነሡ አሉ::

ዳን.6÷16 – ነቢዩ ዳንኤል በአንበሶች ጉዳጓድ በተጣለ ጊዜ አንበሶች አልበሉትም:: ምክንያቱም መልአኩ የአንበሶችን አፍ ዘግቶ ነበርና:: ከአራዊት ጋር ያውም አስቀድመው ሳይላመዱ መዋል ማደር አይቻልም:: ነገር ግን ቅዱሳን አድርገውታል:: አቡነ ሳሙኤል ዘዋጠልድባም በአንበሳ ላይ ተቀምጠው ተዘዋውረው አስተምረዋል:: አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከአናብስትና አናምርት ጋር ኑረዋል::

3. **የእምነትን ታላቅነት መግለጥ**:– ቅዱሳት መጻሕፍት በእምነት፣ ስለ እምነት ለእምነት የተጻፉ መጻሕፍት ናቸው፡ ለመረዳትም ሆነ የተናገሩትን ያዘዙትን ለመፈጸም በእምነት መኖር ያስጠፈልጋል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፣ ጽድቅን አደረጉ፣ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ፣ የአንበሳን አፍ ዘጉ፣ የእሳትን ኃይል አፉ፣ ከሰይፍ እሳት አመለጡ፣ ከድካማቸው በረቱ፣ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፣ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ /ዕብራ. 11÷33–34/:: በማለት እንደገለጠው በአዋልድ መጻሕፍትም ሐዋርያትና ሰማዕታት በእምነት ነገሥታትን ድል ነሥተው ከሞቱበት ሲነሡ እናያለን፡ እነ ቅዱስ ጊዮርጊስ ተፈጭተው ዐመድ ከሆኑ በኋላ ይነሣሉ፤ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ሂድ ብትሉት ይሄዳል በተባለው መሠረት /ማቴ.17÷20/ እነ ስምዖን ጫማ ሰፊው በተአምረ ማርያም ተራራውን አስነሥተው አሰግደውታል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አስቀድሞ በእምነት በባሕረ ገሊላ ላይ በእግሩ ተጉዞ ነበር:: በኋላ በተጠራጠረ ጊዜ ሰመጠ:: ጌታችንም ስለ እምነቱ ጉድለት ገሠጸው:: /ማቴ.14÷28/:: አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ከፋሌ ባሕርም በአጽፋቸው ደቀ መዛሙርትን አሳፍረው ባሕረ ገሊላን ተሻግረውታል::

«በኔ ያመኑ እባቦችን ይይዛሉ /ይገዛሉ/» /ማር.16÷17/ በተባለው መሠረት አቡነ አረጋዊ ዘንዶውን ገዝተው በዘንዶው ጭራ ወደ ደብረ ዳሞ ወጥተዋል:: «የሚገድል ነገር ቢጠጡ አይጐዳቸውም» /ማር.16÷18/ እንደ ተባለውም ቅዱስ ጊዮርጊስ የተሰጠውን መርዝ አማትቦ ቢጠጣው ሞትን ቀርቶ ሕማምን አላመጣበትም:: እነ ሙሴና ኢያሱ በእምነት ነገሥታትን ድል እንደነሡ ሁሉ እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በእምነት ሞተለሚን ድል ነሥተዋል::

4. **በእግዚአብሔር ያመኑ ሰዎች ያደረጉትን ተጋድሎ መግለጥ** :–

እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሁ አይሠራም:: ትዕግሥተኛው ኢዮብ «እግዚአብሔር በአንድም በሌላም መንገድ ይናገራል፡ ሰው ግን አያስተውለውም» እንዳለ /ኢዮብ 33÷14/ እግዚአብሔር ሥራውን በልዩ ልዩ መንገድ ይሠራል:: ከነዚሁም አንዱና ዋነኛው ልዩ ልዩ ቅዱሳንን አሥነስቶ በእምነታቸው ጽናት፣ በገድላቸው ብርታት፣ የሚሠራው ድንቅ ሥራ ነው:: በዚህም መሠረት በአሥራው መጻሕፍት ውስጥ የብዙ ቅዱሳን ገድል ተጽፎ ይገኛል:: ለምሳሌ:–

| | |
|---|---|
| በመጽሐፈ ሩት | – የሩት |
| በመጽሐፈ ነህምያ | – የነህምያ |
| በመጽሐፈ አስቴር | – የአስቴር |
| በመጽሐፈ ዮዲት | – የዮዲት |
| በመጽሐፈ ጦቢት | – የጦቢት |
| በትንቢተ ዳንኤል | – የዳንኤልና የሠለስቱ ደቂቅ |
| በሐዋርያት ሥራ | – የቅዱሳን ሐዋርያት በተለይም የጴጥሮስ በስፋት ደግሞ የቅዱስ ጳውሎስ ገድላት ተጽፈዋል:: |

በአዋልድ መጻሕፍትም «በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ይሠራል» ከዚህም በላይ ይሠራል /ዮሐ.14÷12/ በተባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ገድል የፈጸሙ ቅዱሳን ታሪክ ተተንትኖ ተጽፏል::

5. **ትምህርተ ሃይማኖትን ማስተማር**:– የቅዱሳት መጻሕፍት ሌላው ዋነኛ ዓላማ የሃይማኖት ትምህርትን ማስተማር ነው:: የአራት መጻሕፍት፣ አርባዕቱ ወንጌል፣ የሐዋርያት መልእክታት ዋና ትኩረት ነገረ ሃይማኖትን ተንትኖ ማስረዳት ነው:: ከአዋልድ መጻሕፍትም አምስቱን አዕማደ ምሥጢር፣ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ፣ ነገረ ማርያምን፣ ነገረ መላእክትን፣ ነገረ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሕግጋትንና ትእዛዛትን፣ ምክርንና ተግሣጽን፣ ሥነ ምግባርንና መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያስተምሩ መጻሕፍትን እናገኛለን::

ለምሳሌ:– ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአራት ዘፍጥረት ምዕራፍ 16 የተጻፈውን የሣራና የአጋርን ታሪክ በአንድምታ ተርጉሞና አብራርቶ በገላ. 4÷21–31 አስቀምጦታል:: አጋር የምድራዊቷ ኢየሩሳሌም ሣራ የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም፤ የሣራ ልጅ የክርስቲያኖች የአጋር ልጅ የአይሁድ ምሳሌ ሆነው ተተርጉመዋል::

በ1ቆሮ.10÷4 የእሥራኤል በኤርትራ ባሕር መሻገር የጥምቀት፣ ውኃ ፈልቆ የጠጡበትን ዐለት የክርስቶስ ምሳሌ አድርጐ ተርጉሞታል:: አዋልድ መጻሕፍትም ይህን የትርጓሜ መሠረት ይዘው በአሥራው መጻሕፍት የተጻፉ ታሪኮችን፣ ትምህርቶችን፣ ምሥጢራትን ተርጉመው፣ አፍታተው ያቀርባሉ:: ይህንንም አበው እንዲህ ይመስሉታል:: የበሬ ነጋዴ በሬውን ለገበያ ያቀርባል:: ባለ ልኳንዳዎች ገዝተው በብልት በብልቱ ያቀርቡታል:: የሥራ ቤቶች ደግሞ በየዓይነቱ ለይተው በምግብነት ያቀርቡታል:: እንደዚሁም እግዚአብሔር የገለጠላቸ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ውን ዕውቀት ነብያትና ሐዋ ርያት አሪት፣ ትንቢት፣ ታሪክ፣ ቅኔ፣ ወንጌል፣ መልእክት ብለው በብልት በብልቱ አስቀምጠውታል:: ነገር ግን የሥጋ ብልቱ ስለወጣለት ብቻ ሊበላ አይችልም:: ስለሆነም ባሥራ ቤቶች የሚመስሉ ሊቃውንት አምስቱ አዕማደ ምሥጢር፣ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ታሪክ፣ ተግሣጽ፣ ምክር፣ ሥርዓት፣ ጸሎት ብለው ለምእመናን ምግብ እንዲሆን አድርገውታል::

እንግዲህ እነዚህንና ሌሎችንም የይዘት ማስረጃዎች ብንመለከት አዋልድ መጻሕፍትን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እንዲመደቡ ያደርጓቸዋል::

## መ. በዶግማቸው

## /Dogmatic Authenticity/

አዋልድ መጻሕፍትን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያደርጋቸው በመሠረተ እምነት ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር የማይጋጩ ስለሆኑና ሲሆኑም ነው:: ዋና ዋና የሚባሉት የቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነትም:-

- በጸሎተ ሃይማኖት የተገለጡት
- በሃይማኖተ አበው መጽሐፍ የተገለጡት
- በልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት የጸደቁትና ሌሌችም ናቸው::

አምስቱን አዕማደ ምሥጢራት፣ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ የቅዱሳን አማላጅነት፣ እግዚአብሔር ሥራውን በልዩ ልዩ መንገድና ሁኔታ /በጠበል፣ በዕመት፣.../ መሥራቱን፣ ህልዎተ እግዚአብሔርን፣ መግቦተ እግዚአብሔርን፣ የእምነትና የምግባርን አስፈላጊነት የሚገልጡ፣ የሚያረጋግጡና ከነዚህም ጋር በቃልም ሆነ በምሥጢር ተፋልሶ ያላገኛቸው መሆን አለባቸው:: ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያናችን የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የሥነ ፈለክ ወዘተ መጻሕፍት ይገኛሉ:: ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች የተተረጐሙ ከክር ስትና አስተምህሮ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ነገር ግን ለሌላ ጥናት የሚጠቅሙ መዛግብትም አሉ:: ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን የባሕልና የቅርስ ማዕከል በመሆንዋ እነዚህን መጻሕፍት ጠብቃ ብታቆይም መጻሕፍቱ ከመሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር ስለ ማይገናኙ ቅዱሳት መጻሕፍት ተብለው አይጠሩም:: ለዚህም አንጋረ ፈላስፋ፣ መጽሐፈ ፈላስፋ፣ እና በርለዓም የተሰኙ መጻሕፍትን መጥቀስ ይቻላል:: አንጋረ ፈላስፋ እና መጽሐፈ ፈላስፋ የጥንት ግሪካውያንን ፍልስፍና የያዙ ሲሆን፣ በርለዓም ደግሞ የሕንዳውያንን ልዩ ልዩ ትምህርቶችና ምሳሌዎች የያዘ ነው:: ዛሬ ዛሬ ባለ ማወቅ ወደ ጥንቆላ የዞሩ የሥነ ፈለክ መጻሕፍትም ቁጥራቸው ይህን ከመሰሉት መጻሕፍት ነው::

እንግዲህ በጠቅላላው አዋልድ መጻሕፍት፣ አምላካውያት መጻሕፍት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ናቸው:: አዋልድ መባላቸው አሥራውን መስ ለው ለመውጣታቸው ምሥክር ነው እንጂ «ብጡል» /የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ያልሆኑ/ ናቸው ማለት አይደለም:: የአዋልድ መጻሕፍት መብዛት የእግዚአብሔርን ቸርነት ያሳያል:: ነገር ግን መብዛታቸው ሌሎች «ብጡላንን» /pseudo Hagiographia/ለማስረጽ ስለ ሚያመቾ የኑፋቄ መጻሕፍት እንዳይ ቀላቀሉባቸው እንደ ቀድሞው ሁሉ ማንነታቸው ተለይቶ ዝርዝራቸው ታውቆ በቀኖና መጻሕፍት መገለጥ አለባቸው:: በየዓመቱ የአዋልድ መጻሕፍትን ቀኖና የሚገልጥ የቀኖና መጽሐፍ ቢታተም፣ ዝርዝራቸውና ይዘታቸው ተገልጦ መለያ ቁጥር ቢሰጣቸው፣ ከአዋልድ ውጭ የሆኑትና ለሌላ ትምህርት የሚያገለግሉት ተለይተው ለተጻፉበት ዓላማ ቢውሉ መልካም ነው::

*ተፈጸመ*

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ከዋሸራ እስከ...

ከገጽ 25 የዞረ

ከደብረ ጽላሎ አማኑኤል ተለይተን ትንሽ እንደተጓዝን ሾሬን ስናይ ሠርግ ቤት አለ:: ድንኳን ተጥሏል:: መንገድ መሪያችን በተለመደው አቀራረባቸው ተጠግተው ውኃ ስጡን አሉ:: ከዚያ ግቡ ብለው አስገቡን ከውኃ አልፈው እንጀራም ቀረበና በላን ጠጣን:: የማናውቃቸውን ሙሽሮች መርቀን ልንነሣ ስንል የአካባቢው ጎልማሶች ከበቡን:: «ምንድናችሁ?» አሉን ቤተ ክርስቲያን ልንሳለም መጥተን ነው አልናቸው:: «በሀገራችሁ ቤተ ክርስቲያን የለም?» አሉን:: አለ ስለዚህ ነው የመጣነው በሀገራችን ካሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ አማኑኤል ነው::» አሉላ መለሰ:: «ይሄማ የኛ ሀገር ነው» አሉና ተቆጡ:: «እኛ የዚህና የዚያ ክልል በሚለው አናምንም፤ ኢትዮጵያ በጠቅላላው ሀገራችን እንደሆነች ነው የምናውቀው» አልናቸው:: «ለማንኛውም መታወቂያ» አሉን:: አሳየናቸው:: ይሄ የውሸት ይሆናል እናንተ እንደውም ሌቦች ናችሁ አሉና አቋምጠው የያዙትን ሽመላቸውን ማዘጋጀት ጀመሩ:: «እናንተን መግደልም ይቻላል፤ በአገር መሞት' ኮ ያለ ነው» አሉ:: ጉድ ፈላ፤ ከአንዱ ስና መልጥ ሌላ:: ችግሩ አላልቅ አለ:: እነዚህ ደግሞ ይባስ አብልተው አጠጥተው የሚደበድቡ ናቸው:: ከመካከል አንዱ ሽማግሌ «ተዋቸው ባይሆን ይሂዱ፥ ቶሎ ይውጡ» ሲሉ ሰማን:: ዕቃችንን እየጠቀለልን ሩጫውን ተያያዝነው::

እንግዲህ ምን እንላለን፥ ስለ ደብረ መድኃኒት እገታ ኢየሱስ ገዳም፣ስለ ደብረ እንቁ ወይዛዝርት ኪዳነ ምሕረትና ስለ ጉንጅ ቅዱስ ቴዎድሮስ ጥንታዊ ገዳም እንዳንተርክ ጊዜ ያጥርብናል፤ ቦታም ይጠበናል፤ ባይሆን በሌላ ዝግጅት ብንመለስባቸው ይሻላል:: የጎንጅ ከተማን መሐል ለመሐል ሰንጥቀን የጎንጅ ቴዎድሮስ ገዳም መውረጃ በረሃን ወደ ቀኝ እየተውን ወደ ኮሬ ከተማ በሚያወጣን ጥርጊያ መንገድ ገሥገሥን:: ከቀኑ 10:30 ግድም ኮሬ ከተማ ገባን:: እዚያው ጥቂት ቆይተን ማምሻውን በደረሰልን አይሱዙ የጭነት ከተማ ወደ ማረፊያ ማዕከላችን የአዴት ግብርና ምርምር ጣቢያ ተጓዝን::

ለአካባቢው እንግዳ በመሆናችን የደረሰብንን መዋከብ ከጥበቃና ከፀጥታ ዐይን አንፃር በገንቢነቱ ብንወስደውም የታዘብነው የአውራጃዊነት መንፈስ ግን ሊታሰብበት ይገባል የሚል እምነት አለን::

ቅዳሜና እሑድ አዴት መድኃኔዓለም ላይ ጉባኤ ተደርጎ ከምእመኑ ጋር ከቆየን በኋላ ሰኞ ወደ አዲስ አበባ መልስ ሆነ:: ለ17 ቀናት ቆይታ ያደረግንባት የይልማና ዴንሣ ወረዳ በአጠቃላይ ከ272,550 በላይ ሕዝብ ያላት ሲሆን ከእኒህም ውስጥ 88.5 በመቶው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ናቸው::

*ተፈጸመ*

**እርማት**

*በ10ኛ ዓመት ቁጥር 1 እትማችን «ቅዱስ አትናቴዎስ ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ዓምድ በሚል ርዕስ ባቀረብነው ጽሑፍ ቅዱስ አትናቴዎስ ግንቦት 7 ቀን 347 ዓ.ም. እንዳረፈ የተገለጠው 374 ተብሎ እንዲነበብ ከይቅርታ ጋር እናስታውቃለን::*



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ቄጤማ ለምን እናስራለን?

*በቀዳም ስዑር ዕለት ቀሳውስትና ዲያቆናት በየቤቱ እየዞሩ ቄጤማ ለምእመናን ይሰጣሉ፤ እኛም በራሳችን እናስረዋለን:: ለመሆኑ የዚህ ትውፊታዊ ታሪክና ትርጉም ምንድን ነው?*

*መስ ቀን ማስተዋል*
*አዲስ አበባ*

ለዚህ ጥያቄ መልስ የምንሰጠው ከነፌ ርግብ ማርቆስ የተባሉ ጸሐፊ በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ የሚያዚያ ወር 1970 ዓ.ም. እትም ካቀረቡት ጽሑፍ በመነሣት ነው::

ቄጤማ በራስ ላይ ማሰር ሰፊ ትርጉምና መንፈሳዊ ባሕልን የያዘ ታላቅ ምሳሌ ነው፤ ይኸውም በመንፈሳዊ ዓለም ቀርቶ በሥጋዊ ዓለምም ሕዝቡ የሚጠቀምበት መሆኑ የታወቀ ነው::

የምሥራች የሰጠ ሰው ምን ያህል ሽልማት እንደሚያገኝ በሁላችንም ዘንድ ከታወቀ ይኸም በቀዳም ስዑር ቀን የምናሥረው ቄጤማ እንዲያው በከንቱ የመጣ ልማድ ወይም ሰው ያለ ቦታው ያስገባነው ባሕል አይ ደለም::

የሰው ልጅ በሠራው ኃጢአትና በፈጸመው በደል ፈጣሪውን አሳዘነ እግዚአብሔርንም አስቀየመ:: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አዝኖ አልቀረም፤ ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በጠቅላላ በዓለም የሚገኘው የሕይወት እስትንፋስ ያለው ሥጋዊ ደማዊ ፍጡርን ሁሉ ከገጸ ምድር ለመደምሰስ ወሰነ:: /ኦ.ዘፍ.7÷5–8/

ፍጥረቱንም ሁሉ ለማጥፋት በወሰነበት ወቅት ትእዛዙን ጠብቆ አምልኮቱ ጸንቶ የነበረውን ኖኅን ከጥፋት ውኃ የምትድንበትን መርከብ ሥራ ሲል ትእዛዙን አስተላለፈለት:: በዚህ ጊዜ ኖኅ በታዘዘው መሠረት መርከብን ሠራ:: የመርከቡን ሥራ ካጠቃለለ በኋላ እንደገና ከተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለዘር የሚሆኑ ወንድና ሴት ወደ መርከቡ እንዲያስገባ ታዘዘ:: የሕይወት እስትንፋስ ካላቸው ፍጡራን ሁሉ ወንድና ሴት እያደረገ በየቡ ድን በየቡድናቸው ወደ መርከብ አስ ገባ:: እሱ ከእነ ሚስቱ ሦስት ልጆቹም ከነሚስቶቻቸው ወደ መርከብ ገቡና መርከቡ ተዘጋ:: ዘፍጥ. 6÷8–22፣7÷1–11::

በዚህ ጊዜ መሬት ተከፈተ ሰማይም ተነደለ:: ከታች ወደ ላይ ውኃ እየፈለቀ ከሰማይም እንደ እሳት የሚያቃጥል ዝናም ሳያቋርጥ 40 ቀን 40 ሌሊት ዘነመ:: ዓለሙ ተጥለቀለቀ:: ወደ መርከቡ ከገቡት በስተቀር የተፈጠሩት ፍጥረታት በሙሉ አለቁ:: /ዘፍጥ.7÷17–23/ ከ40 ቀን በኋላ እግዚአብሔር በመርከቡ ገብተው ያሉትን ፍጥረቶች አሰበ:: ነፋስን አነፈሰ:: ነፋሱ የድርቅ ነፋስ ነበር:: ነፋሱም በነፈሰ ጊዜ ውኃው ጐደለ፣ታላላቅ ኮረብታዎች መታየት ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ ኖኅ ምናልባት ማረፊያ እናገኝ እንደሆነ፣ ውኃው ጐድሎ እንደሆነ፣ አልጐደለም እንደሆነ አይተሽ ነይ» ሲል ርግብን ላካት:: እሷም እንደተላከች ውኃው በጣም ስላልጐደለ የምታርፍበት ቦታ አጥታ ደክማ ተመለሰች:: እንደገና ለአንድ ሳምንት ቆይቶ ሁለተኛ ጊዜ ቢልካት ውኃው ጐድሎ በውኃ ተደ ፍነው የነበሩት ዛፎች ዝቅ ዝቅ ብለ ው ስላገኘች ለምለም የሆነውን የወይራ ቅጠል /ቄጤማ/ በአፏ ይዛ ወደ ኖኅ ተመለሰችና «የምሥራች ሐፀ ማየ አይኅ፣ ነትገ ማየ ኃጢአት፤ የጥፋት ውኃ ጐደለ÷ የኃጢአት ባሕር ደረቀ» ስትል አበሠረችው:: /ኦ. ዘፍጥ.8÷11/::

በዚህ ምክንያት ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አድርጋ ቄጤማውን በራሷ ላይ በማሰር ስትጠቀምበት የምትኖረው:: የተላከችው ርግብ የውኃውን መጉደል ለኖኅ እንዳበሠረችውና በአፏ ቄጤማውን ይዛ 40 ቀን 40 ሌሊት ሲዘንም የሰ ነበተው የጥፋት ውኃ ደረቀ ስትል የምሥራችን እንደነገረችውና ኖኅ የምሥራቹን ሰምቶ እንደተደሰተ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ተዘግቶ የነበረው የገነት በር በክርስቶስ ስቅለት በክርስቶስ መከራና ሞት ተከፈተ:: አምስት ሺ ከአምስት መቶ ዘመናት ከሲያል ባርነት ወደ ዕረፍተ ገነት ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገሩ ስትል እነሆ ለሚከተሏት ምእመናን ለምለም ቄጤማን ይዛ ታበሥራለች:: ቤት ለቤት እየዞረችም «ሞት ጠፋ፣ ኃጢአት ተደመሰሰ፤ አባታችን አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ ልን፤ ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሃደ» እያለች ቄጤማውን ታድላለች:: ምእመናንም ለቤተ ክርስቲያን የሚውል ገጸ በረከት ያቀርባሉ:: ከትንሣኤው በኋላ ገብረ ሰላም የተባለ ግብር ካህናቱ ያገባሉ:: ስለዚህ ነው የርግብን ሰላም ሰላማችን አድርገን ቄጤማውን በራሳችን የምናሥረው:: ቤተ ክርስቲያናችን ከመጽሐፍ የተገኘውን በቸልተኝነት አታልፈውም:: ቄጤማ ልምላሜ የማይለየው በበጋም ሆነ በክረምት የማይደርቅ ቅጠል ነው:: ስለዚህ የበደሉም ሰዎች የሞት ተገዥዎች ሁነው የኖሩበት ዘመን አልፎና በክርስቶስ ሞት ተሽሮ እንዲሁም ጠፍቶ የነበረው ልጅነት ክርስቶስ በተቀበለው ጸዋትወ መከራ ስለ ተመለሰ የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ ከጨለማውና ከደረቁ እሳት ወጥተው ልምላሜ ወደማይለየው ጥንተ ቦታችን ተመለስን ሲሉ ለምለም ቄጤማን በራሳቸው አስረው በዓሉን ሲያከብሩ ይኖራሉ::

ቄጤማ ሁልጊዜም ቢሆን የደስታ ምልክት ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው ግብዣ በሚያደርግበት ጊዜ ምንም እንኳ በወርቅ ያሸበረቁ ልዩ ልዩ ምንጣፎች ቢኖሩበትም ቤቱን የሚጐዘጉዘው በቄጤማ መሆኑን ሁላችን የምናውቀው ነው::

ስለዚህ ከዚያ በፊት ባይታወቅና ባይሠራበትም ኖኅ ርግቧን በላካት ጊዜ የወይራ ቅጠል ቄጤማን ይዛ ከተመለሰች ወዲህ ቄጤማ የደ ስታ ምልክት ሆኗል:: አባቶቻችን አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ ተድላ ደስታ ሲያደርጉ ቆጽለ ልምላሜን መያዝ ያዘወትሩ ነበር:: /ኦ.ዘሌዋ. 24÷40/:: ልምላሜ ያለው ነገር ለመንፈሳዊ ደስታ ብቻ ሳይሆን በሥጋዊ በኩልም በጣም ተፈላጊ ነው:: እንዲያውም አንድ ጊዜ ሕዝቡ ተሰብስበው አቡዛርድን ወደተባለው ፈላስፋ መጡና በመንፈሳዊ ፍልስፍና በጣም የተራቀቀ ስለነበር ለሥጋችንና ለነፍሳችን የሚሆነንን ጥበብ አስተምረን ብለው ቢለምኑት ከሰጣቸው ጠቃሚ ምክር አንዱ እንዲህ የሚል ነበር «የጠራውን ውኃ ሲፈስ ማየት የሚወዱ ፊት በማየት ዓይንን ብሩህ ያደርጉታል» ካለ በኋላ በበለጠ ደግሞ ዓይንን ብሩህ ሊያደርግ የሚችለው ሁል ጊዜ ልም ላሜ ያላቸው አትክልቶች ሲታዩበት ነው» ብሏል::

እንግዲህ ፈላስፋው አቡዛርድን የተናገረው ልምላሜ ያላቸው ነገሮች ማለት ቄጤማና ቄጤማን የመሳሰሉት ተክሎች መንፈሳዊ ስሜትን የሚያረኩ ብቻ ሳይሆኑ የሰውነት መብራት የሆነውን ዓይንን የጠራና ንጹሕ ብሩህ ሊያደርገው እንደሚችል እንገነዘባለን::

በአጠቃላይ ጌታ የአድኅኖተ ዓለም ሥራውን ጨርሶ በመቃብር ባረፈበት ዲያብሎስ በተሻረበ ት በዐቢይ ሰንበት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የድኅነትን የምሥራች ትናገራለች፤ እኛም የምሥራቹን ዜና ተቀብለን መግለጫው የሆነውን ቄጤማ በራሳችን እናስራለን::

**እንኳን ለብርሃነ ትንሣ ኤው በሰላም አደረሳችሁ!**



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ሰሙነ ሕማማት

እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከሆሣዕና እስከ ትንሣኤ ያሉት ቀኖች ሰሙነ ሕማማት /የሕማማት ሳምንት/ ይባላሉ:: የዚህ ምክንያቱ አንድም ዕለታቱ የዓመቱ ፍዳ፣የዓመተ ኩነኔ መታሰቢያ እንደመሆናቸው ወደ መቃብር በመውረድ ላይ ወደ ሲኦል መውረድ የነበረባቸው የሰው ልጆች ስቃይ የሚታሰብበት በመሆኑ ዳግመኛም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእያንዳንዱ ጉስቋላ ምስኪን ዕዳ ከፋይ ሆኖ በእኛ ፋንታ እርሱ የተንገላታበት፣ መከራ የተቀበለበት በሰዎች የተጐሳቆለበት ሳምንት በመሆኑ የሕማማት ሰሞን ይባላል::

አዎ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጢአት የጐሰቆለውን ዓለም በቅዱስ ደሙ ሊያነጻ በኩነኔ የወደቀውን የሰው ልጅም ከሲኦል ግዞት ያወጣ ዘንድ በገዛ ፈቃዱ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሠላሳ ሦስት ዓመት ሙሉ በምድር እየተመላለሰ ዓለምን አስተማረ፤ ድውያንን ፈወሰ፤ የተራቡትን አጠገበ፤ በደረቅ ግንባር ላይ ዓይንን ፈጠረ፤ በአጠቃላይ ለዓለም የሚያስፈልገውን ሁሉ ፈጸመ::

ይሁን እንጂ ዓለም መድኃኒቱን አላወቀምና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ስለ አደረገ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን በቅንዓት ተነሡበት፤ ስለዚህም በተንኮል ሊያጠምዱት ፈለጉ፤ ሆኖም ሐሰት በአፉ አልተገኘበትምና ለተንኮላቸው መግቢያ አላገኙም::

ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን የሚያድነው በቅዱስ ደሙ ስለሆነ በፈቃዱ ራሱን ለሞት አሳልፎ ሰጠ:: ቅዱስ እለስክንድሮስ በድርሳኑ በፈቃዱ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ መስጠቱን ያለበደሉም ሞት የፈረዱበት መሆኑን በብዙ ቦታዎች ገልጾ አስተምሮዋል::

«በእርሱ ለማይነገር ለዚህ እንግዳ ምሥጢር አንክሮ ይገባል:: ፈራጅ እርሱን ፈረዱበት፤ ከማዕሰረ ኃጢአት የሚፈታ እርሱን ዐሰሩት፤ ዓለምን የያዘ እርሱን ያዙት፤ ለሰው ሕይወትን ለሚሰጥ ለእርሱ ሐሞትን አጠጡት፤ የሚያድን እርሱ ሞተ:: ሙታንን የሚያስነሣቸው ተቀበረ::. በሰማይ ያሉ ኃይላት አደነቁ:: መላእክትም በተደሞ ፈዘዙ:: እርሱ ግን ዝም ብሎ መከራ ተቀበለ፤ የማይታየው ታየ የማይያዘው ተያዘ፤ የማይታመመው ታመመ:: አልተበቀለም፥ የማይሞት እርሱ በፈቃዱ ሞተ:: ይሁን ብሎ በመቃብር አደረ:: ፍጥረታት ሁሉ አደነቁ የማይታመመው እርሱ ለሰው ብሎ መከራ ተቀብሏልና::» ብሏል:: ሃይማኖተ አበው ምዕ.16 ክፍ. 1 ከቁጥር 4–8 እነዚህ ከትንሣኤ በፊት ከሆሣዕና በኋላ የሚውሉ ዕለታት የሚታሰቡት በተለየ ሁኔታ ነው::

ክርስቲያኖች ከጠዋት እስከ ማታ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በሚያዝዘው ሁኔታ በምህላ፤ በጸሎትና በስግደት በቤተ ክርስቲያን በመገኘት ያከብሩዋቸዋል:: የሚነገሩት ቀለሞችና የሚዜሙት ዜማዎችም ሕማማቱን የሚያመለክቱ ናቸው::

በነዚህ ዕለታት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ተቀብሎባቸዋልና የተቀደሰ ሳምንት ይባላል:: በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 595 ቁጥር እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል:–

«ሴቶችም ጌጣቸውን ይተዉ ሁሉም ለእያንዳንዱ በ40 ጾምና በሰሙነ ሕማማት መጠበቅ ይገባዋል፤ ደኅንነታችንና የኃጢአታችን ሥርየት በእነርሱ ነውና::... ክብርት በምትሆን በሕማማት ሳምንት እንዱስ እንኳ በምንጣፍ ፈጽሞ እንዳይገናኝ ከኃብቻ ሕግ የወጣ ነው:: ይህችን ኃጢአት የሚሠራት ሰው ወዮለት» ይላል::

በእርግጥም ሰሙነ ሕማማትን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች በፍጹም ጾም በጸሎት፤ በስግደት የሚያሳልፉት ሲሆን በተለይ በገጠሩ ከሆሣዕና በፊት ከሚውለው ዓርብ ጀምሮ በዓሉ ይከብራል:: በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ይህ ከሆሣዕና በፊት የሚውለው ዓርብ ወፍጮ መድፊያ ይባላል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሕማማት ውስጥ ወፍጫ አይፈጭምና::

ዛሬም ይህንን ዐቢይ በዓል በጥንቃቄና በኀዘን በጸሎት በስግደት ልናከብረው ይገባል:: ደኅንነታችን የተረጋገጠው ከሲኦል ባርነት ነፃ የወጣነው በዚህ ሳምንት በተፈጸመው በሕማሙ፤ በሞቱና በትንሣኤው ነውና::

በአጠቃላይ በሰሙነ ሕማማት በገላ.3÷1 እንደተገለጠው ጌታችንን ይበልጥ በዓይናችን ፊት እንደ ተሰቀለ ሆኖ እናየዋለን:: የእግዚአብሔር ሰዎች በጆሮአቸው የሰሙትን ሁሉ በእምነት በዓይነ ልቡናቸው ያዩታል:: «እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በፊቴ አየዋለሁ» /መዝ.15÷10/ እንዳለ ቅዱስ ዳዊት:: በመሆኑም እንደ ውሻ ወደ ተፋነው ኃጢአት፣ቀድሞ ወደ ገዛን ጠላት በመመለሳችን ራሳችንን እየወቀስን:–

ሀ/ መከራ መስቀሉን፣

ለ/ ቅዱሳን በከሃድያን ፊት የተቀበሉትን መከራ፣

ሐ/ እንደ ዳዊትና እንደ ጴጥሮስ ኃጢአታችንን እያሰብን ልናለቅስ ይገባል:: ፈያታዊ ዘየማንን በመስቀል ላይ ሳለ ያሰበው አምላክ እኛንም በመንግሥቱ በመጣ ጊዜ ያስበን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን:: አሜን::

❖❖❖

## ጥብጣቤ

ትርጉሙ:– ቸብ፣ቸብ ማድረግ ማለት ነው:: እያንዳንዱ ምእመን ሲሰግድና ሲጸልይ ከዋለ በኋላ ሠርክ ሲሆን ወደ ካህኑ እየቀረበ በሰሙነ ሕማማት የሠራውን ኃጢአት ሲናዘዝ ስግደት ይሰጠዋል:: ጥብጣቤውም አንድም የተግሣጽ ዳግመኛም የጌታ ግርፋት ምሳሌ ነው::

## የይሁዳ መረገም

የአስቆሮቱ ይሁዳ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ነበር:: ነገር ግን የተመረጠበትን ሐዋርያዊ ተግባር ትቶ ከስቃልያን እግዚእ ጋር ጌታውንና መምህሩን አሳልፎ በመስጠቱ በኋላም በጥፋቱ ተፀፅቶ እንደ ጴጥሮስ ንስሐን ሳይሆን በብልጠት ምሕረትን ስለፈለገና ራሱን ስለገደለ የእርግማን እርግማን ተፈጽሞበታል:: የተለያዩ መዝሙራት በማስተዛዘል በሚጸለዩበት ጊዜ "ለይሁዳ ወልዱ ወለወልደ ወልዱ ይደምሰስ፣የይሁዳ ልጅ ከልጅ ልጆቹ ጋር ይደምሰስ፣ይጥፋ" የሚል የመርገም ቃል አዝማች ይነገራል:: ይህንን ለማሳየት ትርዒት ነክ የሆነ ሥርዓት አለ:: ይኸውም በመቋሚያ ላይ ጧፍ ተደርጐ አንደኛውን የዳዊት መዝሙር /መዝ. 1÷1–6/ በማስተዛዘል ከተነበበ በኋላ «ወፍኖቶሙሰ ለኃጥዕ ከመዝ ትጠፍዕ፤ የኃጥአን መንገድ እንደዚህ ትጠፋለች» ከሚለው ላይ ሲደርስ ማኅበረ ካህናቱ በያዙት መቋሚያ አንድ ጊዜ ውርጅብኝ በማውረድ መብራቱን ያጠፋታል:: የይሁዳ የዘር ዘር እንዲህ ይጠፋል ሲሉ:: በመጨረሻ «ንሴብሖ ለእግዚአሔር ስቡሐ እንዘ ተሰብሐ፤ እግዚአሔርን እናመስግነው የተመሰገነ ምስጉን» በማለት ቤዛነቱን ያበሥራሉ::

## አክፍሎት

በዕለተ ስቅለት የተጀመረ የጾም መጀመሪያ ነው:: ይኸውም ጌታችን በማቴ.9÷14–17 «ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያን ጊዜም ይጦማሉ» ሲል በተናገረው፤ አንድም ከጌታ ስቅለት በኋላ እመቤታችን ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስና ዮሐንስ የጌታን ትንሣኤ ሳናይ እህል ውኃ አንቀምስም ብለው እስከ ትንሣኤ ቆይተዋል:: ይኸንንም አብነት አድርገው ከዓርብ እስከ እሑድ ሌሊት የሚያከፍሉ አሉ:: ይህ የማይቻለው ዓርብ ማታ ቀምሶ እስከ ትንሣኤው ይቆያል:: ሁለት ቀን ማክፈል ቢከብድ እንኳን ቅዳሜን ማክፈል ተገቢ ነው:: /ፍ.ነ.ፍ.መ. 15÷579/::





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ይዲድያ ማራ እና ይዲድያ

በ1993 ዓ.ም. በዝግጅት ክፍሉ በተደረገው የአጭር ልቦለድ ውድድር 4ኛ የወጣ::

ከይዲዲያ አሱን ባኩት

/በእግዚአብሔር የተወደደ መራራ እና በእግዚአብሔር የተወደደ/

1987 ዓ.ም መጋቢት ወር ነበር ከማራ ጋር የተገናኘነው:: የለበሰችው ጥቁር ልብስ የውስጧንም መጥቆር ይገልጣል:: ገጿም እንደ ልብሷ ጠቀሯል:: ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ዓይኖቿን ወደ ሰማይ ሰቅላ በቁጣ ቃል ከፈጣሪዋ ጋር ትሟገታለች:: የምትናገረው በዝግታ ቢሆንም ይሰማኝ ነበር::

«እኔን መጠበቅ ለምን አቃተህ? ይሄ ሁሉ ሲደርስብኝ ለምን ዝም አልክ? አትፈርድም? በእኔ ላይ ምን አስጨከነህ? ለምን? ስለማትወደኝ? አዎን ስለማትወደኝ!» በዓይኖቿ እንባ ግጥም ቢልም አላለቀሰችም፤ ታግላ ዋጠችውና ወደ ሙግትዋ ገባች:: አሁንም ትከራከረዋለች:: ገረመኝ÷ ስለማትወደኝ ነው?! አልኩ በውስጤ:: እንዴት ስለማትወደኝ ነው ይባላል? ደሙን ያፈሰሰው የሞተው ለማን ሆነና? በጣም ገርሞኛል:: እኔ በንግግርዋ እየተገረምኩ እያለሁ ሙግቷን ጨርሳ በቅያሜ ዓይን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እየተመለከተች ፊቷን አዙራ ሄደች:: አንድ ጥያቄ በውስጤ ተፈጠረ፤ «ለምን ከፈጣሪዋ ተጣላች?»

ምክንያት ስላላገኘሁ ከተቀመጥኩበት ተነሥቼ ተከተልኳት:: በመጠኑ የራቀች ቢሆንም በፍጥነት ተከተልኳት:: ስትሄድ ጥላዋንም የምታምነው አትመስልም:: ፍንጥር ፍንጥር እያለች ከሰው እየሸሸች ቁልቁል የአራት ኪሎን መንገድ ይዛ ወረደች:: ተጠጋኋት:: ገና ስታየኝ ሸሸቺኝ:: ብትሸሸኝም ቀስ ብዬ ቀረብ አልኳትና:-

«የእኔ እኅት ይህንን ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ጥለሽው ነበር» ብዬ አንድ መጽሐፍ ሰጠኋት:: ፈገግ ለማለት እየሞከረች

«አመሰግናለሁ፤ ረስቼው መጣሁ ለካ?» አለችና መጽሐፉን ተቀበለችኝ

«መቼስ አታባርረኝ» አልኩና አጠገቧ ሆኜ መራመዴን ቀጠልኩ ከእሷ ጋር መሆኔን ያልፈለገችው መሆኑን ከሁኔታዋና ከመልሶቿ አጫጭር መሆን ብረዳም ልነግራት የፈለግኩትን ያንን ሳልናገር ልለያት አልፈለግኹም::

በመጠኑም ቢሆን ስለ መጽሐፉ እየተነጋገርን ለመግባባት ሞከርን:: ከባድ ቢሆንም በመጠኑ አናግሬ አታለሁ::

«ቤተ ክርስቲያን ትሄጃለሽ?» አልኳት:: ዝም አለቺኝ÷ መግባቢያ መፈለጌ ነበር::

«ለምን አትሄጂም?» አሁንም ዝም አለቺኝ፤ እንደውም የሰማችኝ አልመሰለኝም:: ወቅቱ የትንሣኤን በዓል የምናከብርበት ወቅት ስለነበረ«ትንሣኤን ለማክበር ተዘጋጅ ተሻላ?!» አልኳት ያለችው ባይሰማኝም የሆነ ነገር አጉተመተመች::

«የት ቤተ ክርስቲያን ታድሪ ያለሽ?» ስል ጠየቅኳት፤ ይህን ሁሉ ጥያቄ ያበዛሁባት ውትወታዬ አሰልችቷት ብትናገር ብዬ ነበር:: እውነትም ጥያቄዬ አሰለቻት መሰለኝ

«የትም!» አለቺኝ በቁጣ

«ለምን?»አልኳት ፈጠን ብዬ

«አንተ የምትወደው እርሱ ግን በማይወድህ ሰው ቤት ሄደህ ታድራለህ?» አለቺኝ በጣም ተቆጥታ:: የማትወደው የማይወድህ?

«ሰው ቢሆን እሺ... ግን እኮ ሰውና እግዚአብሔር በጣም ይለያያሉ፤ እሱ እንደ ሰው ...» ያሰብኩትን ሳልጨርስ «አዎ÷ አይመሳሰሉም» አለችና ነገሩን በአጭሩ ለመዝጋት ፈለገች:: እኔ ግን አልቻልኩም፤ መናገር ስችል ሳልናገር ብታመልጠኝ ምን ልል ነው? ቅድም ቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ ስትል ከነበረውና አሁንም ከተናገረችው ነገር በመነሣት ትንሽ ልናገር ብዬ ቀጠልኩ::

«እግዚአብሔር ሁላችንንም ይወደናል፤ የሞተው ደሙን ያፈሰሰው ለማን ሆነና ታዲያ÷ ባይወደንማ አይሞትልንም ነበር:: በአንድ ነገር በመፈተንሽ ውስጥሽ ተረብሿል ይመስለኛል:: ፈተና ያለ ነው:: ኢዮብ ስለማይወደድ ነው ያ ሁሉ መከራ የመጣበት? አይደለም:: ከዚያ ፈተና በኋላ፤ በፊት ከነበረው ሁሉ ይበልጥ ጽናት ሀብት፣ ልጆች አግኝቷል:: መፈተኑ ለበጐ ነበር:: ብዙ አባቶች በፈተና የሚያዙት ስለማይወደዱ ነው? አይምሰልሽ:: መፈተን መለካት በመሆኑ ነው::» ነገርኳት ተናግሬ አልወጣልኝም፤ ዝም ብላ ታደምጠኝ ነበር::

መለያየችን ከመድረሱ በፊት በፈለገችው ጊዜ ልታገኘኝ የምትችልበትን አድራሻ ሰጠኋት:: ዞር ስልላት የምትጥለው ትመስላለች:: ማለት የምፈልገውን ገና አላልኩም:: መመስከር ነበረብኝ፤ ግን እኔ ሳልሆን የሚያስተምር እሱ እግዚአብሔር ነውና በፈቀደ ጊዜ ያስተምራታል አልኩና በዚህ ተጽናናሁ:: እሷም የአውቶቡስ ተራን ታክሲ ይዛ ነጐደች...

ቤቴ ሁሉ ገብቼ የማስበው ስለ እሷ ነበር:: አሳዝናኛለች:: «ምን ሆና ይሆን?» እላለሁ:: «ወይኔ እኅቴን፤ ይሄኔ ቀላል ነገር ይሆናል የሚያብሰለስላት» እላለሁ፤ አሁንም ምን እንደሆነች ሳስብ፤ ወደ ፈጣሪዬ ስጸልይም፣ የጠፋች ልጅ ትገኝና ታከብረው ዘንድ በሰጠኋት አድራሻ እንድትመጣ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ ይህንን በልቧ ያለውን ሀሳቧን ትታ ከአምላክ እንድትታረቅ ፈጣሪዬን ለመንኩ::

ሦስት ወር:: ማራ ብቅም አላለች:: በየዕለቱ ትመጣለች ብዬ ባስባትም ፈጽሞ አልመጣችም:: ፈቃደ እግዚአብሔር ባይሆን ነው ብዬ እርሱው እንዲረዳት እየተማፀንኩ ኑሮዬን ቀጠልኩ:: ግን ከማራ ጋር ከተገናኘን በኋላ «ለምን ሰው ይህንን ያህል ያመራል? ሁሉም ወቅቱን ጠብቆ ያልፍ የለም?» እያልኩ ከራሴ ጋር እሟገት ነበር::

ልክ በአራተኛው ወር ያላሰብኩት ነገር ተከሰተ:: ዓይኖቼን ማመን አልቻልኩም:: «ተመስገን ተመስገን» ከማለት በስተቀር ምንም አላልኩም:: ማራ መጣች:: ቢሮዬ ነበርኩ:: እኔም ላይ እምነት ያላት አትመስልም:: ግን መጥታለች:: ዋናው መምጣቷ ነው÷ ደግሞ የመጣችው ብታምነኝ አይደል?!

ቀና ብላ አላየቺኝም፤ ቃል አልተናገረችም፤ አጐንብሳ የሹራቧን እጅጌ ታፍተለትላለች:: «ለምን ጠፋሽ? ደኅና ነሽ?» እያልኩ ዳር ዳር በማለት ጊዜ ላጠፋ አልወደድኩም፤ ቀጥታ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሲያስጨንቀኝ ወደ ከረመው ጥያቄ ገባሁ::

«ማራ?» አልኳት

«አቤት» አለች ቀና ሳትል

«እስቲ ልትነግሪኝ የምትፈልጊው ነገር ካለ ንገሪኝ?» አልኳት

ገና ሳታወራ እንባዋ በዓይኗ ግጥም አለ በረጅሙ ተነፈሰችና እንዲህ ስትል ጀመረችልኝ... «ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ እያለሁ ነበር በማላውቃቸው ሁለት ወንዶች ተገድጄ የተደፈርኩት፤ ከዚያም አባቴ ሞተ፤ አንድ ያለኝ እርሱ ብቻ ስለ ነበር ዙሪያው ገደል ሆነብኝ:: የምበላው የምለብሰው ስላጣሁኝ ሰው ቤት ተቀጠርኩ:: ትምህርቴንም እዚው እየሠራሁ መከታተል ጀመርኩ:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ በመጣልኝ ነጥብ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ገባሁ:: እዛ ስገባ ለእኔ ሁሉም ነገር ከባድ ሆነብኝ:: በተቋሙ ውስጥ ከሚሠራ ሰው ጋር አልተኛም በማለቴ የትምህርት መረጃዎቼን ሁሉ አበላሽቶ ከተቋሙ እንድባረር አደረገ:: ከዛም ምንም ምርጫ ስላልነበረኝ ተመልሼ ወደ ሰው ቤት ገባሁ:: ለሁለት ወር በሰዎቹ ቤት ከሠራሁ በኋላ ያ በልጅነቴ የደረሰብኝ ዓይነት መከራ በድጋሚ ደረሰብኝ:: የተቀጠርኩበት ቤት ልጅ ባላሰብኩት ሰዓትና ጊዜ ደፈረኝ:: በዚህ ጊዜ ከሰዎቹ ቤት ወጣሁ:: ምን ማድረግ፣ ማን ጋር መሄድ እንዳለብኝ እንኳን ሳላውቅ ባዶ እጄን ነበር ብርር ብዬ የወጣሁት:: ሁለት ቀን ጐዳና ላይ አደርኩ:: በሦስተኛው ቀን ግን ረሃቡም ስለበረታብኝ ወደ አንድ ኬክ ቤት ገብቼ ለመንኩ:: አጋጣሚ ሆነና ባልጠበኩት መንገድ እዛው ኬክ ቤት ተቀጠርኩ:: አሁን እዛው እሠራለሁ:: ግን ደስተኛ አይደለሁም ኃዘንተኛ ነኝ:: አጽናኝ ወገን ዘመድ የሌለኝ ብቸኛ...» ከዚህ በላይ ምንም መናገር አልቻለችም:: ይሄንን ሁሉ ስትነግረኝ ያለማቋረጥ ይፈስ የነበረው እንባዋ አሁን ፈጽሞ ሊያስወራት አልቻለም::

«ለምን ብቸኛ ሆንሽ?» መጠየቅ የሌለብኝ ጥያቄ ነበር፤ ግን ከመደንገጤ የተነሣ ዝም ከማለት ብዬ ሳልዘጋጅ ጠየቅኳት::

«ማንንም ማመን አልቻልኩም:: ሰው ሁሉ አጥፊዬ ይመስለኛል፣ ተጠራጣሪ ሆንኩ፣ ፈጣሪዬንም ለምን ይሄንን አደረግክብኝ እያልኩ እሞግተዋለሁ፣ መጸለይ አልቻልኩም፣ ዘወትር የማስበው ስለደረሰብኝ ነገር ነው:: መተኛት፣ መሥራት፣ መብላት ፈጽሞ አልቻልኩም:: እንዳላብድ እፈራለሁ» ተንሰቅስቃ አለቀሰች:: የእኔም ልብ ክፉኛ አዘነ የምመክራትን ነገር ሁሉ መካሪ አምላክ እንዲያሳውቀኝ ለመንኩት:: «አይዞሽ ማራ» አልኳት ወደ እርሷ እየተመለከትኩ:: የደረሰባት ነገር የሚያሳዝንና አሁን ሁሉንም እርሺው ማለትም እንደማይቻል ባውቅም ምንም ያልተፈጠረ ለማስመሰል እራሴን አረጋጋሁና ይሄ እኮ ቀላል ነገር ነው በአንቺም ላይ ብቻ የደረሰ እንግዳ ነገር አድርገሽ ማሰብ አልነበረብሽም:: በብዙ እኅቶቻችን ላይ የሚደርስ ነገር ነው:: ደግሞ ሰው ሲፈተን ለምን ተፈተንኩ አይልም:: እንዴት ነው በሰላም ፈተናውን ማለፍ የምችለው? ነው የሚለው፤ አንቺም አንዴ ይኼ ነገር ሆኖብሻል:: ካሁን ወዲያ ለምን? እያሉ መጠየቁ መፍትሔ ሳይሆን ሌላ ችግር ነው የሚያስከትልብሽ:: የሚበጀው «እንዴት ልወጣው»ማለቱ ነው:: በዛን ጊዜ እግዚአብሔር አንቺን ማዳን አቅቶት አልነበረም፤ ወይም አንቺ እንዳልሽው ስለ ማይወድሽ አይደለም ይህንን ፈተና ስትፈተኚ ዝም ያለው:: ብዙ አሁን ያልተገነዘብሻቸውን ነገሮች ሊያስተምርሽ ወይም ከአንድ ነገር ሊጠብቅሽ አሊያም ከዚህ በኋላ ትልቅ በረከት ሊሰጥሽ አስቦ ይሆናል:: አንቺ እንደውም ዕድለኛ ነሽ እንደዚህ ዓይነት ነገር የደረሰባቸው እኅቶቻችን ያረገዙ፣ በስንት በሽታ የተያዙ፣ በድብደባ የሞቱ ብዙ ብዙ ዐይነት ነገር የገጠማቸው አሉ:: አንቺ ግን ይሄ ሁሉ አልገጠመሽም:: ታዲያ አንቺ አልተሻልሽም?... በዚህ ሁሉ ደግሞ አምላክሽን ልታመሰግኚው ልትጽናኚ ነበር የሚገባሽ:: ስላለፈውም እንዳታስቢ እንዳትጨነቂ መጸለይ ነው ያለብሽ:: ሰው ደግሞ መጥፎም ጥሩም ነው:: እመቤታችን፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሌሎችም ቅዱሳን አባቶቻችንና እናቶቻችን ቅዱሳን ሰዎች ናቸው:: እነ ይሁዳን የመሳሰሉት ደግሞ መጥፎ ሰዎች የምንላቸው ናቸው:: ስለዚህ ሰዎችን ሁሉ በጅምላ ልትጠያቸው አይገባም:: በዛ ላይ ነገር ሁሉ ለበጐ መሆኑን አትርሺ:: ስንቶቹ አባቶቻችንና እናቶቻችን መሰሉሽ ብዙ መከራ ገጥሟቸው ያለፉት:: በትንሽ መከራ መሸነፍ አይገባም፤ መጠንከር መጽናት ያስፈልጋል፤ አምላካችንም አጠንክረን አጽናን ብለን ከለመንነው ይረዳናል...» አቋረጠችኝና

«እኔ እኮ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ መጸለይ አልቻልኩም፤ ቆሜ ሰዎቹን መርገም እሱንም ማማረር ብቻ ነው የቻልኩት»

«መቆም በራሱ ጸሎት ነው» አልኩና አንድ ምሳሌ ነገርኳት

«አንድ እናት ልጇ ከትምህርት ቤት ሲመጣ ቤቷን ቆልፋ ምሳም ሳትተውለት ርቃ ሄዳለች ልጁ በጣም ተርቦ ውሎ ማታ መጣች:: ልጁ ምን የሚላት ይመስልሻል? እሰይ እንኳን ቆለፍሽብኝ ብሎ የሚያመሰግናት ይመስልሻል? አያመሰግናትም:: እሷም ከእሱ በፍጹም ምስጋናን አትጠብቅም:: በቃ እግዚአብሔርም የደረሰብሽን ሁሉ ያውቃል:: ስለዚህ በምትናገሪውም አያዝንም:: አንድ ቀን ልብሽን እስኪጠግነው ድረስ ይታገሥሻል:: እግዚአብሔር እኮ ማንንም እንዲጠፋበት አይፈልግም፤ ሁላችንንም ይወደናል:: አሁን አንቺን ተስፋ እያስቆረጠ እንድትርቂ የሚያደርግ ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ነው:: ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም ሲባል አልሰማሽም ሁልጊዜ ተስፋ በልባችን አለ፤ ምንም ዓይነት መከራ ቢደርስብን ልንወጣው እንደምንችልና ነገር ሁሉ ደግሞ ለበጐ የሆነ እንደሆነ እናስባለን:: ከሌላውም የሚለየን ይሄ አይደል እንዴ? ከመከራ በኋላ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀልንን በረከት ማን ያውቃል? ተስፋ አድርጊ፣ ተጽናኚ ሥራውን እስኪሠራም እስቲ ጠብቂው::

«ተጽናኚ! ጠብቂው?!» አለች በድንገት ለረጅም ጊዜ በዝምታ ታዳምጠኝ ከነበረችበት ሁኔታ ለየት ብላና እኔ ያልኩትን በምፀት ንግግር ደግማ

«እንዴት ልጽናና? እስከ መቼስ ልጠብቀው? ከፊቴ የሚታየኝ ምንም ብርሃን የለም:: ተሠብሬአለሁ፤ ዳግም ላልጠገን ተንኮታኩቼ ደቅቄ ወድቄአለሁ:: ካሁን ወዲያ ምንም የሚያጽናናኝ ነገር የለኝም:: እርሱንም አልጠብቀውም፤ ደጁንም አላይም ጠልቶኛል...::»

እንባዋ ያለማቋረጥ ይፈሳል:: ጨነቀኝ:: ያላሰብኩት ነገር በመሆኑ ብዙ አልመከርኳትም:: በዚህ ሁኔታ ላይ ሆና መምከርም ከባድ ነው ስለዚህ ሀሳቧን ለመቀየር ሌላ ጥያቄ እጠይቃት ጀመር::

«ሠፈርሽ ወዴት ነው?» አልኳት

«አውቶቡስ ተራ»

«ትምህርትሽን የት ጨረስሽ?»

«አዲስ ከተማ ነበር»

«ስንት ዓመትሽ ነው?»

«የእኔ ...22 ነው » የምትመልስልኝ ከጠየቅኳት ከረጅም ቆይታ በኋላ ተስፋ በቆረጠ ስሜት ነበር::»

«እርጅተሻላ! ከዘራሽን ታዲያ ለምን ጥለሽ መጣሽ? እኔ አልደግፍሽም ለእራሴም ደክሜአለሁ::» አልኳት የግዷን እንባዋን አብሳ ፈገግ አለች:: መረጋጋቷን አይቼ ወደ ዋናው ጉዳያችን ገባሁ::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

«ዛሬ እንዴት መጣሽ?»

«ስለባሰብኝ እንዳላብድ ፈራሁ የማማክረውም ሰው ስለሌለኝ ወደዚህ መጣሁ» አለች በተሰበረ ልብ::

«አይዞሽ ሁሉን ነገር እግዚአብሔር ያስተካክለዋል:: ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ትሄጃለሽ?» ስል ጠየቅኳት::

ዓይኖቿን መሬት ላይ ተክላ ለረጅም ጊዜ ዝም ካለች በኋላ ያስታወሰችው ነገር ያለ ይመስል

«ድሮ ...» አቋረጠችው፤ ልትነግረኝ የፈለገችውን ተወችውና

«አንዳንዴ ለመሟገት እሄዳለሁ::»

«ድሮ ግን ትሄጂ ነበር?» ዝም አለቺና በረጅሙ ተንፍሳ

«አዎ እሄድ ነበር... ይህ ነገር ከደረሰብኝ በኋላ ማለትም የሁለተኛው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ላለመድረስ ወስኜ ነበር:: ግን አንዳንዴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመጨቃጨቅ ለመሟገት መሄዴን አልተውኩም ነበር:: በሩ ላይ ቆሜ አልቅሼ ተናድጄበት እመለስ ነበር:: ከዚያም ሁሉን ተውኩትና ከዚህ ችግሬ ለመላቀቅ ስል የራሴ ያልኳቸውን የመጽናኛ ዘዴዎች በራሴ መንገድ እፈጽም ጀመር:: ከዘዴዎቼ መሀከል አንደኛው እራሴን የውስጤን ለመርሳት ከማይሆኑ ጓደኞች ጋር መግጠምና ፈጽሞ ቤተ ክርስቲያን የሚባል ቦታ አለመድረስ ነበር:: ቀን ከጓደኞቼ ጋር ስሆን ምንም ያልደረሰብኝ እመስል ነበር ቤቴ ገብቼም በቤተሰቦቼ ፊት ደስተኛ ለመምሰል እጥር ነበር:: በሰው ፊት መምሰሉ ቢሳካልኝም እንዲህ መሆኔ ውስጤን ይበልጥ ያሳምመኝ ነበር:: ሆኜ እንዳልሆንኩ፣ ተሰብሬ እንዳልተሰበርኩ፣ ወልቄ እንዳልወደቅኩ፣ ሞቼ እንዳልሞትኩ ...» አሁንም የፈረደ በት እንባዋ ያለማቋረጥ በጉንጮችዋ እየወረደ የምታፍተለትለው የሹራቧ እጀታ ላይ ጠብ ጠብ ይላል:: ላቋርጣት አልፈለግኩም ተናግራ ይውጣላት አትታፈን ብዬ ዝም አልኳት::

«አልጋዬን ገልጬ ስተኛ ትክክለኛ ማንነቴን አየዋለሁ:: ያንን እየሸፋፈንኩ ያባስኩትን፤ እንዲያመረቅዝ ያደረግኩትን ቁስሌን አየዋለሁ:: ያንን በልጅነት ገላዬ ላይ የወረደብኝን ዱላ እያሰብኩ ብቻዬን አለቅሳለሁ:: ሰው ሁሉ የረከስኩ አድርጎ የሚቆጥረኝና የሚጠላኝ ስለሚመስለኝ ብቸኝነቴ ጐልቶ ይታየኛል:: አቤት የምልበት ያጣሁ ብቸኛ ነኝ... በዚህ ሁኔታም ራሴን እያታለልኩ መቆየት አልቻልኩም:: ይሄኛው ዘዴዬ መጽናኛ ሊሆነኝ አልቻለም አባሰብኝ እንጂ:: ቀጥዬ ቤተ ክርስቲያን መሄድ እንደሌለብኝ የወሰንኩትን ውሳኔ ሳላነሣ ከጓደኞቼ ርቄ መጻሕፍትን ዓለማዊ ልቦለዶችን፣ ፊልም ማየትን፣ ሙዚቃ መስማትን መጽናኛ አደረግኩት ከዘዴዎቼ ሁሉ መጥፎው ይሄ ነበር:: ሀሳቤ ስለ ማይሰበሰብ መጽሐፉንም ፊልሙንም መቼ መሀል እንደ ገባሁ ምን እንዳየሁ፣ እንዳነበብኩ ሳላውቀው ያልቃል:: በዛ ላይ ትልቁ መጥፎ ነገር ከአንዳንዶቹ መጻሕፍትና ከፊልሙ የማላውቀውን ኃጢአት ያላሰብኩትን በቀል፣ ዝሙትና የመሳሰሉትን ማወቅ መማር ጀመርኩ:: የባሰ በሽታ ስለ ሆነብኝ ይህንንም ርግፍ አድርጌ ተውኩት::

ከዛም ወደ ተለያዩ የመዝናኛ ስፍራዎች ሄጄ ልዝናና ሞከርኩ:: ግን አልተሳካልኝም:: ሁሉን ሞክሬ እንቢ ሲለኝ ጥሩው ዘዴ ቤትን ዘግቶ ለብቻ ሆኖ ምንም ሳይሠሩ ማልቀስ እንደሆነ አመንኩ :: አልፎ አልፎ ግን እንደ ድሮዬ ለሙግት ቤተ ክርስቲያን መሄድ ጀመርኩ::: ቢሆንም ግን እንደ ድሮዬ ለሙግት ዓይኖቼ በእንባ ብዛት ፈዘዙ፣ ከሰዎች ጋር ያለኝ ግንኙነት ቀረቤታ ፈጽሞ ጠፋ፣ ማኅበራዊ ኑሮ ብሎ ነገር ተረሳኝ::

ከደኑ እንደ ወጣ አውሬ መልመድ አቃተኝ፣ ብቸኛ፣ ኃዘንተኛ፣ ሴት ሆንኩ:: ከዕድሜዬ በላይ ገረጀፍኩ ተስፋ ከውስጤ አለቀ፣ ከአምላኬ ተጣላሁ፣ ጨለማም ከበበኝ፤ መሄጃ መድረሻ ያጣሁ ኃዘንተኛ ሆኛለሁ...::» እንባዋ እንደበፊቱ ይፈሳል:: «ምስኪን» አልኩኝ በሆዴ «እውነትም ሲያዩዋት ተስፋ የሌላት ኃዘንተኛ» የጠቆረች፣ የከሳች በኃዘን የገረጣች ብቸኛ ሰው ናት::

«ማራ ትሰሚኛለሽ አንቺ በራስሽ መንገድ ዘዴ የምትያቸውን ነገሮች ሁሉ ተጠቅመሽ ያመጣሽው ለውጥ የለም:: እንደነገርሺኝ ከሆነ እንደውም ባሰብሽ እንጂ:: ከእግዚአብሔር ጋር እየተጋፋሽ ነው ያለሽው:: ማራ ከእርሱ ርቀሽ ትዘልቂያለሽ? ማሰብሽም ይገርማል:: ለምን የደረሰብሽን ብቻ ታስቢያለሽ፤ ያደረገልሽን መጥፎ ነገር ብቻ የሆነልሽንም አስቢ እንጂ:: ያን ሁሉ መከራ አይቶ እንዳዳነሽ ከሲዖል እንዳወጣሽ አትርሺ ::

ከልጅነትሽ ጀምሮ እስካሁን የማይከፈልበትን ግን ሕይወት የሆነውን አየር እየመገበ እንዳኖረሽም አትርሺ ይሔም ነገር ቢደርስብሽ ከበስተኋላው ከሚመጡ ብዙ ነገሮች እንደጠበቀሽ አትዘንጊ:: የሰው ትልቁ ችግር ውለታውን መርሳቱ ነው እንዲህ መሆን የለብሽም:: ነገሮች ሁሉ በትዕግሥት ቀስ በቀስ ይለወጣሉ:: ደግሞ እርሱ የሰጠውን እርሱ ራሱ ነው

የሚጠግነው:: አለማዊ ጥበቦች ሊ
ያድኑሽ ሊያጽናኑሽ ያልቻሉትም ሊ
ዚህ ነው:: አንቺ ስታለቅሺ
ስታዝኚ እግዚአብሔር ደስ የሚለው
ይመስልሻል? ጨካኝ እኮ አይደለም::
በባሕርይው ኃዘን የማይስማማው ቢ
ሆንም ካንቺ በላይ ያዝንልሻል፤
ካንቺ በላይ ስላንቺ ያስባል ደግሞ
ሁሉንም ነገር ሊያደርግልሽ ይች
ላል:: ግን ጊዜውን ይጠብቃል፤ ለሁ
ሉም ጊዜ አለውና ምናልባት አሁን
ስላዘንሽ ብሎ ሁሉን ቢያደርግ ጊ
ዜው አልሆነ ይሆናልና መጨረሻው
አያምርም ግን እሱ በፈቀደው ጊዜ
ሲያደርግ ሁሉ እስከ መጨረሻው የ
ሠመረ ይሆንልሻል:: ማራ ለምን
አትታገሺውም?»

«እስከ መቼ?» አለች ቅስሟ
ስብር ብሏል::

«ጊዜው እስኪደርስ በቃሽ እስኪ
ልሽ:: እስከ ዛሬ ብዙ ተሰቃይተሽ
ኖረሻል ማን ያውቃል በቃሽ የሚ
ልበት ጊዜው ደርሶ እንደሆነ? ለምን
ለመጽናናት ተስፋ ለማድረግ አትሞ
ክሪም:: ያለፈውን እያሰቡ መተከዝ
መፍትሔ አይሆንም:: ይኼ ሁሉ
በምድር ላይ የምታይው ሰው ምንም
ፈተና ያልገጠመው ይመስልሻል?
ሁሉን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጥቶ
እንጂ ፈተና ያልገጠመው ማንም
የለም:: አንቺ ላይ ብቻ የደረሰ አድ
ርገሽ አታስቢው:: ሁላችን ፈተና
ይገጥመናል:: ካንቺ የተለየነው ግን
መውጫውን ፍለጋ አምላካችን ተስፋ
አድርገን በመለመናችን ነው:: ያለፈ
ውን ቢያስቡት ምንም ለውጥ አይ
ኝም:: ራስሽን ነው የምትጐጂው:
ከእግዚአብሔር ጋርስ ስለ ተጣላ
ማን ይጐዳ? እሱ ነው ወይስ አንቺ
እሱ አይጐዳም የተጐዳሽው አንቺ
ነሽ:: ለቅዱስ ጳውሎስ የመውጊ
ያውን ብረት ብትቃወም የሚብሰው
በአንተ ነው አይደል የተባለው:
ስለዚህ መበርታት በጸሎት መትጋት
ነው ያለብሽ:: ያልፉል የማያልፍ
ነገር የለም፡ «ወይ ያ ጊዜ» የም
ትይበት ወቅት እኮ ይመጣል:
የእግዚአብሔር የማዳን ጊዜ ሩቅ
አይደለም:: የምታርፊበት ጊዜም
ቅርብ ነው ብቻ ጸልይ::»

ምክርም ተግሳጽም ነበር:
እነዚህን ሁሉ ሳወራ በዝምታ ታ
ምጠኝ ነበር:: ምን ያህል እንደ ተ
በለቺኝ ባላውቅም ጥያቄም ሳት
ይቀኝ ምንም ሳታወራ ተሰናብታ
ወጣች::

ከዚያን ቀን ወዲህ ማ
በሳምንት ቢያንስ ሦስት ቀን እየመ
ጣች የእግዚአብሔርን ቃል እን
ገር እንጫወት ነበር:: ቀስ ቢቀስ
የተለያዩ አባቶችና ወንድሞች



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የጻፏቸውን መጻሕፍት ማንበብ፣ የስብከት ክሮችን ማድመጥ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድና ልዩ ልዩ ጉባኤዎችን መካፈል ጀመረች:: ሙሉ ለሙሉ ባትለወጥም ከዕለት ወደ ዕለት የምታሳየው ለውጥ ጥሩ ነበር:: ለዚህም ሥራው መክሮ አስተምሮ ላረጋጋት እግዚአብሔር ምስጋናን አቀረብኩ::

ማክሰኞ ቀን በሳምንት ከምንገናኝባቸው ቀኖች አንዱ ነበር:: ማራ በጠዋት ነበር የመጣችው:: ከሁሉ ቀን ዛሬ በጣም ደኅና ትመስ ላለች፡፡ «ሥራህ አያልቅ ምን አድር ገህ ይሆን ደግሞ?» እያልኩ ልትነግረኝ የመጣችው ምን እንደሆነ በጉጉት እጠባበቅ ጀመር::

«ዛሬ ትልቅ ነገር ልነግርህ ነው የመጣሁት» አለቺኝ ፊቷ በፌገግታ በርቷል:: ተመስገን ያ በእንባ ጠቁሮ የነበረ ፊት ... ምን ይሣንሀል አምላኬ ልጅህን አገኘህ አልኩ አሁንም በልቤ ከልቤ:: ልትነግረኝ የመጣችው ጥሩ ነገር እንደሆነ ስለተረዳሁ ለመስማት ይበልጥ ጓጓሁ::

«ስሜ ማራ ሳይሆን ይዲድያ ነው::» አለቺኝ::

«እኔም ሁልጊዜ ስምሽ ይገርመኝ ነበር ታዲያ ለምን ማራ ተባልሽ?»

«ኑኃሚን መጽሐፈ ሩት ላይ ለምን ማራ በሉኝ እንዳለች ታስታውሳለህ አይደል? እኔም እግዚአብሔር አስመርሮኝ ነበረና ራሴን «ማራ» አልኩት «ቤተሰቦቼ ግን .ይዲድያ ብለው ነበር የሰየሙኝ:: በደረሰብኝ መከራ ሁሉ ግን በእግዚአብሔር የተወደድኩ ሳይሆን የተመረርኩ የሆንኩ ስለመሰለኝ ስለ መራራው ሕይወቴ ስል ራሴን «ማራ» አልኩት:: ካሁን ወዲያ ግን «ማራ» ሳይሆን «ይዲድያ» እንድትለኝ የምሬቴ ጊዜ አልፎአልና» አለቺኝ:: ዛሬ የኀዘን ሳይሆን የደስታ እንባ በዓይኗ እየሞላ::

በጣም ስደነግጥና ስደሰት ዝምታን እመርጣለሁ አሁንም ከደስታዬ የተነሳ ዝም አልኳት:: እሷም ይሄንን ተረድታ ነው መሰለኝ

«ዛሬ ተራው የእኔ ነው:: እኔ ነኝ የማወራው» አለችና ንግግርዋን ቀጠለች::

«በመጀመሪያ እንደዛ ሳማርረው የነበረውን እግዚአብሔርን አንተን የመሰለ ጥሩ መንፈሳዊ ወንድም ስለሰጠኝና ከምንም በላይ ደግሞ እንደዛ ሳማርረው ሳጣጥለው ያልተቆጣኝን ለጥፋት አሳልፎ ያልሰጠኝን፣ ትዕግሥቱን ያሳራቀብኝን አምላኬን አመሰግነዋለሁ:: በሁለተኛ ደረጃ አንተን ወንድሜን አመሰግንሀለሁ:: ለእኔ መጽናኛ እንደሆንከኝ እግዚአብሔር ለአንተ መጽናኛ፣ ረዳት፣ ጓደኛ ይሁንህ:: ከዚህ በፊት የመከርከኝ ነገር ሁሉ ትክክል ነው በተቻለኝ አቅም ሁሉንም ለመፈጸም እንድችል እጸል ያለሁ:: ውለታህን ሁሉ እግዚአብሔር ይክፈልህ አንተ ጥሩ ጓደኛዬ ነህ»... ከእንግዲህ ራሴን ችዬ መቆም አለብኝ «ዳ...ዴ» ያልኩበት ወራት አልፎአል መንገዱን አሳይተህኛል፤ ስለዚህ ካሁን ወዲያ ትለቀኝና ራሴ መራመድ እጀምራለሁ:: እግዚአብሔር ይመስገን የደረሰብኝ ነገር ሁሉ ጠንካራና ብዙ ነገሮችን ዐዋቂ አድርጎኛል ይሄን የተረዳሁት አሁን ነው:: ስለዚህ ካሁን ወዲያ ልጅነት የለም:: ራሴን መቻል አለብኝ፣ በጾም በጸሎት በስግደት እየተጋሁ ኑሮዬን «ሀ» ብዬ ልጀምረው ወስኛለሁ:: እግዚአብሔርም ኃይሉን ያልብሰኝ:: ግን በክርስትና ሕይወት መፈተን ያለ ነውና ከእዛ እጠበቅ ዘንድ እስከ ዛሬስ ለሆነው ስላደረግኩት ኃጢአቴ ደግሞ ይቅር እባል ዘንድ፣ ልብ እገዛም ዘንድ ምን ላድርግ?» መልሴን ትጠባበቅ ነበር::

«አሁን የክርስቲያን ጥያቄ ጠየቅሽ እኅቴ፤ ቅዱስ ዳዊት በድሎ ናታን በተላከበት ጊዜ ምን ላድርግ? ነበር ያለው:: አንቺም ይህንን መጠየቅሽ በእውነት ውስጥሽ መለወጡን ያሳያል:: እግዚአብሔር ይመስገን:: እንግዲህ እኔ የምልሽ እስከ ዛሬ በደካማነቴ ያለቺኝን አካፍዬሻለሁ:: እሱ በወደደ በፈቀደ ጊዜ ጠርቶ አቅርቦሻል:: ከእንግዲህ ወዲያ እኔ የምልሽ አንድ ነገር ብቻ ነው:: «እኔ ዝቅ ዝቅ ልል እሱ ከፍ ከፍ ሊል ይገባዋል» አይደል ያለው መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ:: ስለዚህም ምን ላድርግ ላልሽው ወደ መምህረ ንስሐሽ ቅረቢ:: የሚሉሽንም ሁሉ አድርጊ ነው የምልሽ:: ከአባቶች ጋር ተማከሪ ካሁን በኋላ ለሚኖርሽ ሕይወት መካሪ መሪ የሚሆኑሽ ንስሐ አባትሽ ናቸው:: በርቺ በጸሎት ትጊ... ::»

ብዙ ብመክራት ደስ ባለኝ ነበር ግን ከደስታዬ ብዛት የተነሣ ከዚህ በላይ ምንም ልላት አልቻልኩም:: በዛ ላይ ለመሄድ ስለተነሣች ብዙ አላልኳትም «ቀኝም ግራም ሳልል ወደ አባቶች እሄዳለሁ ንስሐ እገባለሁ፣ ከአምላኬም እታረቃለሁ:: በልጅነቴ ዐውቀው እናፍቀው የነበረው ፍቅሩ የዕጣኑ ሽታ፣ ከበሮው ዝማሬው ሁሉ ነገር ናፍቆኛል:: ትዝ እያለኝም ለመሄድ እንጓለሁ ቀጥታ ንስሐ ገብቼ ወደ ቤቴ እመለሳለሁ:: እግዚአብሔር ይርዳኝ ጸልይልኝ:: አንተም እግዚአብሔር ይስጥህ» አለችና እጇን ለሰንብት ዘረጋችልኝ:: ጨበጥኳትና «እግዚአብሔር ይርዳሽ ይከተልሽ» አልኳት ፊቷን አዙራ ነጐደች...

ለመጀመሪያ ቀን ስንተዋወቅ የተጓዘችበትን የ4 ኪሎ መንገድ ወደ ታች ትታ ሽቅብ ወደ 6 ኪሎ በመሳቀቅ ሳይሆን በልበ ሙሉነት ዛሬ ትወጣው ጀመር:: እኔም እመ ብርሃኑን በመንገዷ ሁሉ ትከተላት ዘንድ እና እንደዚህ ዓይነቱን በሴቶች ላይ የሚደርስን ነገር ከሀገራችን ታርቅልን ዘንድ ድርጊቱን ለምንፈጽመውም ልቡናን ትሰጠን ዘንድ በኃጢአተኛ አንደበቴ «እናታችን እርጂን» ልላት ወደ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በፍጥነት አመራሁ...::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

## ዶሮ ጮኸ

ማቴ.26÷74

*ወርቅነሽ ቱፋ*

ነጋ መሰለኝ ሌሊቱ
ሰዓቱ ተገባደደ
አምላኬን የካድኩበት
ጊዜው ከነፈ ነጐደ
የዶሮው ጩኸት
ሲያበቃ
እኔም ከእንቅልፌ
ስነቃ
ጌታዬ እጆቹ ታስረው
በሽላቾቹ ፊት ቆሞ
ዓለም ሲዘባበትበት
ከቀያፋ ቤት ዕድሞ
በፍቅር እያስተዋለኝ
በዚያ ብርሃን ፊቱ
እሞትልሻለሁ ገና
አለኝ በአስተያየቱ
እኔም ቀና ብል
ከጐለጐታ
ጌታዬን ላየው
ላንድ አፍታ
የተዘረጉት እጆቹ
ለኔ መሆኑ ሲገባኝ
በንስሐ እንባ እየታጠብኩ
ከመስቀሉ ሥር
አለሁኝ::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከዋሸራ እስከ ገረገራ

*ዲ.ያሬድ ሃ/መድኅን እና አሉላ ጥላሁን*

*ባለፈው እትማችን ከዘርዐ ቡሩክ እስከ ጨጎዴ ሐና በሚል ርእስ የጻድቁ አቡነ ዘርዐ ቡሩክን ዜና ሕይወት ከዳሰስን በኋላ የጨጎዴ ሐናን ደብር፣የዋድላ መንገድ የቅኔ ምስክር ቤተ ጉባኤን ጠቅላላ ገጽታ ማስተዋወቃችን ይታወሳል:: በዚህ እትማችን ደግሞ የጽሑፉ አቅራቢዎች ካቆሙበት በመቀጠል የጉዞ ማስታዋሻቸውን የመጨረሻ ክፍል ያቀርቡልናል::*

ዬኔታ ያሬድ እስከ ቅድስት ሐና ድረስ እያዘኑ ሸኙን:: በዐይናቸው እየተከተሉ ተሰናበቱን:: ወደ ዋሸራ እያመራን ነው:: መንገዱ አስቸጋሪ ነው፤ «ሕዝቡ የከተማ ሰው ሲያይ ግራ ሊገባው ይችላል እንዳይጣላችሁ» ብለው ፈርተዋል:: ስለዚህ አንድ ተጨማሪ ተማሪያቸውን ሰጡንና ጉዞው ተጀመረ:: አሉላ ትንሽ ስላረፈ እግሩን ሻል ብሎታል ቢሆንም ግን ያዝማድረጉን ጨርሶ አልተወውም:: ጨጎዴን ለቀን ወጣንና መንገዱን ተያያዝነው::

የተነሣነው ሦስት ሰዓት ከጠዋቱ ነበር:: ለስድስት ሰዓት ያህል ተጉዘን ዘጠኝ ሲል አረፍ ብለን ስንቃችንን ተቋደስናት፤ በአንድ ምሳ አለቀች:: ከዚያ መንገድ ጀመርን:: እረኞች በየቦታው ገርሟቸው ያዩናል:: አንዳንዶም እናንተ ምንድናችሁ? ይሉናል:: በድካም ላይ ሲጠይቁን ሆድ ስለሚብሰን ቅን አንመልስም፤ «ሰው ነን» ብለናቸው እናልፋለን:: ሊያስፈራሩን ቢሞክሩም አልፈራንም፤ ፈርተን የት ሊደረስ ባይሆን ደፈር ማለት ይሻላል ብለናል::

አሥር ሰዓት ገደማ አንድ ትልቅ ተራራ እየተንሸራተትን ወረድን መውረጃ መንገዳችን ዙሪያ ጥምጥም ስለሆነብን በሽርተቴ ተያያዝነው:: ከተራራው እንደ ወረድን ሞላ /ትንንሽ/ ልጆች ከበቡን:: ሜዳ ስለነበር የንግላል ተኝተናል:: መጥተው እያዩን ያወሩን ጀመር:: በሩቅ የሠርግ ጨዋታ ይሰማል:: የምን ሠርግ ነው አልናቸው ጓደኞቸው እያገባ መሆኑን ነገሩን:: የአምስትና የሰባት ዓመት ልጆች ስለሆኑ ጓደኞቸው በማግባቱ ተገረምንና ጠየቅናቸው:: ይባስ ብለው ሁላችንም አግብተናል አሉን:: ጉድ ፈላ! በዚህ ዕድሜያቸው ሁሉም ተድረዋል:: ቤተሰብ ኃላፊነቱን ወስዶ የሚፈጽመው ጋብቻ እንዲህ ሲፈጥንም ችግር አለው:: ኋላ ነፍስ ሲያውቁ ላይስማሙ ይችላሉ፤ ሲዘገይም ችግር ነው:: ቤት እሠራ መኪና ቀረ፤ እየተባለ ሲቆይም ሕግ ሊጣስ ይችላል:: ለማንኛውም በጊዜው የሚጠቀም ዕደለኛ ነው ብለን አለፍን::

ሜዳውን እንዳቋረጥን መንደር አገኘን:: በጣም ደክሞናል ÷ ውኃ ጠምቶናል:: ስለዚህ ወደ አንድ ጎጆ ጠጋ አልንና ተጣራን:: አንዲት ልጃገረድ ወጣች:: የሚጠጣ ውኃ እንድትሰጠን ለመናት÷ ምንም አልተናገረችን÷ ገባች÷ ከዚያ መልስ የለም:: ብንጠብቅ ብንጠብቅ ሰው የለም:: ግራ ገባን:: ኋላ ላይ ቀና ብለን ስናይ በግድግዳው ጠርዝ አንድ ዓይን ብቻ ብቅ ብሎ ያየንና ጥልቅ ይላል:: በግድግዳው ስናየው ዞረና ወደ መስኮቱ መጣ:: በቤታቸው መስኮት በአንድ ዓይናቸው ያዩንና ይደበቃሉ:: ለካስ ፈርተውን ነው:: እንኳን ውሃ ሊሰጡን ምን ጉድ መጣብን ብለዋል:: ምናችንን ፈርተው ነው ብለን ተያየን፤ የከተማ ሰው መሆናችን በራሱ የሚፈጥረው ነገር አለ:: በዚያ ላይ አሉላ ፀጉሩ ተንጨብርሮ ሲታይ እንኳን እነርሱ እኔም የግድ ሆኖብኝ እንጂ አንዳንዴ እፈራዋለሁ:: የሚሰጠን አጥተን ውኃ እንደጠማን ጉዞ ጀመርን:: ኋላ አንዲት እናት አጋጣሚ አግኝተው ይዘውን ገቡ፤ በሚገባ አስተናገዱን «ኢይኃድጋ ለሀገር ዘእንበለ አሐዱ ኄር፤ ሀገርን ያለ አንድ ደግ ሰው አይተዋትም» ብለን አለፍን::

ወደ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ገደማ ነው:: ዋሸራ ገባን:: የቅኔዋን ዓምባ የእነማዕበል ፈንቴን ሀገር አየናት:: ትንሽ መንደር ናት:: ቤተ ክርስቲያኑ ከመንደሩ ባሻገር ስለሆነ መጀመሪያ ወደ መንደሩ ነበር የገባነው:: እዚያ እንደገባን ሰው ሁሉ ከየቤቱ እየወጣ ማየት ጀመረ፤ ምን መጣ ተባለ:: መሃል ከተማው ደረስን ጠየቅን:: ቤተ ክርስቲያኑ ወዴት ነው? አልን:: ይሄኔ የቀበሌው ሊቀ መንበር ታጣቂ አስከትሎ መጣ:: «መታወቂያ» አለን አወጣን:: «ለምን መጣችሁ?» ቤተ ክርስቲያን ልናይ ነው አልነው:: «አሁን መሽቷል በዚያ ላይ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መቅረብ አይቻልም፤» ደነገጥን:: ዬኔታ ያሬድ የሰጡን ተማሪ ቀበል አድርጎ «መሪጌታ ዘለዓለም ጋር ነው የምንሔደው» ብሎ መለሰ:: ሊቀ መንበሩ የመሪጌታ ዘለዓለምን ስም ሲሰማ ዝም አለ ግን አልተፈታም:: ገጹን እንደቋጠረብን ጥሎን ሄደ:: ውኃ ጥም ስላለቀቀን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ከመሄዳችን በፊት ወደ አንድ ሻይ ቤት ጎራ አልን:: ግማሹ ሻይ ሌላው ጠላ አዘዘን:: በዚህ መሐል ሊቀ መንበሩ ተመልሶ መጣና ቆሞ አየን፤ ሁላችሁም ሻይ ብቻ ነው እንዴ የምትጠጡት» አለን:: «ጠላም» አለ አልነው:: ምን ለማለት እንደፈለገ ገብቶናል:: ጠላ የሚጠጣ ከሌለ «መንጤ» /መናፍቃን/ ልትሆኑ ትችላላችሁ ነው:: ጠላውን እነሣንና ተጎነጨን:: ስካር እንጂ መጠጥ መች ተከለከለ የምንል መሆናችን ገባው:: ጥሎን ሄደ:: ይሄ ነገር ያስፈራል ስለተጠራጠሩን ነገር ሊፈልጉን ይችላሉ ብለን ወጣንና ወደ መሪጌታ ቤት አመራን:: መሪጌታ ዘለዓለም የቆሎ ተማሪው ዘመዳቸው ኖሮ አዩትና ሳሙት:: ከዚያ ስለ እኛ ሲነግራቸው ትንሽ አቆሙን:: ጥያቄ በጥያቄ አደረጉን:: መቼም እርሳቸው ካላስገቡን የት እንደምናድር እናውቀውም:: አለቀለን ማለት ነው:: ግን እርሳቸውም አልከፋብን:: ጠያይቀው ሲጨርሱ እርሳቸው ቤት በሰላም አደርን:: ጠዋት የዋሸራ ቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ዐየናት:: እስቲ ከዚህ በኋላ ስላለው ነገር ከአሉላ ጋር ልተዋችሁ::



የዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ገዳም

መሪጌታ ዘላለም ጌታሁን ገ/ሕይወት የዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳም የድጓ ምስክር ናቸው:: ተወልደው ፊደሉን ቆጥረው ዜማውን ጮኸው ቅኔውን የተቀኙት እዚያው ዋሸራ ነው:: ለ12 ዓመት ከመንፈቅ በትምህርት ዓለም ካሳለፉ በኋላ ከባልንጀራቸው ከመምህር ወልደ ሚካኤል ጋር በመሆን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በ200 ጠገራ ብር በገዙት ያልተመለከተ /ቦሃ ዘር/ የአገር መጽሐፍ -ድጓ- በ1953 ዓ.ም. ከቤተ ልሔሙ ሊቀ ምሁራን አምሳሉ መርሻ ዘንድ ብቃታቸውን አስመስክረው፤ የድጓውን ዐዋጅና ይትበሃሉን ለመጠንቀቅ /ለማጣራት/ ሁለት ዓመት ሙሉ እየጻፉ ሲያመለክቱ ከቆዩ በኋላ በ1955 ዓ.ም. ወንበር ዘርግተዋል፡፡ የዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳም ቤተ ክርስቲያን የአብነት ት/ቤትን ትምህርት ሚኒስቴር ስለሚያውቀው ለቅኔው ለድጓውና ለትርጓሜው መምህር የአበል አከፋፈል ስኬል አውጥቶ 376 ብር በየወሩ ያስብላቸው እንደ ነበር፤ ከ1989 ዓ.ም. ወዲህ ግን ይህ እንደ ተቋረጠ መሪጌታ ዘላለም አጫውተውናል፡፡

መሪጌታ ዘላለም «ዋዛ ለቁም ነገር » በሚለው አዝማች ንግግራቸው እያለፉ ከሚያደርጓቸው ትምህርታዊ ጭውውቶች መካከል ድጓ ስለሚለው ቃል ትርጉም እንዲህ ብለውናል፤ «ድጓ ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ የደረሰው የዜማ መጽሐፍ ነው፤ ስለ ቃሉ አመጣጥ ድጓ ያለውን ለቤተ ክርስቲያን ሥርጓ ይሉት ነበር፡፡ ሥርጓ ማለት ጌጧ ሽልማቷ ማለት ነው፡፡ ይኸውም የድጓው መጽሐፍ «አሠርገዋ ለምድር በሥነ ጽጌያት፣ አሠርገዋ ለሰማይ በከዋክብት ብሩህ» ያለውን ይዘው ነው፡፡ ደግሞም አላልተው ድጓ «የቤተ ክርስቲያን መቀነቷ፣መታጠቂያዋ» ብለው ይተረጉሙት ነበር፡፡ ነገር ግን ከባላባት ሲረዱት ይጣራልና ከዘመናት አንድ ቀን አንድ ሰው አድዋ ከተማ ጨው ጭኖ መጥቶ ለከብቶቼ ገፈራ ለመግዛት ሲፈልግ «ድጓ ስጡኝ» አለ ይባላል፤ «አንተ ሰው ድጓ ምን ያደርግልሃል?» ቢሉት፣ «ለከብቶቼ አበላዋለሁ» ቢላቸው ብልህ አይታጣምና «ዓይነቱን አሳየን» አሉት፡፡ እርሱም በአውድማ የተቆለለ የጤፍ አበቅ አሳይቶ «ድጓ ያልሁት ይኸን ነው» አለ ይባላል፡፡ እነርሱም የአበቁን ብዛትና ደቃቅነት የድጓንም ብዛቱንና የጽሕፈቱን ረቂቅነት አመዛዝነው «ድጓ ማለት ረቂቅ ማለት ነው» ብለው ተረጎሙት፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ድጓ-ደግደግ-ቀጠነ ከሚለው ግሥ የወጣ ነው እየተባለ በሊቃውንት ዘንድ ይነገራል፡፡»

በመሪጌታ ዘላለም አቅራቢነት ከተዋወቅናቸው መምህራን መካከል አንዱ መሪጌታ ጥዑመ ልሳን ልየው ይባላሉ፡፡ መሪጌታ ጥዑመ ልሳን ልየው የደብሩ የቅኔ መምህር ሲሆኑ ባለ ትዳርና የሁለት ልጆች አባት ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአማካይ 150 ተማሪዎች አሏቸው፡፡ ይህ ቁጥር ቢያንስ 40 እና 50 ሲበዛ ቢውል ደግሞ ከ200 አያልፍም፡፡ ይሁንና ዋሸራ በዋንኛነት የቅኔ ምንጭና መገኛ እንደ መሆኗ ከዓመታት በፊት 2000 ያህል ደቀ መዛሙርት የከተሙባት እንደ ነበረች መዛግብት ይጠቁማሉ፤ ዛሬ ግን ስንኳን እኒህን ያህል ደቀ መዛሙርት 40 እና 50ዎቹን እን ኳን ለመመልከት አልቻልንም፡፡ ምክንያ ቱም አንድም ቀደም እንደ ገለጥነው ወቅቱ የሠርግ /ዘመነ መርዓዊ/ በመሆኑ ተማሪ ለቀለብ ስብሰባ በመውጣቱ ሲሆን በዋንኛነት ግን የልመናውን እንጀራ ለማግኘት ሁኔታዎች ባለመቻል ስለተወሰኑ ተማሪው ቤተ ጉባኤውን ጥሎ ስለተሰደደ መሆኑን ከመምህራኑ አንደበት አድምጠናል ፡፡

እነ ማዕበል ወልደ ሕይወት የመሪጌታ ዘላለም አባት የሆኑት እነ መሪጌታ ጌታሁን ገ/ሕይወት ያስተምሩበት የነበረውን ሥፍራ ተመልክተናል፡፡ የዋሸራ ተማሪዎችን ጎጆ ከሌላው የሚለየው ከየጉጆው ጋር የተሠሩ ዶሮ ቤቶችን ማየታችን ነው፡፡ በዚህም ተማሪው በዶሮ ርባታ እንቁላል እየሸጠ የሚያስፈልገውን ለመሸመት የሚያስችለውን ገቢ እንደሚያገኝ ተረድተናል፡፡ የቤተ ጉባኤውም ግድግዳ ምርጊት የለውም፤ ይኸውም በሌሊቱ የቅኔ ጉባኤ ተማሪው በእንቅልፍ እንዳያናውዝ ተብሎ ነው፡፡


ከዚህ በተቀረ የዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳምን አመሠራረት ታሪክ መሪጌታ ዘላለም ጌታሁን በንባብ ካስሙን የልሳን ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መጽሔት ቁጥር 12/1987 ዓ.ም. እትም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

## የዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳም

አያሌ ሊቃውንትና እልፍ አእላፍ ደቀ መዛሙርት የነበሩባት ጥንታዊቷ ባለ ታሪክ ገዳም ደብረ ምዕራፍ ዋሸራ ማርያም የምትገኘው በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት በቋሪት ወረዳ ነው፡፡ ገዳሟ የምትገኝበት ስፍራ ታላላቅ ኰረብታዎችና ሰንሰለታማ ተራራዎች የሚበዙበት አካባቢ ሲሆን በቀድሞ ዘመን አሁን ገዳሟ ያለችበት ሜዳማ ስፍራ ታላቅ ባሕር የተንጣለለበት ሐይቅ ነበር፤ ያ ተንጣሎ የነበረው ባሕር ከብዙ ጊዜያት በኋላ በደጋግ አበው መነኰሳት ተባርኮ በነበረበት ቦታ ላይ ታቦተ ማርያም እንደምትተከል ትንቢት ይነገር ነበር፡፡

በአንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት

በአጤ ድልነአድ ዘመነ መንግሥ
መጨረሻ በ900 ዓ.ም ገደማ በዚህ ባሕ
አጠገብ ቁራ ገደል እየተባለ በሚጠራ
ዋሻ ጥግ ታቦተ ራጉኤል ተተክሎበ
ነበር፡፡ ይህ ቦታ በጠፍንት ከቆየ በኋ
በአጤ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥ
በ1265 ዓ.ም ገደማ ወደ ቆላማው ክፍ
ተዛወሮ አሁን ጦር መስቀያ እየተ
በሚጠራው ገደል አጠገብ ለሁለተኛ ጊ
ታቦተ ራጉኤል ተተክሎ ከቆየ በኋ
በአጤ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥ
በ1304 ዓ.ም የወንድ ገዳም ሆኖ ነበር
በኋላም እስከ አጤ ዓምደ ጽዮን ዘመ
መንግሥት ቦታው ጠፍ ሆኖ የቆየበ
ጊዜ ጀምሮ ዋሻ ራጉኤል እየተባለ ይ
ራ ነበር፡፡ ዋሸራ የሚባለው ስምም ከዚ
ልሳን የተገኘ እንደሆነ ይነገራል፡፡ አ
ዳንድ አበው ሲናገሩ ደግሞ ቦታው ዋ
ራ የተባለበት በገዳሙ ሥርዓት መ
ረት ማንኛውም የመንግሥት አካል በ
ሁ ቦታ በወራሪነት ገብቶ ድንኳን ተክ
ሠራዊቱን በሕዝብ ቤት መርቶ እን
በላና እንዲጠጣ ማድረግ አይፈቀድም
አንድ ንጉሥ ግን በድፍ ረት ገብ
ድንኳን ተክሎ ከላይ የተከለ ከለው
ነገር ሊፈጽም ሲል ከሸራ የተሠራ
ድንኳኑ በነፋስ ኃይል ተነቃቅሎ በገ
ወንዝ ስለ ወደቀበት «ዋ! ሸራዬ፣ ወይ
ሸራዬ» እንደ ማለት ዋሸራ ተባ
ይላሉ፡፡ በዚህች ቦታ በቀድሞ ዘመ
/10ኛው መ.ክ.ዘ/ አንድ ድህሪም የሚባ
ተመራማሪ ነበር፡፡ ይህ ተመራማሪ ፊ
ስፋ በዋሸራ ባሕር አጠገብ በቁራ ገደ
ጫካ ይቀመጥ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊ
ብቻ ብቅ እያለ ትንቢት ይናገር ነበር
ትንቢቱም የዋሸራ ባሕር እንደሚደርቅ
በቅዱሳን ጸሎት ባሕሩ ወደ የብስነ
ተለውጦ ታቦተ ማርያም ከሰሜን ኢት
ጵያ ተራራማ ዋሻ መጥታ እን



/የዋሸራ የአብነት መምህራን/





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ምትተከል የሚገልጽ ነበር። ይህ ደገኛ ሰው ከትንቢቱም በተጨማሪ በቅኔውም የተደነቀ ሲሆን የመጀመሪያው የዋሸራ ቅኔ ደራሲ እርሱ ነበር። ከትንቢታዊ ቅኔውም፤

*ርኢኩ ሕልመ ዘኮነ መንክረ*
*ዕዝራ ዘርዕ ወነጸረ*
*ባሕርኒ ርእየት ወኃየት ድኅረ ወለብሰት ምድረ*
*ወኮነት ደብረ* የሚል ይገኝበታል።

በዚያ ጥንታዊ ዘመን የግእዝ ቅኔ አደራረስ የተጀመረ በዚህ መልክ ነበር። ድህሪም የተባለው ተመራማሪ ፈላስፋ እንደ ዕዝራ ሱቱኤል ከኀሊናው ምሥጢር የማመንጨት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለነበረው ድህሪም ዕዝራ ሱቱኤል ተብሎ እንደ ተሰየመ ይነገራል። በዚህ በዋሸራ በአጤ ሰይፈ አርእድ ዘመነ መንግሥት ታቦተ ጊዮርጊስ ተተክሎ ነበር። ከሰይፈ አርእድ ዘመነ መንግሥት ትንሽ ቀደም ብሎ በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የሰማዕቱ የቅዱስ ጊዮርጊስ ዜና ገድል ከውጪ ስለ መጣና ፈጣን ተራዳኢነቱም ስለ ታወቀ ታቦተ ጊዮርጊስ በዚያው በዋሸራ ተተክሎ መቆየቱ ይነገራል።

በዚህ ቦታ ታቦተ ማርያም የገባችው በአጤ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው። ታቦተ ማርያምን ከሰሜን ኢትዮጵያ ተራራ ዋሻማ ሥፍራ ይዘው የመጡ ቅዱሳን አበው መነኰሳት ከጥር 1 እስከ ጥር 21 ቀን ሱባኤ ከገቡ በኋላ ሦስት ሱባኤ ሊጨርሱ አንድ ቀን ሲቀራቸው ቀድሞ በደጋግ አበው መነኰሳት በተነገረው ትንቢት መሠረት ባሕሩ ወደ ውስጥ ሰርጎ የብስ ከሆነ በኋላ ከመካከሉ ላይ ጥቂት ውኃ ቀለበት ሠርታ ታየች፤ በመጨረሻው የሱባኤ ቀን ባሕሩ ሰምጦ የብስ ከሆነበትና የመጨረሻዋ ውኃ እንደ ቀለበት ምልክት ሆና ከታየችበት ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ታቦተ ማርያምን አስገብተዋል። የዋሸራ ማርያምን ደገኛነት የተረዱት አጤ ዘርዐ ያዕቆብም በቦታዋ እየተገኙ ውዳሴዋን ሲያደርሱ እመቤታችን በገሃድ ታነጋግራቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ደብረ ምዕራፍ ዋሸራ ማርያም ገዳም «አጤ ቤት÷ ቤተ አጼጌ» እየተባለች እስከ መጠራት ደርሳ ነበር። ይህም መሠረት ሆኖ በአጤ በዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት «ከአበያ እስከ በሊያ አፈ ጉባኤ» የሚል የክብር ስም ለገዳሟ ተሰጥቷት ነበር።

በዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳም «መንክር ኃይላ» የምትባል የእመቤታችን ሥዕል አለች። ይህቺ ሥዕል ተናጋሪዋ ሥዕል በመባል ስትታወቅ ሥዕሏም ቅዱስ ሉቃስ ከሣላቸው የድንግል ማርያም ሥዕለ አድኅኖዎች አንዷ ናት። በቀድሞ ዘመን የነበሩ ምእመናን በንጽሕናና በቅድስና ሆነው ይህችን ሥዕል ሲማፀኑት ሥዕሏ ቃል በቃል በማነጋገር ሐሳባቸውን ትፈጽምላቸው ነበር። በጎንደር ዘመነ መንግሥት «መንክር ኃይላ» ለአጤ በካፋ ያሳየችው ተአምር አለ። ይህም አጤ በካፋና ወለተ እስራኤል የተባሉ ሴት በፈጠሩት አለመግባባት ወለተ እስራኤል ከአጤ በካፋ ሸሽተው ዋሸራ ገዳም ደወል ደውለው ገቡ። አጤ በካፋም በዋሸራ ማርያም ገዳም እንደ ሚገኙ በሰሙ ጊዜ ወደ ገዳሙ መምህርና መነኰሳት መልእክተኛ ልከው ወለተ እስራኤልን አስረው እንዲልኩላቸው ቢጠይቁ የገዳሟ ሥርዓት በሚያዝዘው መሠረት ደውለው የገቡ በመሆናቸው አንሰጥዎትም አሏቸው። በዚህ ጊዜ አጤ በካፋ ተናድደው «ሺ ጦር ሆኜ እመጣለሁ፤ ከእጃችሁም ነጥቄ እወስዳታለሁ» ብለው ወደ ገዳሟ ሲልኩ የገዳሟ መምህርና መነኮሳቱም «እኛም ሺህ አቡነ ዘበሰማያትና ሺህ ጸሎተ ማርያም ይዘን እንጠብቀዎ ታለን» ብለው መልስ ሰጡ። በዚህ ጊዜ አጤ በካፋ ሺ ጦር ይዘው ከገዳሟ ወለተ እስራኤልን ነጥቆ ለመውሰድ በመጡ ጊዜ ደረቅ ፈፋ እየተባለ በሚጠራው ተራራማ ሥፍራ ሲደርሱ ጦር የተጫነው ፈረስና በቅሎ እየደነበረ አስቸገረ፤ የገዳሟ ገጽታም ከንጉሡና ከሠራዊቱ ተሠወረች። ወዴት እንደሚሄዱም ለንጉሡ ተነገራቸው። ሠራዊቱ መበጣበጥ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ «እመቤቴ ማርያምሚ ይቅርታ አድርጊልኝ» ብለው ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ። ከቤተ መንግሥታቸውም እንደ ደረሱ በስልፍ ቀን የሚለብሱትን የክብር ቀሚስና የወርቅ ለምድ ለገዳሟ ሰጥተዋል። በዚህም ምክንያት እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ «የበካፋ እመቤትሚ መንክር ኃይላ» እየተባለች ትጠራ ነበር። ከዚያም በኋላ በአጤ በካፋና በወለተ እስራኤል መካከል እርቅ ስለ ተፈጠረ ወለተ እስራኤል ከዋሸራ ገዳም ሄደው ሞጣ ጊዮርጊስን ተክለዋል።

በደብረ ምዕራፍ ዋሸራ ማርያም ገዳም ከ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የግእዝ ቋንቋ ሕግጋት የሆኑት ዐቢይ አገባብ ደቂቅ አገባብ ንኡስ አገባብ እንደዚሁም ዕርባ ቅምርና ሌሎችም የገዳሟ ባለ ታሪክ ሊቃውንት የደነገጓቸው ልዩ ልዩ የግእዝ ቋንቋ አዋጆች የተነገሩባት ስትሆን በአገባቡና በዕርባ ቅምር አዋጆች ተመድበው በተመጠኑ ቀለማት ተሳክቶ በዜማና በንባብ ተስማምቶ በትርጉምና በምሥጢር ተያይዞ የቅኔ ትምህርት የተጀ መረባት ጥንታዊትና ባለ ታሪክ ቦታ ናት።

የቅኔን ትምህርት በምሥጢርና በያሬዳዊ ዜማ ስልት የወሰኑትና ማንኛውንም ግሥ ከንኡስ አንቀጽ ወደ ቀዳማይ አንቀጽ መልሰው የገሠሡት የታላቁ ሊቅ የአለቃ ተክሌ የትውልድ ሥፍራ በሆነችው በደብረ ምዕራፍ ዋሸራ ማርያም ገዳም ከመጀመሪያው የቅኔ ፈጣሪ ከድህሪም/ዕዝራ ሱቱኤል/ ጀምሮ በንጽሕናቸውና በቅድስናቸው አቻ የማይገኝላቸው አያሌ ሊቃውንት ነበሩባት። የዋሸራ ሊቃውንት በአብነት መምህርነታቸው የሚታወቁት በቅኔ ብቻ አልነበረም። በሐዲሳት፣ በብሉያት፣ በፍትሐ ነገሥት፣ በመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ በመጽሐፈ መነኰሳት ትርጓሜም ጭምር ስለነበር በዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳም አራቱ ጉባኤያት ተዘርግተው ደቀ መዛሙርት በዝተው ይኖሩ ነበር። የአብዛኞቹ ሊቃውንት ሕይወት በምናኔ የተዋጠ ስለ ነበር ሊቃውንቱ በጉባኤያቸው ካሉት ደቀ መዛሙርት ብቃት ያለው ደቀ መዝሙር ሲያገኙ በጉባኤያቸው /በወንበራቸው/ እየተኩ ውዳሴ ማርያም ደግመው ከፍጹምነት ደረጃ የደረሱት ብዙዎች ናቸው። የሚገርመው ነገር እኒያን የመሰሉ በተማሪዎቻቸው ተለምኖ ከሚመጣ ቁራሽ በቀር ከማንም ምንም ሳይፈልጉ በመንኖ ጥሪት መኖራቸው ነው።

በደብረ ምዕራፍ ዋሸራ ማርያም ገዳም የነበሩት ሊቃውንት የሚቀኙአቸው ቅኔዎች የምሥጢረ ሥጋዌና የነገረ መለኮት ትምህርት ያለባቸው ነበሩ። በጎንደር ዘመነ መንግሥት የዋሸራ የቅኔው ጉባኤ ምስክር የነበሩት መምህር ቀስሙ በትሩፋትና በትምህርት የታወቁ በእመቤታችን በድንግል ማርያም በዕድሜዋ ልክ 64 ጊዜ በቀን በቀን ውዳሴ ማርያም የሚደግሙ ብቃት የነበራቸው ደገኛ መምህር ነበሩ። ስለ እኒህ መምህር በገዳሟ ታሪክ እንደ ተጻፈው ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን በአንድምታ ተርጉመው ለሊቃውንት ያቀረቡ መምህር ቀስሙ ናቸው።

መምህር ቀስሙ ውዳሴ ማርያም ሲደግሙ በገዳሟ ያለችው ሥዕለ እግዝእትነ ማርያም /መንክር ኃይላ/ በግልጽ ታነግራቸው ነበር። መምህር ቀስሙ ዘዋሸራ እመቤታችን ድንግል ማርያም ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ፀንሳ በነበረችበት ጊዜ በመልኳ ላይ ይታይ የነበረውን የኀብረ አምሳል መለዋወጥ በመግለጽ የተቀኙትን አንድ መወድስ ቅኔ ለማዘከር ያህል፦

*ተኃብዐ ዮናስ በከርሠ አንበሪ*
*በቀዳማዊ ዘመን ወለስብእ ኢትህብአ*
*በመልክአ ዘውስጥ ዮናስ መልክአ አንበሪ ዘአፍአ*
*ባሁቱ ይትአጸብ ልበ ዮሴፍ*
*በነገር እንግዳ ኃቤሁ ዘመጽአ*
*መልክአ ወላዲት እንተ አፍአ*
*በመልክአ ሕጻን ዘወስጥ ተኃብዐ ጊዜ መርዓ*
*ዮሴፍ ሂ እስከነ ክህደ ሃይማኖተ ድንግል መልክአ*
*አርአያ ወላዲት ቅብዐቢረሌ*
*ለአብርሆ ገጽ እስመ ተቀብአ*
*ወነገረ ዘንተ ከመ ያስ ተዓጽብ ሰብአ*
*እስመ አርአያሃ ለወላዲት በአርአያ ወልድ ተጸውአ*

በማለት ጌታ በእመቤታችን መልክ በመለኮታዊ ኅብረ አምሳል እየተለዋወጠ ይታይ ስለነበርና ወንጌላዊው ማቴዎስ «ወኢያእመራ ዮሴፍ እስከ አመ ወለደት ወልደ ዘበኩራ፤ የበኩር ልጅዋን እስከወለደች ድረስ አላወቃትም» ያለው የእመቤታችንን ገጽ /ፊት/ ቅዱስ ዮሴፍ በአንድ ዓይነት መልክ ሊያውቅ አልቻለም ተብሎ የተነገረው በጽንሷ ጊዜ መሆኑን ከላይ በተጻፈው ቅኔአቸው ገልጸዋል።

ይህን ቅኔ መምህር ቀስሙ የሚቀኙበት ጊዜ ሲደርስ መንኖ በበረሃ ለሚኖር ለአንድ ባህታዊ እመቤታችን ተገልጻ ዋሸራ ሂድና ቀስሙ የሚቀኙልኝ ቅኔ ስላለ ለጎንደር ሊቃውንት አምጥተህ ንገራቸው ብላ ስላዘዘችው ያ ባህታዊ ብዙ ቀን ይፈጅ የነበረውን መንገድ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

በአንድ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተጉዞ ደብረ ምዕራፍ ዋሸራ ማርያም በመድረስ መምህር ቀስሙ ሲቀኙ ሰምቶ ይዞ በመ ሄድ እመቤታችን እንዳዘዘችው ለጎንደር ሊቃውንት ነግሯቸዋል።

በዚህች የተቀደሰች ባለ ታሪክ በሆነችው ዋሸራ ደብረ ምዕራፍ ማርያም ገዳም እንደ መምህር ቀስሙ ስመ ጥር የሆኑ ሊቀውንት እነ መምህር ወልደ ሩፋ ኤል፣ እነ ሣልሳይ ጌዴዮን፣ እነ አለቃ ተክሌ፣ እነ ዘቦቱ ወንድ ሁነኝ /የደብረ ኤልያስ ድምህ ገነት እነ መምህር ገብረ ማርያም/፣ እነ መምህር ወልደ ሚካኤል፣ እነ ግጨው ገብሬ፣ እነ አለቃ ደለለ ካሣ፣ እነ ማዕበል ፈንቴ፣ እነ አለቃ ነቢየ



/የማንብ ኪዳነ ምሕረት ጥንታዊት ደብር/

ልዑል፣ የታላቁ የአለቃ ተክሌ የልጅ ልጅ እነ መምህር ሰዋስው፣ እነ መሪጌታ ጌታሁን ገብረ ሕይወት እነ መሪጌታ ወር ቅነህ፣ እነ መሪጌታ በየነ ባያብል የመሳ ሰሉት በጸሎታቸውና በትሩፋታቸው አገር የሚጠቅሙ አበው ሊቃውንት ነበሩ።

ከዋሸራ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ የምናየው ግንብ ኪዳነ ምሕረትንና ጎንጅ ደብረ ጽላሎ አማኑኤልን ነው። ዋሸራ እስከ ስድስት ሰዓት ቆይተን ወጣንና ጉዞ ቀጠልን። ወደ አሥራ ሁለት ሰዓት አንዳ ት መንደር ደረስን። ገረገራ ትባላለች። ከዚያ የአንድ ብር ከሃምሣ መደብ ተከ ራይተን አደርን። ጠዋት ወደ ግንብ ኪዳነ ምሕረት አመራን። ግንብ ኪዳነ ምሕረት ሦስት ሰዓት ላይ ደረስን። ይህች ጥንታ ዊት ቤተ ክርስቲያን ከሩቅ ሲያዩዋት ግርማዋ ያስታውቃል፡ ጥንታዊ መሆን ይመሰክራል። ጠጋ አልንና ዐየናት። በሩ ዝግ ነው። ተጣራን። ዘበኛው ወጡና ዐ ዩን። «ለእናንተ መግባት አይፈቀድም።» አሉን። «ሌላው ይቅርና ቢያንስ ተሳል መን እንውጣ» አልናቸው። አልፈ ቀዱልንም። ስለዚህ አሉላ ዛፍ ላይ ወጣ። ፎቶ ግራፍ አነሣ። ቤተ ክርስቲያኒቷን በውጭ ሆነን ተሳልመናት አለፍን። አሉላ፣ ስለ ግንብ ኪዳነ ምሕረት የምትናገረው ይኖርሃል?

አዎ፥ የግንብ ኪዳነ ምሕረት ጥንታዊ ደብር የተመሠረተችው በ13ኛው መ.ክ.ዘ በአጤ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ነው። ከ724 ዓመት በፊት ማለት ነው። ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ከማ ርጀቱ የተነሣ ፈርሶ የአጥቢያው ምእመን በቅጥሩ የሚገኘውን የጥድ ዛፍ በመቁረጥና የጭቃ ጡብ በማዘጋጀት ጥገና አካሂዶ ለታል። በደብሩ የሚገኙት መጻሕፍትና ሌሎች ቅርሶች በልዩ ልዩ ተባዮች መበ ላታቸውና መቀደዳቸው፣ በመብረቅ መቃጠ ላቸው እንዲሁም ዝርፊያ የወቅቱ ዐበይት ችግሮች መሆናቸውን የይልማና ዴንሣ ወረዳ ባሕልና ስፖርት ጽ/ቤት የ1986 ዓ.ም. ጥናት ይጠቁማል። ዲ.ያሬድ ብትቀጥል።

ከግንብ ኪዳነ ምሕረት በኋላ ያመ ራነው ወደ ጎንጅ ጽላሎ ነው። ሥራችን መጓዝ ሆኗል። አሁን ከቋሪት ወረዳ ወደ ይልማና ዴንሣ ወረዳ የገጠር ቀበሌዎች ገብ ተናል። ወደ ስድስት ሰዓት ላይ ጎንጅ ጽላሎ ደረስን። የጎንጅ ደብረ ጽላሎ አ ማኑኤል ገዳም የሚገኘው በይልማና ዴንሣ ወረዳ ጽላሎ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ነው። የተመሠረተው በአጤ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት /13 መ/ክ/ዘ/ ነው። መሥራቹም የአጤ ፋሲል ልጅ ጻድቁ ዮሐንስ ናቸው። መቼም ጎንጅ ሲነሣ አጭር አገባቡና ከባድ የሆነው የጎንጅ ቅኔ ፍልስፍና አመጣጥ፡ የቅኔው ጥበብ ሲነገር ደግሞ አብነቱ ተዋናይ የሚታወስ ነው።

«ደብረ ጥበብ» የምትባለው የደብረ ጽላሎ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ትታያለች። የጾመ ድጓ ተማሪዎች በየቦታው ይጮኻሉ። ጎጆዋቸው በዙሪያው ይታያል። በመካከላቸው አለፍን። ዳዊት ያስተዛዝላሉ፡ «ፍካሬ ዘጻድቃን ወዘኃጥአን» ሲሉ ሰማን «መዝሙር ዘዳዊት ሃሌ ሉያ» አልናቸው «ብፁዕ ብእሲ»ን አሉ፤ «ወዘ ኢቆመ» ብለን መለስን። እንዲህ እየተ ባባልን እየዞርን እየመለስን እነርሱም እየጮኹ መዝሙር አንድ አልቆ ሁለትን ዘለቅን። አቀባበል የተደረገልን በመ ዝሙር ነበር። ከዚያ ቤተ ክርስቲያን ደረስንና ተሳልመን ገባን። እንደ ገባን በስተግራ መቃብር ቤት አለ። ዕቃችንን አስቀምጠን ተጠጋነው። ገጽታው ግን ማረከን። የምናየው የመቃብር ቤት ኢ ትዮጵያዊቷ ዳግማዊት ሆሜር የተባሉት የቅኔ መምህርት የእማሆይ ገላነሽ ሐዲስ ነው። ለጎንጅ የቅኔ አገባብ ምስክር ሆነው ከ50 ዓመት በላይ ከጉባኤ ሳይለዩ በርካታ ሊቃውንት ያፈሩት እማሆይ ገላነሽ ያረፉት ሐምሌ 12 ቀን 1978 ዓ.ም. ነበር። ሊቅነታቸውን የተገ ነዘበው ሕዝብም «ጎንጅና ጽላሎ አንድ ነው መሬቱ፤ ጽላሎ ይበልጣል አንቺ ያለሽበቱ» ብሎላቸዋል። በሲሚንቶ የተ ለሰነ አነስተኛ ቤት ነበር። በሩ ብረት ነው። ስንመለስ ልናየው አሰብን። ወደ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ቀረብን። ዙሪያው በሸንበቆ ታጥሯል። በረንዳው ሸምበቆ ነው። በትላልቅ የጥድ እንጨት የተሠሩ ትላልቅ በሮች ላሉት ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ሰገድን። ከዚያ ዞረን ዐየ ነውና እንዴት እንደምንዘግብ መነጋገር ጀመርን። በዚህ መሐል አንድ ሰው እየ ፎከረ መጣ። «ምንድናችሁ? የማንም ቦላሌ ታጣቂ እንዴት ይደፍረናል» አለና ዐየን። ጤነኛ ስላልመሰለን ዝም አልነውና ውይይታችንን ቀጠልን። ነገር ግን አላቋረጠም። «ኑ ውጡ ብያለሁ ውጡ፤ እንዴት ማንም መጥቶ ይደፍረ ናል» አለ። ከዚያ ያኾጎደጉደው ጀመር። ይናገራል ይናገራል ማቆም የለም። ንግግሩ ፋከራም ሽለላም አለ በት። ዝም ብለን ማየት ጀመርን። ዝምታችን ስላናደደው «ለማንኛውም መጣሁ ፡ ጠብቁኝ» ብሎን ሄደ። የቆሎ ተማሪዎች ደነገጡ። አብረውን ከአዴት የሄዱት ስንበት ተማሪዎችም እንውጣ አሉን። አንዱ ተማሪ ጠጋ አለና «የቤተ ክርስቲያኑ ጠባቂ ነው። መሳሪያ ሊ ያመጣ ስለ ሄደ ቶሎ ሽሹ» አለን። አሉላ ፎቶ ግራፍ እንዲያነሳ ተነጋገርንና እኔ ሳየው ተከተልኩት። ቤቱ እዚያው ቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ነው። እየጮኸ ግቢውን አልፎ ቤቱ ገባ። ቤተ ክርስቲ ያኑን፣ የእማሆይ ገላነሽን መቃብር፣ ተ ማሪውን ያገኘነውን ሁሉ በከፍተኛ ፍጥ ነት ፎቶ አነሣን። አሉላ ሰውየው መጣ ልህ እየተባለ ብልጭ ድርግም ያደር ጋል። ያገኘውን ሁሉ ያነሣል፤ ዶሮው፣ በጉ፣ ላሙ ሁሉ ዕድል ቀንቶት ሳይነሳ አይቀርም። በዚህ መሐል አንስተን እንደ ጨረስን ሰውየው ራሱን ጨርቅ አምሞና ጠ ምጥሞ ለፀብ ተዘጋጅቶ በረት ይዞ ወጣ። ፈጠን ብለን ከቤተ ክርስቲያኑ ተለየንና በእርሱ በር እያለፍን መጓዝ ጀመርን። «ሂዱ በፍጥነት ውጡልን፤ እኛ እዚህ ሆነን ያልጠ በቅነውን ቅርስ ከሸዋ ድረስ መጥታችሁ ልትጠብቁ ነው? አሁን ሳትዋረዱ ብትሄዱ ይሻላል። እደፋችኋለሁ» ብሎ እየደነፋ ቀረበን። እግዚአብሔር ይዞልን እየዛተ በሩ ቅ ቀረ።

/ወደ ገጽ 13 ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አቡነ ሐራ ድንግል ዘፎገራ

*መምህር ተስፋ ማርያም ዓለማየሁ*
*እና ግርማ ኤልያስ*



በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት በጣና ሐይቅ ዙሪያ የሚገኘው ሜዳማ ሀገር ያፈራቸው ታላቅ ጻድቅ አባት ናቸው:: በስማቸው ጽላት ተቀርጾላቸዋል:: ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በስማቸው ታንጸው ይቀደስባቸዋል ይውለስባቸዋል:: የእኚህ ጻድቅ ገዳም ከባሕር ዳር አልፎ ወደ ጎንደር በሚወስደው መንገድ አሥር ኪሎ ሜትር ላይ ሲገኝ እዚያው በፈዋሽነቱ የሚታወቀው ጠበላቸው ይገኛል::

አቡነ ሐራ ድንግል አባታቸው የራማው ቄስ ገበዝ ዮሐንስ እናታቸው የላጉናው ባላባት ልጅ ወለተ ጊዮርጊስ ይባላሉ:: የተወለዱት ጥቅምት 19 ቀን 1540 ዓ.ም ነው:: ሐራ ድንግል የተባሉትም በተጠመቁበት ዕለት ነው:: ሐራ ማለትም ጭፍራ÷ሠራዊት ማለት ነው::

የአቡነ ሐራ ድንግል ወላጆች ሦስት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆች የወለዱ ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱ በቅድስናቸው የታወቁት ጻድቁ አቡነ ሐራ ድንግል ናቸው:: አቡነ ሐራ ድንግል ገና ከመወለዳቸው በፊት ቄስ ገበዝ ዮሐንስና ባለቤታቸው ወለተ ጊዮርጊስ "እንግዲህስ ልጅ ከሰጠኸን ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግልና ለቅድስና የሚመረጥ ልጅ ስጠን" በማለት ይመኙ ነበር:: በዚህ ምኞታቸው መሠረት የተወለደው አቡነ ሐራ ድንግል በደም ግባቱና በቅላቱ በሥነ ውበቱ የተደነቀ ፊቱ እንደ ፀሐይ የሚያበራ ነበር::

ቄስ ገበዝ ዮሐንስና ባለቤታቸው ወለተ ጊዮርጊስ እንደ ተመኙት ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት የሚገባና የተባረከ ልጅ እግዚአብሔር ሰጥቶናል ብለው ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ:: ልጃቸውን በሚገባ እየተከባከቡ ካሳደጉት በኋላ በሰባት ዓመቱ ለመምህር ንባብ ሰጥተውት በወላጆቹ እየተረዳና እየተማረ በአካባቢው አደገ:: መንፈስ ቅዱስ አድሏቸው ወደ መንፈሳዊው ዓለም ቢመራቸው አባ ሐራ ድንግል ከትምህርት ቤት ወደ ወላጆቻቸው ቤት ሳይመለሱ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ከጎንደር ወደ ጎጃም ተሻግረው በደብረ ድማህ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ገብተው መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ቀጠሉ::

አቡነ ሐራ ድንግል እስከ አርባ ዘመናቸው ድረስ በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እየተማሩ ብዙ ዘመናትን አሳለፉ:: ብሉያትንና ሐዲሳትን አጠናቅቀው በመማር ይበል የተባለላቸው የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቅ ለመሆን በቁ:: አቡነ ሐራ ድንግል ገና በጎጃም ትምህርት ቤት ሳሉ አባትና እናታቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ሰሙ:: ከጎጃም ወደ ጎንደር ፎገራ ሄደው የወላጆቻቸውን ሀብትና ንብረት በሙሉ ለነዳያን መጽውተው ወደ ጎጃም ደብረ ድማህ ተመለሱ:: አባ አጽቀ ድንግል በሚባል ኤጲስ ቆጶስ አማካይነት መዓርገ ምንኩስና ከተቀበሉ በኋላ ከጎጃም ወደ ሸዋ ተሻግረው በደብረ ሊባኖስ ገዳም በምናኔ ተቀመጡ::

አባ ሐራ ድንግል በደብረ ሊባኖስ ገዳም መንነው ሲቀመጡ አርከ መርዐዊ የተባለ የእናታቸው ወንድም ከፎገራ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሄዶ አገኛቸው:: «ወንድማችን አባ ሐራ ድንግል እኛ ቤተ ሰቦችህ አንተ በአጠገባችን ብትቀመጥልን የዓይን ተስፋ ትሆነናለህና ከአጠገባችን ሳትርቅ በተወለድክበት ቀበሌና ደብር እንድትቀመጥ አብረን ወደ ሀገራችን እንሂድ» ሲል ለመናቸው:: አባ ሐራ ድንግል ግን መናኝ መነኩሴ ከቤተሰቡ አጠገብ መቀመጥ የለበትም በማለት የአጎታቸውን ጥያቄ አልተቀበሉትም:: አጎታቸው ግን እጅግ በጣም ፍቅርና ናፍቆት በተመላበት መልኩ ለመናቸው:: አቡነ ሐራ ድንግልም አጎታቸውን ላለማስቀየም ሲሉ «እንግዲያስ በተወለድኩበት ቀበሌና መንደር ሳይሆን ትንሽ ራቅ ወደ አለች ቦታ የራሴን ገዳም መሥርቼ እንድቀመጥ ሀገሬ ከደረስኩኝ በኋላ በተወለድክበት መንደር ተቀመጥ ብለህ አንተም ሆንክ ሌሎች ዘመዶቼን እንዳታስቸግሩኝ ቃል ግባልኝ» ሲሉ ጠየቋቸው::

አጎታቸውም አባ ሐራ ድንግል ባቀረቡት ሀሳብ መሠረት ተስማምተውና ቃል ኪዳን ተገባብተው ከሸዋ ደብረ ሊባኖስ ተነሥተው ፎገራ ደረሱ:: ከዘመዶቻቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ አቡነ ሐራ በተወለዱባት አውራጃ በደቡብ ጎንደር በፎገራ ወረዳ ደራ ከተባለው አካባቢ ቀስቀርያ በተባለች ኮረብታማ ቦታ የራሳቸውን ገዳም መሠረቱ::

አቡነ ሐራ ድንግል ቀስቀርያ በተባለች ቦታ በደረሱ ጊዜ ያች በረሃማና በደን የተሸፈነች ገዳም በዱር አራዊት የተመላች ማለትም



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዝሆን፣ አንበሳ፣ ነብር፣ ክርከሮ እንደዚሁም ሌሎች የተለያዩ የዱር አራዊት በየዓይነታቸው ሞልተውባት ነበርና ይህችስ ለገዳማውያን ኑሮ የምትመች የጽሞና ገዳም ናት ብለው ለገዳምነት መርጠዋታል:: በዚያም ከተራራው ሥር ባለችው የውኃ ምንጭ አካባቢ ትንሽ ማደርያ ጎጆ በመሥራት በጸሎትና በትሕርምት ተወስነው ገዳማዊ ኑሮአቸውን መኖር ጀመሩ::

አቡነ ሐራ ድንግል የቀን ሐሩር የሌሊት ቁር፣ በጣም አስፈሪ የሆኑ የአራዊት መንጋ ጩኸት ሳይበግራቸው በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጠባቂነትና ተራዳኢነት አናምርትና አናብስት እንደ ውሻና ድመት እየታዘዙላቸውና አብረዋቸው እየተኙ ብዙ ዘመናት ተቀመጡ:: ለዕለት ምግብ የሚሆናቸውን ሙዝና ሌሎችም አትክልቶችን እያለሙ ያች የአራዊት መናኸርያ የነበረችው ገዳም በአትክልት ልማት ወደ ምድረ ገነት ተለወጠች:: በቅርብና በሩቅ የሚኖሩ መናንያንና ምእመናን ወደ እርሳቸው እየመጡ ጸሎትና ቡራኬ በመቀበል ሲመለሱ የተቀሩት ደግሞ አብረዋቸው በምናኔ ይኖሩ ጀመር::

አቡነ ሐራ ድንግል በመሠረቱት ገዳም ውስጥ ያለሙትን አትክልት ከየአቅጣጫው ለሚመጡ ምእመናን በተወሰነ ገንዘብ በመሸጥ ከዚያ በሚያገኙት መጠነኛ ገቢ ነዳያንንና አካለ ስንኩላንን በመርዳት ይኖሩ ነበር:: በገዳሙ ውስጥ ባለችው የውኃ ምንጭ የተለያዩ ሕሙማንን እያጠመቁና መዝገበ ጠበሉን እያጠጡ የተለያዩ በሽተኞችን መፈወስ ጀመሩ::

ከዚህ በኋላ አቡነ ሐራና የመሠረቷት ገዳም በሕሙማን ፈዋሽነታቸው በመላ ሀገሪቱ ዝናቸው ተሰማ:: የተለያየ ደዌ ሥጋ የያዛቸውና ርኩሳን መናፍስት ያደሩባቸው ሰዎች ከየአቅጣጫው በመጉረፍ ከሕመማቸው ተፈወሱ:: በይበልጥ የሰዎችን ገላ እየቆራረጠ እጅንና እግርን ጉንዱሽ በማድረግ የሚታወቀው የሥጋ ደዌ የያዛቸው ሰዎች፣ በመላ አካላታቸው የነቀርሳ ሕመም የበሳሳቸው ሕሙማን ወደ አቡነ ሐራ እየቀረቡ በመባረክና ጠበል በመጠመቅ ይፈወሱ ጀመር:: በዚህ ምክንያት አቡነ ሐራ ድንግል በነገሥታትና በመኳንንት በካህናትና በመነኮሳት እንደዚሁም በምእመናን ዘንድ ከፍተኛ ክብርና ዝናን እያገኙ በመሄዳቸው በሕይወት ዘመናቸው ፈዋሴ ድውያን ቅዱስ ሐራ ድንግል በመባል ታወቁ::

በወቅቱ አጤ ሱስንዮስ ወደ ካቶሊክ እምነት የተለወጡበትና ኦርቶዶክሳውያኑን የሚያሳድዱበት ዘመን ነበር:: ሹመትና ሽልማት ፈላጊዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳንን ከየተደበቁበት ገዳምና ጥሻ እያደኑ በማውጣት ለሱስንዮስ ሰይፍ ያስረክቡዋቸው ነበር:: የአቡነ ሐራ ድንግል ዘመዳቸው የሆነ ሱስንዮስን ያገለግል የነበረው የፎገራ ሀገረ ገዢ «አባ ሐራ ድንግል ቀደም ሲል የጀመረውን እምነት ይዞ ድውያንን መፈወስ ከቀጠለ ንጉሥ ሱስንዮስ ያሥረኛል ከሥልጣኔ ያባርረኛል» ብሎ ሰጋ:: በቀጥታ ወደ ንጉሡ ሄዶ «በማስተዳድረው ሀገር አባ ሐራ ድንግል የተባለ መነኩሴ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነቱን ይዞ ሕሙማንን በመፈወስ ላይ ይገኛል» ብሎ ነገረው::

ንጉሡም አንድ ጊዜ ሰይጣን ተዋርሶታልና እንደ ልማዱ በሌሎች ቅዱሳን ላይ እንደ አደረገው ሁሉ አጋድሞ ለማረድ በአስቸኳይ ተይዞ እንዲመጣ ብሎ አዘዘ:: አቡነ ሐራ ድንግል በራሳቸው ዘመድ ወታ ደሮች እየተንገላቱ ወደ አጤ ሱስንዮስ ችሎት ቀረቡ:: ነገር ግን ንጉሡ የቅዱሱን መንፈስ እግዚአብሔር የተመላበት ግርማ ሞገስ ባየ ጊዜ «ይህንን መነኩሴ ከአጠገቤ አርቁልኝ ወዲያ ወደ መጣበት መልሱልኝ» በማለት አዘዘ:: አቡነ ሐራ ድንግል የንጉሥ ወቀሳ እንኳን ሳይደርስባቸው በኃይለ አምላካቸው በሰላም ወደ ገዳማቸው ተመለሱና የተለመደውን ድውያንን የመፈወስ ተግባራቸውን ቀጠሉበት::

አባ ሐራ ድንግል 'ማርያም ተስፋ' የተባለ ረድእ እና 'አመተ ማርያም' የተባለች መበለት ረዳቶች ነበሯቸው:: «ብርሃን» እየተባለ የሚጠራ እንደ ታዛዥ የሚያገለግላቸው አህያ ነበር::

ይህ 'ብርሃን' የተባለው አህያቸው ጠባቂ ሳይኖረው በረድኤተ እግዚአብሔር ይጠበቅ ነበር:: የተከተለው ሰው ሳይኖር ብቻውን ከገዳሙ ጭኖው ሲሰዱት ፎገራ ከተባለው ሀገር ደርሶ ይመለስ ነበር:: አመተ ወልድ የተባለች መነኩሲት ስትረዳቸው ቆይታ በደረሰባት ሕመም ምክንያት ብትሞት ወደ እግዚአብሔር ለመኑ:: እግዚአብሔርም «ይህች ነፍስ የሐራ ድንግል ናት ለምን አመጣችኋት አሁንም ስለዚች ነፍስ እነሆ ያዝናል፣ ያለቅሳል እና ከሥጋዋ አዋሕዳችሁ ወደ ቀደመው ኑሮዋ መልሷት» ቅዱስ ገብርኤልንም «ሂድና ሐራ ድንግል ወዳጄን በአንተ ያመኑትን ሁሉ ምሬልሃለሁ ብለህ ንገረው» ብሎ ሲያዝዘው ከምድር ሆነው በጸጋ ሰምተዋል:: ቅዱስ ገብርኤልም ወርዶ ነግሮአቸዋል:: አመተ ወልድም ከመ ቅጽበተ ዓይን ተነሥታለች:: አቡነ ሐራ ድንግል አትክልት እየተከሉ ፍሬውን በመሸጥ ገንዘቡን ለነዳያን ሲመጸውቱ እርሳቸው ግን ከመነኑበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ልብሳቸው አንዲት አጽፍ ነበረች:: በአንድ ወቅት ሌቦች ገንዘብ አላቸው በማለት ሊሰርቋቸው መጥተው ከቤታቸው መግባት አልቻሉም:: ከውጭ በተቀመጡበት መነጋገር አቅቷቸው እጃቸውንና እግራቸውን እንደታሠሩ ሁሉ ፈዝዘው ደንግዘው ጠዋት ተገኝተዋል:: አባ ሐራ ድንግል አድራጐታቸውን አውቀው «እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ወደ በጐ ነገር ይመልሳችሁ እንደዚህ ያለ ነገር እንዳ ትደግሙ ሂዱ» ባሏቸው ጊዜ ሌቦቹም በምሕረታቸው እየተገረሙ የእግዚአብሔርን ሥራ እያደነቁ ሂደዋል::

ሰይጣን በብዙ መልኩ ይፈታተናቸው ነበር:: ከጸሎት ቆይተው ሲመጡ ከመኝታቸው የሞተ መስሎ እንደ በድን ተኝቶ ይቆያቸው ነበር:: ይጥላቸውም ነበር:: በሴት አምሳል አብረን እንኑር እያለ ለማሳት በብዙ ሽልማት እና ጌጣጌጥ ስ ፈታተናቸው ማየ ጸሎታቸውን ቢረጩት «ንሣ ሂድ ኩልህ ደስ ይበልህ» ብሎ ከነ ድንኳኑና ከነሠራዊቱ ተነቅሎ ጢስ እሳት ከባሕሩ ሲወድቅ አባታችን በገዳማቸው ሆነው የባሕሩን መታወክ በጸጋ እግዚአብሔር ሰምተዋል:: ከዚያም ወዲህ ድውያን በይበልጥ ይፈውሱ ጀምረዋል:: በ1625 ዓ.ም በአጤ ፋሲል ዘመነ መንግሥት በሰማንያ አምስት ዓመታቸው ጥር 11 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እልፍ አእላፍ መላእክትን አስከትሎ ወደ ሳቸው መጣ:: ቅዱስ ገብርኤል እንደነገራቸው «ሐራ ድንግል ወዳጄ ሆይ÷ በአንተ ያመኑን ሁሉ እስከ ሰባት ትውልዳቸው ምሬልሃለሁ:: ስለእኔ ሥጋህን አድክመሃልና የብርሃናት ድንኳኖች ከተተከሉበት አገባልሃለሁ» ሲል ቃል ኪዳን ሰጥቶአቸዋል:: ሲሞቱም የሚቀበሩበትን ቦታ ለረዳታቸው ጽጌ ድንግል አሳይተውት ነበር:: ዘመዶቻቸውም ሰው ከሌለበት ቦታ ወንድማችንን አንቀብረውም እኛ ከምን ቀበርበት ራማ ወስደን እንቀብረዋለን በ ማለት አስከሬናቸውን ከሌላ ቦታ ለመቅበር በአሰቡ ጊዜም መብረቅ ወርዷል÷ ምድርም ተናውጣለች:: በመጨረሻም ቀደም ብለው ለጽጌ ድንግል በአሳዩት ቦታ ላይ ተቀበሩ:: ዘመዶ ቻቸውም ይህን ተአምር እያደነቁ ሄደዋል:: ከመቃብራቸውም ከምድር እስከ ሰማይ ዓምደ ብርሃን ተተክሎ ገዳሜንና መቃብሬን ጠብቂ ከሰው አትጨመሪ ብለው ያዘዟት አመተ እግዚእ የተባለችው እመ ምኔት የብርሃኑን ፋና ታይ ነበር:: ከዚያ ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድርስ ሕሙማኑ የመቃብራቸውን አፈር እየተቀቡ ከብዙ ሕመም እየተፈወሱ ይገኛሉ::

የአቡነ ሐራ ድንግል ጠበል ፈዋሽነቱ ለድሆች ብቻ ሳይሆን እንድናለን ብለው አምነው ለሚመጡ ነገሥታት፣ መኳንንት፣ ካህናት፣ መነኮሳት ለሁሉም ሰብአዊ ፍጡር ነው:: በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የነገሡት አጤ ዮሐንስ አራተኛ በአንገታቸው ላይ እባጭ ወጥቶባቸው ሠራዊታቸውን አስከትለው ወደ አቡነ ሐራ ገዳም ሄዱ:: የጻድቁን ጠበል ለሰባት ቀናት ከተጠመቁ በኋላ አንገታቸው ላይ ያበጠው ነገር ፈንድቶ ወዲያውኑ ፈውስ በማግኘታቸው ተደስተዋል:: በዚህም በዙሪያው ያለውን ሀገር በርስተ ጉልትነት ለገዳመ አቡነ ሐራ ከመስጠታቸውም በላይ በወቅቱ ይዘውት የነበረውን የራሳቸውን የወርቅ ዘውድ፣ ምንጣፍና አልባሳት በሙሉ ለአቡነ ሐራ ገዳም አስረክበው ወደ ቤተ መንግሥታቸው በሰላም ተመልሰዋል::

አቡነ ሐራ ድንግል ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ሥጋቸው ቢቀበርም በአካለ ሥጋ እያሉ የጀመሩት ሕሙማንን የመፈወስ ተግባር እስከ ዘመናችን ድረስ ቀጥሏል:: ጠበላቸው ወደር የማይገኝለት የደዌ ሥጋ ሕሙማን ፈውስ ስለሆነ በየጊዜው በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሕሙማን ወደዚያው ጠበል እየጎረፉ በመፈወስ ላይ ይገኛሉ::

*የአባታችን ጸጋና በረከት በእኛም ላይ ይደርብን:: አሜን::*





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ክርስትናና ዘመናዊነት

ዲ.ያሬድ ገ/መድኅን

ዘመን አልፎ ዘመን በተተካ ቀጥር ያልነበሩ ግኝቶች እየተከሰቱ እየተገኙ የምርመር ውጤቶች አዲስ ታሪክ እያመጡ ነገሮች ይቀያየራሉ፡፡ የሰው ልጅ ንቃተ ኅሊናም ያድጋል፡፡ ትናንት የማያውቀውን እያወቀ ያልደረሰበት ላይ እየደረሰ ዕውቀቱ ይሰፋል፡፡ በዚህ መሐል ክርስቲያኑም እንደ ዘመኑ በሚቀያየሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሚከሰቱበት ዓለም ውስጥ ስለሚኖር ራሱን ከዘመኑ ጋር አብሮ ያስኬዳል፡፡ ትናንት በእግር ተጉዞ በፈረስ ገሥግሦ እንዳላስተማረ ዛሬ በባቡር በመኪና በአውሮፕላን እየተጠቀመ በአጭር ጊዜ ብዙ ቦታዎችን ያካልላል፡፡ በዚህ መልኩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

መንፈሳዊ ሰው ዘመን ባመጣው መሣሪያ አይጠቀም፣ ቤተ ክርስቲያን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ራሷ አታስገባ የሚል አዋጅ የለም፡፡ ሥርዓት ካላፋለሰ ትውፊታችንን ካላስጣለ ዘመኑን መዋጀት መልካም ነው፡፡ በኮምፒዩተር ተጠቀማችሁ በትራክተር አረሳችሁ ብሎ የሚከስ ስለሌለ እነዚህን መጠቀም በደል አይሆንም፡፡ በጌታችን ዘመንም ሐዋርያት መረብ ጥለው ዓሣ ያጠምዱ ነበር፡፡ ይህ የዘመኑ ውጤት ነው፡፡ እርሱም ከእንግዲህ ሰው ታጠምዱ ዳላችሁ ብሎ መረባቸውን አስጣላቸው እንጂ ዓሣ ማጥመድ ኃጢአት ነው አላላቸውም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያነት እያገለገለም እንኳን ድንኳን ይሰፋ ነበር፡፡ ይህ ጥበብ የዘመናዊነት ውጤት ነው፡፡ በአጠቃላይ ድንኳን መስፋት፣ ዓሣ ማጥመድ፣ ቀለም በጥብጦ ብራና አልፍቶ ብርዕ ቀርጦ ጽሑፍ መጻፍ በሐዋርያት ዘመን ለነበረ ሕዝብ ዘመናዊነት ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን በየዘመኑ የቴክኖሎጂ ውጤት ተጠቅማለች፡፡ ከሥርዓቱና ከትውፊቱ ውጭ ያልሆነውን ልጆቿ እንዲጠቀሙበት ትመክራለች፡፡ «ዘመኑን ዋጁ» ትላለች፡፡ ስለዚህ ይህን ትውልድ ለማስተማር ይህን ዘመን መዋጀት ያስፈልጋልና መንፈሳዊ ሰው ዘመኑን መዋጀት አለበት፡፡

በዚህ መሠረታዊ ሐሳብ መነሻነት ዘመኑን መዋጀት እንዳለበት የሚያውቅ እንደ ዘመኑም ለመራመድ የሚጥር አለ፡፡ ይህ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን ዘመኑን ለመምሰል በሚያደርገው ሩጫ ክርስትናውን መላ እንዳያሳጣው መጠንቀቅም አለበት፡፡ ማስገባት ያለበትን እያስገባ ማስቀረት ያለበትን ካላስቀረ አስቸጋሪ ነው፡፡ ዘመንኛ ነው የተባለው ሁሉ ፈቃድ ተሰጥቶት ወደ ምእመኑ ይድረስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይግባ ከተባለ አደጋ ይኖረዋል፡፡

ዛሬ ዛሬ በየሥፍራው ምእመናንን ከሃይማኖት ለማፈናቀል የምግባር ሕጸጽ እንዲኖርባቸው ለማድረግ ያሰፈሰፉ ብዙ ፈተናዎች አሉ፡፡ መናፍቃኑ የሚሮጡት ሩጫ፣ አረማውያኑ የሚያፌጡት ፍጥጫ... ለዚህ ምስክር ይሆኑናል፡፡ ከዚሁ ጋር ዘመናዊነትም የራሱን ድርሻ እየተወጣ ነው፡፡ የምእመኑን ሕይወት ለመሸርሸር አስተዋጽዖውን ያበረክታል፡፡ ይህን ሐሳብ ግልጥ ለማድረግ በዘመናዊነት ሰበብ ኦርቶዶክሳዊ ለዛቸውን፣ የተቀደሰ ሐሳባቸውን፣ ትውፊትና ሥርዓታቸውን እየተነጠቁ ያሉ ምእመናንን ሕይወት እናያለን፡፡ እነዚህ ምእመናን «ዘመናዊ» ነን ብለው ፈተና ላይ የሚወድቁት በተለያየ መልኩ ነው፡፡ የተወሰኑትን ለማየት ያህል :-

## በአመለካከት

እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ አመለካከት አለው፡፡ እንደ እምነቱ ዓይነት እንደ ዕውቀቱ ስፋት እንደ ጠባዩ በጎነትና እልከኝነት የሚለያይ አመለ የራሱን ካከት ይኖረዋል፡፡ መንፈሳዊም ሰው በዚሁ የተለያየ አስተሳሰብ ባለው ዓለም ስለሚኖር አስተሳሰብ ቤተ ክርስቲያን ካስተማረችው ትምህርት አባቶች ከኖሩት ሕይወት ጋር የሚተያይ በመንፈሳዊነት የታሸ አስተሳሰብን ገንዘብ አድርጎ ይጓዛል፡፡ አመለካከቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበት ክርስትናውን የማያስነቅፍ ለተጠመቀባትና ለሚኖርባት ቤተ ክርስቲያን ምስክር የሚሆን ነው፡፡

ባለንበት ወቅት ይህንን ዘንግቶ ሠለጠንኩ በማለት ብቻ «በዘመናዊነት» ሰበብ አስቸጋሪ የሆነ አመለካከት ያለው ሰው አለ፡፡ እንዲህ ያለ ሰው ከዘመኑ ጋር የሄደ እየመሰለው የማይቆፍረው ጉድጓድ ስለሌለ ሳያውቀው ቤተ ክርስቲያንንም ይነቅፋል፡፡ ለምሳሌ አሕዛብና ስመ ክርስቲያኖች የጻፉትን አንብቦ «ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን ከሥልጣኔ ወደ ኋላ አስቀርታዋለች» ማለት አንዱ ነው፡፡ ትናንት ከትናንት ወዲያ እንዲሁም ዛሬ የሠራችውን ሥራ በዜሮ አባዝቶ ተጠያቂ ማድረግ ስሕተት ነው፡፡ እንዲህ ያለ ሰው ቤተ ክርስቲያን ለዚህች ሀገር የታሪክ የሥልጣኔ ምንጭ እንደነበረች እንዳያስብ በዘመናዊነት ሰበብ የሚያነባቸው ጽሑፎች ዓይነ ልቡናውን ይጋርዱታል፡፡

«እግዚአብሔር መጨከን ስለሌለበት ሃይማኖት ሁሉ ወደ ገነት ያደርጠሰናል፡፡ አንዱን ትክክል ሌላውን ስሕተት ነው ማለት አይገባም» የሚልም የዘመናዊነት አመለካከት አለ፡፡ «ዩኒቨርሳሊዝም– ሁሉም አንድ እግዚአብሔርን ስለሚያመልክ አንድ ነው፣ ሁሉም እምነት የራሱ እውነት አለው» የሚል አስተሳሰብ የሚመጣውም ከዚሁ ነው፡፡

## በሃይማኖታዊ አካሄድ

ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ተቀብሎ ያልገባውን ጠይቆና ተረድቶ እንደቀደሙት አባቶች መጓዝ አለበት፡፡ ከእኛ እንደ ተቀበላችሁት ወግና ሥርዓት ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን» 2ተሰ.3÷6 እንዳለ የአባቶቹን ወግና ሥርዓት ማክበር መጠበቅ አለበት፡፡ ቤተ ክርስቲያን በአባቶች ሥርዓትና ትውፊት ነውና፡፡ ስለዚህ ወደ እርሷ ሲመጣ አባቶቹን መምሰል ይገባዋል፡፡ ሥርዓቷን ማክበር ይጠበቅበታል፡፡ አንዳንድ ዘመናዊ ነን የሚሉ ሰዎች ግን ይህን ባለመረዳት ሥርዓት ካልተጣሰ ብለው ሲሟገቱ ይታያሉ፡፡ አንድ ወቅት ያጋጠመኝን ላጫውታችሁ፡፡ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ካሉት አብያተ ክርስቲያናት በአንዱ ነው፡፡ ክርስትና ቤት ኀራ እላለሁ፡፡ ከቅዳሴ በፊት ሰው ክርስትና ለማስነሣት ተዘጋጅተዋል፡፡ እኔም አቋቋመኝ ካለኝ ባነጀራዬ አጠገብ ቆሜ ቆየሁ፡፡ ካህናት መጡና ጸሎት ጀመሩ፡፡ ሁሉም ሕጻናቱን ለክርስትናው ጥምቀት ማዘጋጀት ጀመረ፡፡ በዚህ መሐል በፔርሙስ የሞቀ ውኃ ይዘው የመጡ ሁለት ሴቶችም ሙቅ ውኃቸውን አቀረቡ፡፡ ደንግጬ አየሁትና ምንድን ነው? አልኩ፣ መለሱልኝ ሙቅ ውኃ ነው፡፡ ፈልጋችሁ ከሆነ ለእና ንተም ልጅ ይበቃል» አሉኝና አረ ፉት፡፡

እንዲህ ያለውን አካሄድ ቤተ ክርስቲያን በዕንቁላሉ ካልቀጨችው ነገ በሬ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ «መዝሙሮቻችን በኦርጋን ይታጀቡ፣ ወደ ቤተ መቅደስ ከነጫማችን እንድንገባ ይፈቀድልን፣ ሴትና ወንድ አንድ ላይ ቆሞ ያስቀድስ፣ መለያየቱ ይቅር» የሚሉ ጥያቄዎች የመጡት ከዚሁ ከዘመናዊነት ጋር ተያይዘው ነው፡፡

ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ይህን የዘመናዊነት ጥያቄ እያስተናገዱ ስለ መጡ ዛሬ ግብረ ሰዶም ቢፈቅድስ ምናለ ተብለው ተጠይቀዋል፡፡ ፓስተሮቻቸውም የግብረ ሰዶማውያንን ጋብቻ ባርከናል እስከ ማለት ደርሰዋል፡፡ ሁለትና ሦስት ሚስት እናግባ የሚል ተከታያቸውንም ጥያቄ ለመመለስ በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ለነገሩ እነርሱ በአሸዋ ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ ምንም ቢሠሩ አይገርመንም:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ግን ይኽን ዓይነት ጥያቄ የሚያነሡ ልጆች ካፈራች ጉዞዋ ፈተና ላይ ይወድቃል:: ሥርዓቷ ይፋለሳል:: ትውፊቷ ይጣሳል:: በእንጭጩ መቀጨት ሳይቃጠል በቅጠል መባል ያለበትም ለዚህ ነው:: አልያ ነገ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶችን የቀላወጠ «ዘመናዊ» ነኝ ባይ ለምን ማለቱ አይቀርም::

## በአኗኗር

መንፈሳዊ ሰው ማንነቱን የሚገልጠው በቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለም:: በቤቱም ጭምር እንጂ:: ስለዚህ በመኖሪያ ቤቱ በሚኖረው ኑሮ መንፈሳዊነቱን ማስመስከር አለበት:: የአባቱ ልጅ መሆኑን የሚገልጽ አኗኗር ያስፈለገዋል:: ለምሳሌ የእንግዳን እግር አጥቦ ያለውን አካፍሎ አብልቶ አጠጥቶ ማስተናገድ አንዱ ነው:: ይህ በጎ ሥነ ምግባር ጌታችን በፍርድ ቀን ከሚጠይቃቸው ጥያቄዎች አንዱ እንደሆነም ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል:: /ማቴ.25÷45/:: ዛሬ ዛሬ ግን በዘመናዊነት ሰበብ እንዲህ ያለው አካሄድ እየተረሳ መጥቷል::

እንዲህ ዓይነቱ ጉዞ አብሮ መብላትን ብቻ ሳይሆን የታመመን መጠየቅ የሞተን መቅበር የመሳሰሉትን ከክርስትና ጋር የተያያዙ ባሕሎች ሊያስቀር ይችላል:: ኢትዮጵያውያን ደግሞ በዘመናዊነቱ ተውጠን ይህን ሁሉ ባሕል ካጣን «ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይቻላልን?» ኤር.13÷23 ከሚለው አምላካዊ ቃል ጋር መጋጨታችን ነው::

የባሕር ማዶው ሕዝብ በሩን ዘግቶ በነጠላ በመኖሩ ማኅበራዊ ሕይወቱ ፈተና ላይ ወድቋል:: መተዛዘን፣ መረዳዳት፣ መተዋወቅ ያልቻለ ኅብረተሰብ እየተፈጠረ ነው:: አንድ ወቅት ከባሕር ማዶ የመጣ ጓደኛዬ ያጫወተኝ ትዝ ይለኛል:: ሴትዮዋ ከሕፃን ልጇ ጋር ተከራይታ ነው የምትኖረው:: አንድ ዕለት ሐሸሽ /አደንዛዥ ዕፅ/ ወስዳ ትገባለች:: እንደ አጋጣሚ የወሰደችው ከመጠን በላይ ነበርና ልጇን ራት እያበላች በዚያው ራሷን ስታ ትወድቃለች:: የደረሰላት የለም:: ቆይታ ትሞታለች:: ልጁ ያለቅሳል አስተዋሽ ግን አላገኘም:: በዚህ መልኩ አድረው በማግሥቱ ወደ ማታ የልጁን ለቅሶ አንድ ጎረቤት ይሰማና ለፖሊስ ይደውላል:: ፖሊስ ከፍቶ ሲገባ እናት ሞታለች:: ልጁን መንግሥት ወሰደው:: እርሷንም ወስዶ ቀበራት:: ታሪኩ አለቀ:: ሰው ባለበት ዓለም ሰው አልባ ሆኖ መኖር ያሳዝናል:: በእኛም ሀገር ሳያውቁት ይህንን የማኅበራዊ ሕይወት ቀውስ ለማምጣት ነው አንዳንዶች የሚሯሯጡት በዘመናዊነት ሰበብ በራቸውን የሚዘጉት::

በቤተሰብ መካከል ለሚፈጠሩት ችግሮች አንዱ ምክንያት «ዘመናዊ ነን ባዮች» የሚፈጥሩት ችግር» ነው:: በወላጆቻቸው የሚቀልዱ የቤተሰብ ፍቅር የሌላቸው ልጆች ያፈራነው ዘመናዊነቱ ተፅዕኖ እያደረገብን ነው:: ስለዚህ ምንም ዓይነት ምቹ ኑሮ ቢገጥመው መንፈሳዊ ሰው ክርስቲያናዊ ባሕሉን እንዳይለቅ መጠንቀቅ አለበት::

## በአለባበስ

ልብስ ብቻውን የመንፈሳዊነት ምስክር አይደለም:: ነገር ግን ውስጣዊ ሕይወት ከተለወጠ በኋላ በውስጥ ያለው በአፍአም መታየት አለበትና ክርስትና በአለባበስም ይገለጣል:: ሳምራዊቷ ሴት ጌታችንን በአለባበሱ ለይታ አንተ የይሁዳ ሰው ነህ እንዳለችው:: ዮሐ.4÷9:: መንፈሳዊ ሰው በአለባበሱ ተለይቶ እገሌ ነህ መባል አለበት:: ቅዱስ ጳውሎስ በሚገባ ልብስ ይሸለሙ፤ /1ጢሞ.2÷9/ በማለት እኅቶቻችንን የመከረውም ለዚህ ነው:: ወንዱም የሚገባ ልብስ ሊለብስ ይገባል::

ዛሬ ዛሬ በተለይ ወጣት መንፈሳውያን «ክርስትና በልብ ነው በሚል ፈሊጥ ማስታወቂያ ስሌዳ ሲመስሉ ማየት ለምደናል:: አንድ ቀን የሆሊውድ ተዋናይ ሌላ ቀን ታዋቂ ዘፋኝ አንዳንዴም የታወቀ ሞዴሊስት እየመሰሉ ብቅ የሚሉ መንፈሳውያን አይጠፉም:: እነዚህ ወጣቶች በአንድ ልብ ክርስትናውንም ይፈልጉታል:: በሌላ በኩል የሚያውቁትን የፊልም ተዋናይ የመሆን ፍላጎትም አላቸው:: በዚህ የተነሣ ግራ የተጋቡ ይመስላሉ:: አንድ የማውቃት ወጣት ትዝ ትለኛለች:: አንድ ሳምንት ፀጉሯን በምናምን ነክራ ትመጣለች:: የምትለብሰው ልብስ ከፀጉሯ ጋር «ማች» የሚያደርግ ተብሎ ጥብቅብቅ ያለ ሱሪ፣ የልጅነቷ ከሚመስል ትንሽዬ ጃኬት ጋር ነው:: ይህን ልብስ ስትለብስ ሰውነቷን ምን ያህል እንደሚያጋልጠው እናስተውል:: ጓደኞቿ ዛሬ እገሌን መስለሻል ብለው አንድ የፊልም ተዋናይ ይጠቅሱላታል:: እንዲህ እንዲህ እያለች ሁል ጊዜ እገሌን መሰለሽ እንደ ተባለች ነው:: ራሷን የምትመስለው መቼ እንደሚሆን አይታወቅም:: በመሠረቱ በክርስትና መምሰል ያለብን ማንን እንደሆነ ተጽፎልናል::

## በአነጋገር

«ንግግራችሁ ሁል ጊዜ በጨው እንደ
ተቀመመ በጸጋ ይሁን» ቆላ.4÷6:: ክርስ
ቲያን ንግግሩ ጨዋታው ምክሩ በመን
ፈሳዊነት የታሸ መሆን አለበት:: ከሰላም
ታው ጀምሮ ከአንደበቱ የሚወጡ ቃላት
ለዛ ያላቸው ሃይማኖቱን ትኅትናውን የሚገ
ልጡ መሆን ይገባቸዋል:: የቀደሙ አባቶቻ
ችን ምክራቸው...የማይጠገበውም ለዚህ
ነበር:: ኀሊና የማይጎዳ የማይሻክር ስለነበረ
ነው::

ዛሬ በዘመናዊነት ሰበብ ጉራማ
ይሌ የሆኑ ቃላት ሲሰነዘሩ ማየት ጀምረ
ናል:: ሰላምታው እግዚአብሔር የሚመ
ሰገንበት መሆኑ ቀርቶ «በሃይ ሃይ» መተ
ካቱ በዚያ ላይ «ነፍሴ እወድሀለሁ፤ እወድ
ሻለሁ» በሚሉ ቃላት መታጀቡ ትርጉም
የሌለውና ምን ለማለት ተፈልጎ እንደተነገረ
ግራ የሚያጋባ እየሆነ ነው:: አንድ ሰው
እነኝህን ቃላት መጠቀም ያለበት ለማንና
ለምን እንደሆነ መረዳት አለበት እንጂ
ዘመናዊ ነኝ ተብሎ በየሜዳው ያገኘውን
«እወድሃለሁ ÷ እወድሻለሁ ፍቅሬ፣ ልቤ፣
አንጀቴ» ከተባለ ወዴት እየሄድን እንደ ሆነ
ማሰብ ይከብዳል::

ከሰው ጋር የቅዱሳንን ስሞች እየ
ቆረጡ በመጥራት በቤተ ክርስቲያናችን
ትውፊት በማይታወቅና እንግዳ በሆነ መን
ገድ «ፍቅርን» መቀራረብን መግለጥ የተለ
መደ ሆኗል:: ልደታ ማርያምን «ልደ
ትዬ».. በዓታ ለማርያምን «ባትዬ» መድኃ
ኔዓለምን «መድሽ» ማለት የተጀመረው ለዚህ
ነው:: በዚሁ በዘመናዊነት ሰበብ «ነቅተናል
ለማርያም» እየተባለ ነው:: ሲናገሩ ድራማ
የሚሠሩ የሚመስሉ ወጣቶች በየ ቦታው
ማየት የተለመደ ሆኗል:: ያመማቸው እስከ
መስል ቃላቱን እየጎተቱ አፉን እንዳልፈታ ሕ
ፃን እየተኮላተፉ የሚናገሩ ወጣቶች በየቦታው
አሉ:: በዚህ ለዛ ባጣ አነጋገር ላይ እንግሊዘኛ
ቃላት አክለውበት ሀበሻ ይሁኑ ፈረንጅ
ወይም ዐረብ የማይ ታወቁ ወጣቶች ቤተ
ክርስቲያን አካባቢም አይጠፉም::

እንዲህ ያሉ ወጣቶች ሳያውቁት ሀበሻዊ
አነጋገራቸውን ደርባባ የሆነ የቃላት አጠቃቀ
ማቸውን ይረሳሉ:: ትውፊት ሥርዓት ይገ
ሳሉ:: «መድሽ» ብሎ መድኃኔዓለምን መጥራ
ት ትልቅ ስሕተት ነው:: እንዲህ ሊሳሳቱ
ይችላሉ:: ከዚህ ሌላ ከቀደሙ አባቶች ጋር
ተቀምጠው ማውራትና መረዳዳት አይች
ሉም:: ቋንቋ ቸው ጉራ ማይሌ ስለሚሆ
መግባት ይከብ ዳቸዋል:: ከዚህ አንጻር ሠለጠ
ን ብሎ በፈ ረንጆቹ የአነጋገር ዜማ እያቀ
ማጠሉ ንግግርን ጉራማይሌ ማድረግ
ለክርስትና ማነቆ እንዳይሆን ያስፈራል::

ከብዙ በጥቂቱ «ዘመናዊነት» በክርስትና
ላይ እያመጣ ያለውን ፈተና ለማየት ሞክረ
ናል:: በአግባቡ ከተጠቀምንበት አገልግሎ
ታችንን ሊያፋጥንልን ይችላል:: ነገር በአግ
ባቡ ባለመጠቀማችን ጉዳት እያስከተለብን
ነው:: ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው ያገኘውን ሁሉ
እየተቀበለ በዘመናዊነት ሰበብ ክርስትናው
እንዳይናጋበት መጠንቀቅ አለበት:: ሥልጣ
ኔው በሃይማኖቱ ላይ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ
እንዳያደርግ በእያንዳንዱ ጉዞው ራሱን መመር
መር ይገባዋል:: በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳች
ሁን መርምሩ፤ መባላችንስ ለዚህ አይደል?
2ቆሮ.13÷5::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔ*




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ

## /1932 - 1982 ዓ.ም/

ዲ.ስሎሞን ወንድሙ

/የመጨረሻ ክፍል/



*ዲ.ስሎሞን ወንድሙ ባለፉት ሦስት ተከታታይ እትሞች ስለ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ዜና ሕይወትና ሥራዎች ጽሑፎችን አገላብጦ ፣ አባቶችንና ደቀ መዛሙርታቸውን ጠይቆ ያዘጋጀውን ጥናታዊ ጽሑፍ በስፋት አቅርበልናል። ባለፉት ሁለት እትሞች በወጡት የብፁዕነታቸው ታሪክ ላይ ዲ.ስሎሞን የጽሑፎቹ አዘጋጅ እንደሆነ ባለመግለጣችን ይቅርታ እየጠየቅን በዚህ እትም የመጨረሻውን ክፍል እናቀርባለን። መልካም ንባብ።*

### *3.10 የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ሐዋርያዊ ፍሬ*

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን በማሰባሰብ በየክረምቱ ያስተምሩ ነበር። "በሕይወተ ሥጋ እስከነበሩበት ሐምሌ 1982 ዓ.ም ድረስ በሦስት ጊዜያት 69 የዩኒቨርስቲና የኮሌጅ ተማሪዎችን በማስተማር ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት አብቅተዋል። ዛሬ በመላው ሀገሪቱ ባሉት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ መንፈሳዊ ጉባኤያትን በማቋቋም ተማሪዎችን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በማዘጋጀትና በመጽሔት፣ በጋዜጣ፣ በካሴት፣ በመጻሕፍትና በበራሪ ወረቀቶች ምእመናንን በማገልገል ላይ የሚገኘው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳንንም በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ውስጥ የጠነሰሱት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ነበሩ።"

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው ምሁር፣ ረቂቅና በሳል የአመራር ብቃት ያላቸው አስተዳዳሪ፣ አስተዋይና አርቆ አሳቢ የቤተ ክርስቲያን አባት ብቻ ሳይሆኑ ልዩ የሆነ የጽሑፍ ተሰጥኦ የነበራቸው ደራሲና የታሪክ ተመራማሪም ነበሩ። በአንደበታቸው የሚገልጡትን ጣፋጭ ትምህርታቸውን በተባ ብዕራቸው ውብ በሆኑ ቃላት፣ ዘወትር ከኅሊና ሊጠፉ በማይችል ሥዕላዊ አገላለጥ ለትውልድ ለማስተላለፍ የበቁ ድንቅ አባት ነበሩ። መጽሐፎቻቸው ውስብስብ የሆነውን የታሪክ ሒደት አብራርተው፣ ሁሉን ነገር በሥፍራው ተገኝተው የሚያዩትን ያህል ግልጽ አድርገው የሚያሳዩ፣ ከገጽ ገጽ ልብን የሚያንጠለጥሉ፣ ስሜትን የሚሰርቁ፣ የማንነትን ዱካ የሚያመለክቱ ማንኛውም ሰው ሊያነባቸውና ሊረዳቸው የሚችሉ በመሆናቸው ከፍተኛ ተወዳጅነትን አግኝተዋል።

ብፁዕነታቸው እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘእንዚናዙ ነገረ መለኮትን አብራርተው ባፍ በመጣፍ ያስተማሩ፣ ለወጣቱ ማንነት የሚጨነቁ፣ ለነገ የሚጠቅመውን ነገር ሥራ መፍታት በማይወዱት እጆቻቸው ስምንት መጻሕፍትን ያዘጋጁ አባት ነበሩ።

የታተሙት መጻሕፍቶቻቸው:-

1. መሠረተ እምነት ለሕፃናት :- ትምህርተ ሃይማኖትን ለማስተማር የተዘጋጀ፣
2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ :- ከዘመነ ብሉይ እስከ አለንበት ጊዜ ድረስ የተጓዘችበትን ሂደት፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን መሠረተ እምነትና ትውፊታዊ ሥርዓት እንዲሁም የኢኩሜኒዝምን መሠረተ ሀሳብ የሚያብራራ ፣
3. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ - የቤተ ክርስቲያን ትርጉምና አመሠራረት፣ ጉዞና መሰናክሎች፣ የተዋሕዶ እምነት የትምጣንና ትምህርትን በሰፊው ያስረዳል።

*ሳይታተሙ የቀሩት መጽሐፎቻቸው ደግሞ :-*

1. *ሥርዓተ ኖሎት*
2. *ነገረ ሃይማኖት*
3. *ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን*
4. ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ
5. የሰንበት ት/ቤት መመሪያና
6. ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ የተባሉት ናቸው።

*ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተናገሩአቸው በርካታ ድንቅ አባባሎችም ነበሩዋቸው። ለአብነት ያህልም:-*

* ስለ እመቤታችን መናገር የምንችለው ስለ ሰውና ስለ እግዚአብሔር ስናውቅ ብቻ ነው።

* የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በመስቀል ላይ ስለሆነ ፈተና ይበዛባታል። ስለዚህ ከግል ሕይወታችሁ ይልቅ የቤተ ክርስቲያናችሁን አቋም አጠናክሩ።

* ሰው ፍላጎቱን ካላሸነፈ የእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም።

* ሥጋዊ ፍላጎቶችን ማሸነፍ ለአክሊለ ሕይወት የሚያበቃ ሰማዕትነት ነው።

* ኢትዮጵ ለእግዚአብሔር የምሥጢር ሀገር ናት፤ በማለት የተናገሯቸውን መጥቀስ ይቻላል። /አሸናፊ፣ 1992፣ ገጽ 16/





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሕፃናት በሚኖሩበት "አብዮታዊት ኢትዮጵያ ሕጻናት አምባ" ውስጥ በኮሙኒዝም ፍልስፍና ተኮትኩተውና ታንፀው ህልዎተ እግዚአብሔርን እንዳያውቁ ተደርገው የነበሩትን ወገኖች በክርስትና ለማነፅና በሃይማኖት ለማሳደግ ከነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሣ በፈቃደ እግዚአብሔር በዚያን ዘመን ሊታሰብና ሊሞከር የማይችል ታላቅ ሥራ በአምባው ውስጥ ሠርተዋል::

ብፁዕነታቸው በሕጻናት አምባው ውስጥ ለሚገኙት ሠራተኞችና ተማሪዎች የቀብር ቦታ እንዲያገኙ ለማድረግ ፊርማ እንዲያሰባስቡላቸው የመነሻ ሀሳብ ያቀርባሉ:: ፊርማው ተሰባስቦ ሲመጣላቸው በየደረጃው ከሚገኙት የመንግሥት ባለሥልጣናት ዘንድ በመቅረብና በመነጋገር በሕፃናት አምባ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ፈቃድ ያገኛሉ:: ከዚያም ሐምሌ 15 ቀን 1982 ዓ.ም ሕፃናት አምባ ውስጥ የደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የመሠረት ድንጋይ ካኖሩ በኋላ በሥፍራው ለተሰበሰበው ሕዝብ ሲያስተምሩ "ሰው የሚፈልገውን ከፈጸመ የሚጠብቀው ሞቱን ነው" በማለት ዛሬ ድረስ ለብዙዎች የሚገርም ነገር ተናግረዋል:: ማታ ደግሞ ወደ ዝዋይ ገዳም ተመልሰው ከሠርክ ጸሎት በኋላ "ልጆቼ÷ ዛሬ ያገኘነውን ቦታ የእኛ አቅም አይችለውም:: ነገር ግን እኛ እንጀምራለን÷ፈጻሚ እግዚአብሔር ነውና እርሱ ይፈጽመዋል:: ከእንግዲህ ጊዜአችንን ግማሽ በዝዋይ፣ የተቀረውን ግማሽ ጊዜ ደግሞ ሕፃናት አምባ አድርገን እንሠራለን::" በማለት ተናግረው ነበር::

## 3.11 የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ድንገተኛ ዕረፍት

ሐምሌ 22 ቀን 1982 ዓ.ም ጠዋት ለቤተ ክርስቲያን አስደንጋጭና እጅግ አሳዛኝ ዕለት ነበር:: ምእመናን፣ ካህናት፣ መነኮሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ዘግናኝና ጆሮን ጭው የሚያደርግ መርዶ የሰሙበት ዕለት፣ የለቅሶና የዋይታ፣ የድንጋጤና የረብሻ ቀን ነበር:: በዕለቱ የሆነውን ነገር የሰማ ሁሉ የሰማውን ለማመን ግራ ተጋብቶ፣ በጭንቀት ተውጦ፣ በፍርሃት ተይዞና የሚናገረው ጠፍቶበት በየፊናው ዕንባውን በጉንጮቹ ላይ ያፈሳል፤ አንዳንዱ በድንጋጤ ክው ብሎ ዕንባው ደርቋል፤ ከወዲያ ወዲህ ይራወጣል:: ሁሉም አንገቱን ደፍቷል:: ቀና ብሎ የሚያይ አልነበረም:: ብቻ የእጆቹን መዳፍ እያፋተገ በደረሰበት መሪር ኀዘን ባለበት ይወዛወዛል::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሐምሌ 22 ቀን 1982 ዓ.ም ከጠዋቱ 1:30 በመቂ ደብረ አሚን ቅዱስ ጊዮርጊስና በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ለሚገኙ ምእመናን ትምህርተ ወንጌል ለመስጠት ሲሄዱ በድንገተኛ የመኪና አደጋ በተወለዱ በ50 ዓመታቸው እስከ ኅልፈተ ዓለም ሳይነቁ አንቀላፉ:: ላይ ባንኑ አሸለቡ:: ያ በርቀት የተያዘ ዕቅድ በአጭር ተቋጨ፣ ያ ሁሉ ዕረፍት የሌለው ሩጫ በሞት ተገደበ፤ ያ ብሩህ ሐሳብ በድንገት ከሰመ:: ከብፁዕነታቸው ጋር ለአገልግሎት አብረው ሔደው የነበሩት ዲያቆን ጳውሎስ በቀለና የመኪናው አሽከርካሪ ዲያቆን ኤፍሬም ዘውዴም በደረሰው አደጋ በለጋ ዕድሜያቸው በመንገድ ላይ አለፉ::

ሐምሌ 23 ቀን 1982 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የአድባራትና የገዳማት አስተዳዳሪዎችና ካህናት እንዲሁም ምእመናን በተገኙበት በዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ መቅደስ ውስጥ ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል::

ዘመን ሲያነሣት፣ ዘመን ሲጥላት፣ ገጽታዋን አንዴ ሲያስከፋት፣ አንዴ ሲያስውባት የኖረችው ዝዋይ በስንት የደከሙላትና የደከሙባት አባት ጥለዋት እንዳይሄዱ፣ የማይጠገቡትንና የሚሳሳላቸውን አባት በጉያዋ ቀብራ ሕዝብ አስለቀሰች፤ የልጆቿን አንገት አስደፋች፤ ቅስማቸውን ሰብራ ተስፋቸውን ባዶ አደረገች:: ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለኮርስ የሄደው ዘነበ ደስታ በቋጠረው ስንኝ የኀዘን ስሜቱንና በክፉ ጠባይዋ የታዘባትን ዝዋይ እንዲህ በማለት ገልጿል::

### ዋ ! ዝዋይ

ጎርጎርዮስ የኦርቶዶክስ ብርሃን  
አንተ ምሁር የሲኖዶስ ልሳን  
ወዴት ነው የምትሄደው ትተኸን  
እንዲህ ከሆነማ ስለምን ጠራኸን?!  
ተናገሪ ተዋሕዶ ተናገሪ ኦርቶዶክስ  
ጨለማ ውጦሻል የለም ጎርጎርዮስ::  
ሕፃኑን ወጣቱን ሰብስበህ  
ስትመግበው ከጥበብ ማር ወተትህ  
እንግዲህ ሳትመጣ ተመልሰህ::  
ሄድክ ሳትነግረን ጎርጎርዮስ ሊቀ ኢትዮጵያ  
የመረመርከውን ታሪክ ከአውሮፓ ከእስያ::  
ዋ! ዝዋይ ማንን ነው የቀበርሽው?!  
ያን..ትልቁን ዋርካ ለአንቺ ጥላ የሆነውን?!  
ንዳዱን ሐሩሩን ያስተካከለውን?!  
ወይስ ትቢያ ገላሽን አረንጓዴ ያለበሰሽን?!  
እረ ማንን ነው?! ተናገሪ ወፎች ወቀሱሽ::  
መጠጊያ አጥተዋል ልባቸው ተከፋ  
ክንፋቸው ሲሰበር ዜማቸው ሲጠፋ፤  
ዋ! ዝዋይ እውነት አይምሰልሽ  
ፍሬ አፍርቶአል ዋርካው ከንቱ ነው ድካምሽ  
አይሆንልሽም ከቶ በከንቱ ተጣደፍሽ::

በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ድንገተኛ ዕረፍት የተሰማቸውን ጥልቅ ኀዘን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በቅኔ ያቸውና በድርሰታቸው ገልጠውታል:: አንድ አባት "ጎርጎርዮስን የመሰለ ምሁርና መናኝ አባት ቀርቶ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ አባት ሲታጣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ጉዳት አለ:: የእሳቸው ደግሞ ከዚህ የከፋ ነው:: በተለይ ሰው ያመርቱባት የነበረችው የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ ቤተ ኀዘን መስላ ስትታይ ቤተ ክርስቲያናችን እጅግ አዝናለች፤ ብፁዕነታቸውን አጥታለችና::" በማለት ኀዘናቸውን ሲገልጹ ሌላው አባት ደግሞ "ዋ ! ያን ሁሉ ጸጋ፣ ያን ሁሉ ዕውቀት፣ ያ ሁሉ ተሰጥዖና ትጋት . . . ፍቅርና ትኅትና፣ አስተውሎትና ቀናነት፣ ያንንስ የሚያክል ግርማ ሞገስ እንደ ምናምንቴ መሬት ትጫነው ይሆን?!" በማለት መሪር ኀዘናቸውን ገልጠዋል::

በዝዋይ ገዳም የሚገኙት ተማሪዎች ከደረሰባቸው መሪር ኀዘንና ከባድ ጉዳት እንዲጽናኑ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስና ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ እስከ አርባ ቀን መታሰቢያ ድረስ በገዳሙ ተቀምጠው ሲመክሩአቸውና ሲያበረታቱአቸው ሰንብተዋል:: ከዚያም በኋላ የተለያዩ አባቶች በገዳሙ እየተገኙ በተለይ አባ ማርቆስ ከሻሸመኔ እየመጡ የራሳቸውን መሪር ኀዘን በልባቸው አምቀው ሌሎችን ሲያጽናኑ፤ አንዳንዴ ደግሞ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ላይመለሱ እንደ ሄዱ፣ ዳግም በአካለ ሥጋ ላይገናኙ እንደ ተለዩአቸው ሲያስቡ ራሳቸው አልቅሰው ሌሎችንም ያስለቅሱ ነበር::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በዝዋይ ሕፃናት አምባ ሐምሌ 15 ቀን 1982 ዓ.ም የመሠረት ድንጋይ ባስቀመጡ በሳምንቱ በዕረፍተ ሥጋ ቢለዩም የደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ግንባታ በጥቂት ወራት ውስጥ ተጠናቅቆ በኅዳር ወር 1983 ዓ.ም ተባርኮ ቅዳሴ ቤቱ ሊከበር ችሏል::




ከአምባው በተሰጠው በግምት አንድ ጋሻ መሬት ላይ ከብት በማደለብ፣ ፍየል በማርባት፣ ሙዝና ቦለቄ በማምረት፣ ዘመናዊ የንብ ዕርባታ በማ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ካሂድ፣ ወፍጮ ቤትና ንዋያተ ቅድሳት መሸጫ ሱቅ በመክፈት ከፍተኛ የልማት እንቅስቃሴ በማከናወን ላይ ይገኛል:: ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ድካማቸውና ምኞታቸው ከንቱ አልቀረም:: ቤተ ክርስቲያኑ የኢኮኖሚ ችግር የለበትም:: የሚተዳደረውም በዝዋይ ገዳም ሥር ነው:: የዝዋይ ሕፃናት አምባ ክርስቲያኖች ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በአምባው ያበሩትን የወንጌል ፋና በማዘከር በአምባው ውስጥ የመታሰቢያ ሐውልት አቁመውላቸዋል::



## 3.12 በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ታስበው ሳይሠሩ የቀሩ ዕቅዶች

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ለቤተ ክርስቲያን አያሌ ጠቃሚ ተግባራትን ፈጽመዋል:: ከዚያም ባሻገር ዛሬ የሚተገብራቸው አጥተው በወረቀት ላይ ሠፍረው የቀሩ ብዙ ዕቅዶች ነበሩአቸው:: ለአብነት ያህልም:-

1. የካህናት ማሠልጠኛዎችን ቁጥር ከፍ በማድረግ ያሉትንም ማሠልጠኛዎች አቅም ወደ ኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ደረጃ ለማሳደግና ሥርዓተ ትምህርት በማዘጋጀት ከየአህጉረ ስብከቱ የሚመጡትን ካህናት በብቃትና በጥራት ማሠልጠን የሚቻልበትን ሁኔታ ያስቡ ነበር::
2. በዜግነት ኢትዮጵያዊ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ተከታይ የሆኑትን የውጭ ዜጎች ነፃ የትምህርት ዕድል በመስጠት በዝዋይ ገዳም ውስጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት በራሳቸው ቋንቋ እንዲማሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹ ነበር::

"የብፁዕነታቸው ዓላማ ቤተ ክርስቲያናችን እንድታስተምራቸው ለሚጠይቁ ሁሉ ይልቁንም ለአፍሪካውያን እናት ሆና ፈጥና እንድትደርስላቸው ማዘጋጀት ነበር::" /ስምዐ ጽድቅ - 1993 ዓ.ም/

3. ብፁዕነታቸው "እናንተ የቤተ ክርስቲያን የስስት ልጆች፣ የቤተ ክርስቲያን ችግኞች ናችሁ" በማለት የሚያበረታቷቸውን ወጣቶች ከተለያዩ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች በማሰባሰብ ያለምንም ተጨማሪ በጀት አሠልጥነው በማስመረቅ ነገ ቤተ ክርስቲያንን ምንም ክፍያ ሳይጠይቁ ከራሳቸው ደመወዝ ቤተ ክርስቲያንን እየረዱ፣ ለካህናት ደመወዝ እየከፈሉ በነፃ የሚያገለግሉ የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑ ዲያቆናትና ካህናት ለመፍጠር ከፍተኛ ዕቅድ ነበራቸው:: ይህን ለማሳካት ተማሪዎቹን ከምንጫቸው ላይ /ከዩኒቨርሲቲና ከኮሌጅ/ ትኩረት ሰጥተው ነበር:: ለፈጣሪያችን ክብር ምስጋና ይግባውና ዛሬ በማኅበረ ቅዱሳን አማካይነት ይህ ዕቅዳቸው ከሞላ ጎደል ተግባራዊ ሆኗል::
4. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከዝዋይ ገዳም በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው በደሴተ ገሊላ የሴቶች ገዳም ለመገደም ከፍተኛ ምኞት ነበራቸው:: ለዚህም ከሰበታ ቤተ ደናግል ጠባባት ገዳም መነኮሳዪያት አምጥተው ለሚመሠረተው ገዳም በመምህርነትና በእመምኔትነት አሠልጥነዋቸው ነበር::
5. ብፁዕነታቸው ለገዳሙና ለዝዋይ ከተማ ነዋሪዎችም አገልግሎት የሚሰጥ ዳቦ መጋገሪያ ቤት ለመሥራት፣ እንዲሁም ከአንድ ጤና ጣቢያ በስተቀር ሆስፒታል ለሌላት የዝዋይ ከተማ ተጨማሪ የጤና ጣቢያ በገዳሙ ውስጥ በማቋቋም ለገዳሙ መነኮሳት፣ ሕፃናትና የአካባቢው ሰዎች በቂ የሕክምና አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ አቅደው ነበር::
6. በተለያየ ዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ የገዳሙ ሕጻናት፣ ዲያቆናትና መነኮሳት በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ እንዲሆኑ ዘመናዊ ትምህርት የሚማሩበት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማሠራት ዕቅድ ነበራቸው::
7. ዘመናዊ ትምህርት ለተማሩ መነኮሳት የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል በመስጠት ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር የሚቻልበትን ሁኔታም አቅደው ነበር:: /አሸናፊ፣ 1992 ዓ.ም. ገጽ 40 - 41/

## ማጠቃለያ

ክርስትና ውጣ ውረድ የበዛበት ሕይወት በመሆኑ ካሰቡት ለመድረስ፣ ሰማያዊውን ርስት ለመውረስ የዓይን አምሮት፣ የሥጋ ፍላጎት ሳያቸንፋቸው ለአክሊለ ሕይወት የበቁትን ቅዱሳን አበውጽናት በማሰብ፤ ከሚታየው ይልቅ የማይታየውን ነገር የሚያስተውሉበት ሕይወት ነው::

ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በመልካም ግብራቸው የምታስባቸው፣ በአባትነታቸው የምትኮራባቸው አያሌ ቅዱሳን አባቶች የሞሉባት፣ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመናት ሁሉ ታላላቅ ሰዎችን የማያሳጣት የጼጋው ግምጃ ቤት ናት::



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

በዘመናችን ከተነሡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አንዱ ነበሩ:: ብፁዕነታቸው በተሰጣቸው ጸጋ ሁሉ እግዚአብሔርን ያገለገሉ፣ በትምህርታቸውና በትሩፋታቸው የሰዎችን ሕይወት ያጣፈጡ፣ በኃጢአት የጎሰቆሉትን ሰዎች በቅድስናና በንጽሕና ያስጌጡ፣ በኃጢአት ባሕር ተዘፍቀው የሕይወት መልሕቅ ለተሰ በረባቸው የሕይወት መርከብ ሆነው፣ ብዙዎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን ያወጡ የማይጠፋ ፋና የተዋሕዶ መቅረዝ ነበሩ::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በዕረፍተ ሥጋ ከተለዩን ከአሥር ዓመታት በላይ ቢያስቆጥሩም መልካም ግብራቸው፣ ሕያው ስማቸው ዛሬም በብዙዎች ኅሊና በጉልህ ተቀርጾ ሲታወስ ይኖራል:: የብፁዕነታቸው ሕይወት ለብዙዎች የአንደበት መክ ፈቻ ቃል፣ የሐሳብ ማስረገጫ ምስ ክር፣ የሥራ መንደርደሪያ የአፈጻጸማቸው መመሪያ ሆኗል:: ብዙ ጸሐፍት ስለ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በየድርሳናቸው ብዙ ዘግ በዋል፤ በንግግራቸውም ብዙ ነገ ሮችን ጠቅሰዋል:: ለአብነትም ያህል:-

«ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ከአምስት በላይ ቋንቋዎችን የሚያውቁ እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን ወክለው በበርካታ ጉባኤያት የተሳተፉ፣ ታላቅ ፋይዳ ያላቸውን ጥናታዊ ጽሑፎች ያቀረቡ አባት ነበሩ:: የቀድሞው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ዋና ፀሐፊ የነበሩት የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ ማር ጎርጎርዮስ ለጉባኤው ምስክርነት ሲሰጡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ የወንጌል ሐዋርያ አግኝታለች:: በበረሃ ሳይቀር በጎቹን የሚጠብቅ መልካም እረኛን አግኝታለች::" /አሸናፊ ዱጋ ፣1992፣ ገጽ 11/

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ሦስት የጃማይካ ዲያቆናትን በዝዋይ ገዳም በእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተምረው ለመዓረገ ቅስና አብቅተዋል:: ይህን አስ መልክቶ ቄስ ወልዴ ዳዊት በምዕራቡ ዓለም አህጉረ ስብከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ጥቅምት 30 ቀን 1980 በላኩት ደብዳቤ "...ብፁዕነትዎ ሦስቱን የጃማይካ ዲያቆናት ተቀብለው ለማሠልጠን ባደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽዖ በጃማይካ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ወንዶችና ሴቶች ልጆችዎ በታላቅ ደስታና አድናቆት ስሜታቸውን ገልጠዋል:: ለካሪቢያን ሕዝብ ባደረጉት መልካም ሥራ "ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ" የሚለው ስምዎት በብዙዎች አንደበት ዘወትር የሚጠራ የተወዳጅ ቤተሰብ ስም እንደሆነ ብዙዎች ነግረውኛል::" በማለት ጽፈ ውላቸዋል::

ሌላው ጸሐፊ ደግሞ "ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እንደ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በትምህርታቸውና በስብከታቸው፣ በድርሰታቸውና በሌላውም ሥራቸው ሁሉ "ከሣቴ ብርሃን" ነበሩ:: .... የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ታላቅ ሰውነት በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ባገኙት ዕውቀት ብቻ አልነበረም:: ልዩ የንግግር የስብ ከትና የማስተማር ስጦታ ከእግዚአብሔር የተሰ ጣቸው ታላቅ አባት ነበሩ:: በዚህም ስጦታ ቸው ቤተ ክርስቲያን ያጣችውን ታላላቅ ሰዎች ወክለው የምእመናንን ልብ የሚያጽናኑ አባት ስለነበሩ ቤተ ክርስቲያናችን እኒህን አኩሪና መመኪያ፣ በአጭር ጊዜ ምትክ የማይገኝላቸውን ታላቅ አባት በማጣትዋ ኀዘንዋ እጅግ ከፍ ያለ ነው::" በማለት ጽፈዋል:: /ዜና ቤተ ክርስቲያን ፣ጳጉሜ 1 ቀን 1982 ዓ.ም/

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የምታስባቸው፣ ምእመናን ዘወትር የሚያስታውሷቸው፣ መምህራን ሊቃውንት ዘወትር የሚያደንቋቸው ታላቅ አባት በመሆናቸው "ስመከ ሕያው ዘኢይመውት - /ስምህ የማይሞት ሕያው ነው/" ተብለው ዘመናዊ የቀለም ት/ቤት በስማቸው የተሰየመላቸው ሲሆን በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የስብከተ ወንጌል አዳራሾችና በምሁር ገዳም ኢየሱስ የሚገኘው የእጠንግዳ ማረፊያ አዳራሽም "ጽርሐ ጎርጎርዮስ" ተብለው በስማቸው ተጠርተዋል::

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ በዘመነ ኮሙኒዝም በማይደፈረውና በጣም በሚፈራው በዝዋይ በየአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሕፃናት አምባ ውስጥ ለነበሩት ክርስቲያኖች የወንጌል ብርሃን በማብራታቸውና የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መሠረት በመጣላቸው የመታሰቢያ ሐውልት በአምባው ውስጥ የቆመላቸው ሲሆን ለወንጌል አገልግሎት ወደ መቂ ሲፋ ጠኑ በድንገተኛ የመኪና አደጋ ከደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር በወደቁበት ሥፍራም - በመቂ ወረዳ መቶ አርባ በሚባለው አካባቢ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በመታሰቢያነት ታንጾ ላቸዋል:: የብፁዕነታቸው ድንቅ የተጋ ድሎ ሕይወት በዘመኑ ለምንገኝ ክርስቲ ያኖችና በአገልገሎት ለሚፋጠኑ አባቶችና ወንድሞች እንዲሁም ለሚመጣው ትውልድ የአባቶቹን ማንነትና ምንነት ለማሳወቅ ዜና ሕይወታቸው በተለያዩ ጸሐፍት በትምህርትነት ተጽፏአል:: የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ የሩጫቸው ቅድሚያ የድካማቸው በረከት ለዘወትር ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::

## ዋቢ ጽሑፎች


ሐመር /1985/ ጥር

መጽሔተ ትምህርት /1951/ ሐምሌ

መጽሔተ ዓምደ ሃይማኖት /1990/ ግንቦት

ስምዐ ጽድቅ /1989/ ሐምሌ

ስምዐ ጽድቅ /1993/ ጥር

አሸናፊ ዱጋ /1992/ አቡነ ጎርጎርዮስ ማን ናቸው? አዲስ አበባ፣ ማኅበረ ጎርጎርዮስ ዘደብረ መዊዕ

አባ ጎርጎርዮስ /1986/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት

አእምሮ ወንድምአገኘሁ /1952/ "አዲሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር" ትንሣኤ የሃይ አምስት ዓመት መንፈሳዊ እርምጃ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት፣ ገጽ 13 -15

ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ /1982፣ ጳጉሜ 1 ቀን/ "ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ አረፉ" ፣ ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ፣ ገጽ 1፣9

ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ /1989/ አዲስ አበባ፣

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ድምፀ ተዋሕዶ /1983/ ሐምሌና ነሐሴ

Abba Gorgorious (1988 "Social Ministry of the Ethiopian Orthodox Church in the past and the present." paper presented a Paris

Ashentfi Duga (1999) "Hi Grace Abune Gorgorious II Hi contribution to the Ethiopian Orthodox Tewahido Church." Unpublished thesis HolY Trinity College pp. 6 –42

Damite Asfaw (1994) "A Biography of Abune Tekle Haimanot" pp. 28 – 48
Addis Ababa University Addis Ababa

Merid Wolde Aregay (1996 "The Missionary Factor in Ethiopia" Papers from a symposium on the impacts of European Mission on Ethiopia society, Lund University.


ወይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

| ተ.ራ ቁጥር | ቃለ ምዕዳን የተደረገላቸው ሰዎች ሰዎች ስም ዝርዝር | ቃለ ምዕዳን የተደረገበት ቀን | ቃለ ምዕዳኑ የተደረገበት ቦታ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መልከ ጸዴቅ /ብፁዕ አቡነ / | 12/06/93 | አዲስ አበባ | ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ የመጀመሪያ ተማሪዎች አንዱ የነበሩ ከብፁዕነታቸው ተምረው ለምንኩስና፣ ለጵጵስና ማዕረግ የበቁ የብፁዕነታቸው የበኩር የመንፈስ ልጅ ናቸው:: ዛሬ በሀገረ ስብከታቸው በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ስም የሚጠራ የሰብከተ ወንጌል አዳራሽ፣ ት/ቤትና እንግዳ መቀበያ አዳራሽ በመታሰቢያነት ያቆሙ አባት ናቸው:: |
| 2 | መሸ በከንቱ /አባ/ | 28/06/93 | አዲስ አበባ | በ1970 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተመሠረተው የፍቅር ወሰላም የባሕታውያን የአንድነት ማኅበር ሰብሳቢ፣ በዝዋይ ገዳም ገብተው በነበሩበት ጊዜ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ችግር የፈጠሩት ባሕታውያን ሰብሳቢና ከሣሽ የነበሩ ናቸው:: ዛሬ በአዲስ አበባ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሰባኬ ወንጌል ናቸው:: |
| 3 | ሚካኤል ገብሩ /አባ/ | 10/07/93 | አዲስ አበባ | በዝዋይ ገዳም የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ደቀ መዝሙር የነበሩ፣ አሁን በቅድስት ሥላሴ ኮሌጅ የቲዎሎጂ የአራተኛ ዓመት ተማሪ ናቸው:: |
| 4 | ሳሙኤል አረጋኸኝ /አቶ/ | 03/06/93 | አዲስ አበባ | በዝዋይ ገዳም የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ደቀ መዝሙር የነበሩ፣ አሁን በታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም በሊቀ ጉባኤነት የሚያገለግሉ ናቸው:: |
| 5 | ተረፈ አስፋው አቶ | 26/06/03 | ዝዋይ | ከገዳሙ መመሥረት ጀምሮ ለ34 ዓመታት በጥበቃ ሥራ ያገለገሉ፣ ማሠልጠኛው በተረሳበትና ጠያቂ ባጣበት ዘመን በታማኝነት ሲጠብቁ የነበሩ፣ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ወደ ዝዋይ ሲመጡም በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ እየተላላኩ ብፁዕነታቸውን ሲያገለግሉ የነበሩ፣ አሁንም በገዳሙ በጥበቃ ሥራ ላይ በማገልገል ላይ የሚገኙ ናቸው:: |
| 6 | ታመነው /አባ/ | 26/06/93 | ዝዋይ | ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከመርሐቤቴ አምጥተው ያስተማሩአቸው፣ በገዳሙ በንብረት ክፍል ኃላፊነት ሲያገለግሉ የቆዩና በዝዋይ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን በአስተዳዳሪነት የሚያገለግሉ አባት ናቸው:: |
| 7 | ኤልያስ /ብፁዕ አቡነ/ | 02/06/93 | አዲስ አበባ | በዝዋይ ገዳም ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ዘንድ የተማሩና ለማዕረገ ጵጵስና የደረሱ አባት ናቸው:: |
| 8 | ኃይለ ገብርኤል ይትባረክ /ቀሲስ/ | | አዲስ አበባ | በዝዋይ ገዳም ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ዘንድ ሄደው የተማሩ፣ በተለያዩ ጊዜያት ብፁዕነታቸውን እየፈለጉ እየሄዱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሲወያዩ በብፁዕነታቸው የሚታዘዙትን ይፈጽሙ የነበሩ ደቀ መዝሙራቸው ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ የደብረ ምጥማቅ ቅድስት ሰዓሊተ ምሕረት ማርያምና ክርስቶስ ሠምራ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ናቸው:: |
| 9 | ክፍለ ዮሐንስ መኮንን /ንቡረ ዕድ/ | 30/05/93 | አዲስ አበባ | ታዋቂ የቤተ ክርስቲያን የቅኔ መምህር ሲሆኑ የብፁዕነታቸውን ትምህርት ናፍቀው ለአራት ዓመት ከ6 ወር ባለቤታቸውን ትተው፣ ልጆቻቸውን ጥለው፣ ቤታቸውን ዘግተው ወደ ዝዋይ የመነኑ፣ የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በሚገባ ተከታትለው በኀሊናቸው እንደ ፊልም ቀርጸው የያዙ ድንቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ሲሆኑ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በቅኔ መምህርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: |
| 10 | ዘድንግል /አባ/ | 22/06/93 | አዲስ አበባ | በዝዋይ ገዳም ከብፁዕነታቸው ዘንድ የተማሩ፣ወደ ገዳሙ በማዕረገ ዲቁና ገብተው በገዳሙ የመነኩሱ አባት ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የአራተኛ ዓመት ተማሪ ናቸው:: |
| 11 | ደጀኔ ሺፈራው /መምህር/ | 06/07/93 | አዲስ አበባ | ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ዘንድ በገዳሙ የተማሩ፣ የብፁዕነታቸውን ዓላማ የተረዱና በግብር በመፈጸም ላይ የሚገኙ - የቤተ ክርስቲያናችን ሰባኬ ወንጌል ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በሀገር ውስጥና በባሕር ማዶ እየተዘዋወሩ ምእመናን በትምህርተ ወንጌል የሚያንጹ፣ ባፍ በመጣፍ ሀልዎተ እግዚአብሔርን የሚመሰክሩ መምህር ናቸው:: |
| 12 | ገብርኤል /አባ/ | 22/06/93 | አዲስ አበባ | በዝዋይ ገዳም ከብፁዕነታቸው ዘንድ የተማሩ፣ በገዳሙ ማዕረገ ምንኩስናን የተቀበሉ በአሁኑ ጊዜ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚማሩ ናቸው:: |
| 13 | ግዛው /መምህር/ | 26/06/93 | ዝዋይ | በዝዋይ ገዳም ከብፁዕነታቸው ዘንድ የተማሩ፣ በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ ት/ቤት የተመረቁ ፣ በአሁኑ ጊዜ የዝዋይ ወረዳ ቤተ ክህነት ሰባኬ ወንጌልና አሁንም በገዳሙ በማገልገል ላይ የሚገኙ መምህር ናቸው:: |




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org





የአዲስ ዓለም ማርያም ዕቃ ቤት ሲቃጠል እና አባቶችና ምእመናን ሲያለቅሱ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org




## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል-1
## እና
## ምሥጢሬን ላካፍላችሁ ክፍል-1
## ለ3ኛ ጊዜ እንደገና ታትመው ቀርበዋል

በተጨማሪም የማኅበረ ቅዱሳን የአማርኛ ያሬዳዊ መዝሙሮች ከቁጥር 1 እስከ ቁጥር 5 በሲዲ ተዘጋጅተው ቀርበዋል።
ሁሉንም በሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች እና በተለያዩ መዝሙር ቤቶች ውስጥ ያገኟቸዋል።

## የተሰጥኦ መመሪያ ካሴት




### ግብረ ዲቁና

ውተሰጥኦ ሕዝበ መማሪያ በቴፕ ካሴት ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

**ይህ ካሴት**

- ለሰንበት ት/ቤት ወጣቶች መማሪያ፣ ማስተማሪያና ማሠልጠኛ
- ለቅዳሴ መምህራን እንደ ማስተማሪያ መርጃ
- ለምእመናን የቅዳሴ ተሰጥኦ መለማመጃና ማጥኛ

**አዘጋጅ:-**

መምህር የማነ ብርሃን ጌታሁን በአዲስ አበባ ታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ገዳም የቅዳሴ መምህር

**አሳታሚና አከፋፋይ:-**

ማኅበረ ቅዱሳን

በሦስት ክፍል የተዘጋጀውን ኦሪጅናል ካሴት በማኅበሩ የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች እና በተለያዩ መዝሙ[ር] ቤቶች ውስጥ ያገኙታል።

ስልክ 56 51 59 የመ.ሳ.ቁ 80078
E-Mail: eoc-m-kidusan@telecom.net.et.

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ ዋጋ ብር 3.00

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡